ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

# በኦሮሚያ ክልል የተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መፃህፍት ለህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት የሰጡት ትኩረት ፍተሻ

(በ7ኛና በ8ኛ ክፍል ተተኳሪነት)

አማርኛ ቋንቋ በማስተማር ስነ-ዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት

በ

ጌቱ ጫካ ጉሉማ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሰኔ 2013 ዓ/ም

# በኦሮሚያ ክልል የተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መፃህፍት ለህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት የሰጡት ትኩረት ፍተሻ

## (በ7ኛና በ8ኛ ክፍል ተተኳሪነት)


በ

ጌቱ ጫካ ጉሉማ

አማካሪዎች፡-

ምህረት ሰዳሞ (ዶ/ር)

ማንያለው አባተ (ዶ/ር)

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል


የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

አማርኛ ቋንቋ በማስተማር ስነ-ዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሰኔ 2013 ዓ/ም

# ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

በኦሮሚያ ክልል ለ7ኛና ለ8ኛ ክፍል የተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መፃህፍት ለህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት የሰጡት ትኩረት ፍተሻ በሚል ርዕስ አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ስነ-ዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት በጌቱ ጫካ ጉሉማ የቀረበው ጥናታዊ ጽሁፍ የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት በማሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል፡፡

<u>የፈተና ቦርድ አባላት</u>

ዋና አማካሪ ______________________ ፊርማ __________ ቀን ___________

ረዳት አማካሪ ______________________ ፊርማ __________ ቀን ___________

የውጭ ፈታኝ ______________________ ፊርማ __________ ቀን ___________

የውስጥ ፈታኝ ______________________ ፊርማ __________ ቀን ___________

# ማረጋገጫ

በኦሮሚያ ክልል አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ በ2009 ዓ/ም የተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መፃህፍት ለህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት የሰጡት ትኩረት ፍተሻ በ7ኛ እና በ8ኛ ክፍል ተተኳሪነት በሚል ርዕስ ጅማ ዩኒቨርሲቲ የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል በአማርኛ ቋንቋ በማስተማር ስነ-ዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑን የተጠቀምኳቸው ዋቢዎችም በአግባቡ የተጠቀሱ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ጌቱ ጫካ ጉሉማ

ፊርማ ____________

ቀን ___________

# ምስጋና

በመጀመሪያ የነገሮች ሁሉ ባለቤት የሆነው ፈጣሪዬ እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ፡፡ ይህ ጥናት የተሟላ እንዲሆን ጽሑፉን በማቃናትና በማረም አስፈላጊውን ማስተካከያ ላደረጉና ለረዱኝ ለመምህሬና አማካሪዬ ለዶ/ር ምህረት ሰዳሞ እና ለዶ/ር ማንያለው አባተ ላቅ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ እንዲሁም ለዋቢነት የሚረዱ ጥናታዊ ጽሁፎችን በመስጠት ለተባበሩኝ ለዶ/ር ጥበቡ ሽቴ ምስጋናዬ ይድረስልኝ፡፡ በተጨማሪ የአማርኛ ቋንቋና ስነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል መምህራን ፈጣሪ ይስጥልኝ እላለሁ፡፡

ሌላው ደግሞ ለትምህርቴ ውጤታማነት በሞራልና በሃሳብ አስፈላጊውን ድጋፍ ላደረጉልኝ ቤተሰቦቼ ለውዱ ባለቤቴ ፀሐይ ገብሬና ለብርቅዬ ልጆቼ ለወጣት ቤዛዬ ጌቱ፣ ለናትናኤል ጌቱና ለሳሙኤል ጌቱ ምስጋና ብቻ ሳይሆን ትልቅ ቦታ ድረሱልኝ ኑሩልኝ እላለሁ፡፡

በመጨረሻም ለዚህ ጥናት ጽሁፍ መሳካት አስፈላጊውን ወጪ ለሸፈኑልኝ ለጅማ ዩኒቨርሲቲ ድህረ ምረቃ መረሃ ግብር አስተባባሪዎች ላቅ ያለ ምስጋናዬን እያቀረብኩ በተጨማሪ የዚህን የትምህርት እድል ሰጥቶ ያስተማረኝን የጅማ ከተማ ለፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ ላቅ ያለ ምስጋናዬን ላቀርብ እወዳለሁ፡፡

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ አዘጋጅነት አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ ለ7ኛና ለ8ኛ ክፍል በ2009 ዓ/ም የተዘጋጁት ማስተማሪያ መፃህፍት ለህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት የሰጡትን ትኩረት መፈተሽ ነው፡፡ ጥናቱ የተካሄደው በመማሪያ መፅሃፍቱ ለህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት የሰጡትን ትኩረት ለመለየት የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መገለጫ ከሆኑት ከባህል፣ ከኃይማኖትና ከፆታ አኳያ በመማሪያ መጽሃፍቱ ግብዓት የሆኑት የምንባቦች፣ የመመሪያዎችና የመልመጃዎች አቀራረብ የተሰጠው ትኩረት ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነው፡፡ ጥናቱ የተከተለው ዓይነታዊ የምርምር ስልትን ሲሆን በዋናነት ጥቅም ላይ የዋለው የሰነድ ፍተሻ ነው፡፡ ከሰነድ ፍተሻው የተሰበሰቡት መረጃዎች በገላጭ ስታስቲካዊ ዘዴን በመከተል በጥናቱ ውስጥ ከተነሱት መሪ ጥያቄች አኳያ የጥናቱን ዓላማ መሰረት በማድረግ ተተንትነዋል፡፡ የጥናቱ ውጤትም እንደሚያሳየው በሁለቱም መማሪያ መጽሃፍት ለህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መገለጫ ለሆኑት ለባህል፣ ለሃይማኖትና ለፆታ እኩል ትኩረት አልተሰጠም፡፡ ከባህል አኳያ በመማሪያ መፃህፍቱ ከቀረቡት 55 ምንባቦች ውስጥ 7(12.73 በመቶ) ባህልን ያልጠበቁ ሆኖ ተገኝተዋል፡፡ ከሃይማኖት አኳያ ሲታይ አንድ ምንባብና አንድ ምሳሌያዊ አነጋገር የክርስትና ሃይማኖትን ያንጸባረቁ ስለሆነ ተማሪዎቹ የተለያየ ኃይማኖት ተከታይ ሊኖሩ ስለሚችል መታየት እንዳለባቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡ ከፆታ አኳያ የተገኘው ውጤት እንደሚያስረዳው በመማሪያ መፃህፍቱ ቋንቋውን ሊያዳብሩ ይችላሉ ተብለው የቀረቡት ምንባቦች፣ መመሪያዎችና መልመጃዎች ውስጥ በግብዓትነት የቀረቡት ስሞች፣ ግለ-ታሪኮች፣ ግሶች፣ ሀረጎችና ዐረፍተ ነገሮችን በተደረገው ፍተሻ የተገኘው አማካይ ውጤት 20.03 በመቶኛ የወንድ ፆታ አመልካች ስሞች፣ ግሶች፣ ሀረጎችና ዐረፍተ ነገሮች ከሴት ፆታ ብልጫ እንዳላቸው ለማየት ተችሏል፡፡ ከዚህ የምንረዳው የፆታ እኩልትን ያልጠበቀ ሆኖ መገኘቱን ነው፡፡ በመሆኑም በሁለቱም መማሪያ መፃህፍት ዝግጅት ወቅት የማስተማሪያ ግብዓት የምንባቦች፣ መመሪያዎችና መልመጃዎች አቀራረብ ከህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት አኳያ በመለየት ማሻሻያ ቢደረግ የተሻለ ነው የሚል ጥቆማ ለመስጠት አጥኚው ይወዳል፡፡

# ማውጫ


ይዘት ገጽ

ምስጋና ........ i

አጠቃሎ ........ ii

የሰንጠረዥ ማውጫ ........ vi

ምዕራፍ አንድ፤ መግቢያ ........ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 4

1.3 የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች ........ 6

1.4 የጥናቱ ዋና ዓላማ ........ 6

1.4.1 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች ........ 7

1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 7

1.6 የጥናቱ ወሰን ........ 8

1.7 የጥናቱ ውስንነት ........ 8

1.8 የቁልፍ ቃላትና ሀረጋት ብያኔ ........ 8

ምዕራፍ ሁለት፤ ክለሳ ድርሳናት ........ 10

2.1. ንድፈ-ሃሳባዊ ቅኝቶች ........ 10

2.1.1. የባህል ምንነት ........ 10

2.1.2. ህብረ-ባህላዊነት ........ 11

2.1.3. ህብረ ባህላዊነትና ብዝሃነት ........ 12

2.1.4. ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ትምህርት ........ 16

2.1.4.1. የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ትምህርት ታሪካዊ አመጣጥ ........ 16

2.1.4.2. የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ትምህርት ምንነት ........ 17

2.1.4.3. የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ትምህርት ግቦች ........ 18

2.1.4.4. የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ትምህርት ጥቅሞች ........ 18

2.1.4.5. የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ትምህርት ባህሪያት ........ 19

2.1.5. የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መገለጫዎች ....20
2.1.6. የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ለህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ትኩረት የመስጠት አስፈላጊነት ....22
2.1.7. የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ባህርያት ....23
2.1.8. የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መማሪያ መፃህፍት አዘገጃጀት መርሆዎች....24
2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ....24
3.1. የጥናቱ ንድፍ....30
3.2. የናሙና አመራረጥ ....30
3.2.1. የመማሪያ መፃህፍቱ እና የክፍል ደረጃ አመራረጥ ....30
3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ....31
3.3.1. የሰነድ ፍተሻ ....31
3.4. የመረጃ አተናተን ....31
3.4.1. ከሰነድ ፍተሻ የተገኙ መረጃዎች አተናተን....31
ምዕራፍ አራት፤ የመረጃ ትንተና እና የውጤት ማብራሪያ.... 32
4.1. የመረጃ ትንተና ....32
4.1.1. የመማሪያ መፃህፍቱ አጠቃላይ አደረጃጀት....32
4.1.2. ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን ትኩረት ያደረጉ ምንባቦች....34
4.1.3. የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ጽንሰ ሃሳብ ያላቸው ምንባቦች ትንተና ....43
4.1.4. ከባህል አኳያ ....47
4.1.4.1. ምንባቦች....47
4.1.4.2. መመሪያዎች ....52
4.1.4.3. መልመጃዎች....52
4.1.5. ከኃይማኖት አኳያ ....55
4.1.5.1. ስሞች....55
4.1.5.2. ምንባብ(የግል ታሪክ)....57
4.1.5.3. መመሪያዎች ....58
4.1.5.4. መልመጃዎች....58

4.1.6. ከያታ አኳያ ....................................................................................................59

4.1.6.1. ምንባቦች..........................................................................................59

4.1.6.2. መመሪያዎች ......................................................................................61

4.1.6.3. መልመጃዎች......................................................................................64

4.2. የውጤት ማብራሪያ ..........................................................................................75

ምዕራፍ አምስት፤ ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና የመፍትሄ ሃሳብ.......................................... 78

5.1. ማጠቃለያ......................................................................................................78

5.2. መደምደሚያ...................................................................................................79

5.3. የመፍትሄ ሃሳብ ..............................................................................................80

ዋቢ ጽሁፎች............................................................................................................ 82

አባሪዎች ................................................................................................................ 84

## የሰንጠረዥ ማውጫ


<u>ይዘት</u> <u>ገጽ</u>

1. ሰንጠረዥ፡- 4.1 የመማሪያ መጽሃፍቱ አጠቃላይ አደረጃጀት …….……..…. 32
2. ሰንጠረዥ፡- 4.2 በ7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሃፍ ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን የሚያንጸባርቁ ምንባቦች ማሳያ ……………..….. 35
3. ሰንጠረዥ፡- 4.3 በ8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሃፍቱ ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን የሚያንጸባርቁ ምንባቦች ማሳያ ……………….... 39
4. ሰንጠረዥ፡- 4.4 የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ጽንሰ-ሃሳብ የተንጸባረቀባቸውና ያልተንጸባረቀባቸው ምንባቦች ማሳያ . 44
5. ሰንጠረዥ፡- 4.5 የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መገለጫዎችና የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ግብዓት ከሆኑት ጋር ያላቸው ግንኙነት ማሳያ .. 46
6. ሰንጠረዥ፡- 4.6. በ7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሃፍ ባህልን ያልጠበቁ(ሊቃረኑ) የሚችል ሃሳብ ያላቸው ምንባብ ማሳያ…………………..…. 48
7. ሰንጠረዥ፡- 4.7. በ8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሃፍ ባህልን ያልጠበቁ(ሊቃረኑ) የሚችል ሃሳብ ያላቸው ምንባብ ማሳያ……………………… 50
8. ሰንጠረዥ፡- 4.8. የስሞች አቀራረብ ከሃይማኖት አኳያ ……………………. 56
9. ሰንጠረዥ፡- 4.9 የምንባቦች(ግለ-ታሪኮች) ከፆታ አኳያ ያላቸው ሽፋን ማሳያ. 60
10. ሰንጠረዥ፡- 4.10. የመመሪያዎችና የፆታ ግንኙነት ማሳያ ………..…….. 61
11. ሰንጠረዥ፡- 4.11. የስሞች አቀራረብና የፆታ ግንኙነት ማሳያ ……….….. 65
12. ሰንጠረዥ፡- 4.12. የግሶች አቀራረብና የፆታ ግንኙነት ማሳያ ……………. 66
13. ሰንጠረዥ፡- 4.13. የሀረጎች አቀራረብና የፆታ ግንኙነት ማሳያ ………….. 68
14. ሰንጠረዥ፡- 4.14 የዐረፍተ ነገሮችና የፆታ ግንኙነት ማሳያ ……………... 69

# ምዕራፍ አንድ፤ መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

አንድ ሃገር ህብረ-ባህላዊና ብዝሃዊ ሃገር ነው ለማለት በሃገሪቱ የሚኖሩ ህዝቦች የተለያዩ ባህል፣ ፖለቲካ፣ ኢኮኖሚ፣ መንፈሳዊ፣ አካላዊና ስነልቦናዊ ልዩነት ያላቸው መሆን ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም የአንድ ህብረ-ባህልዊ ሀገር የብዝሃነት መገለጫዎች ወይም የመኖር ምክንያቶች በማህበረሰቡ ውስጥ የተለያየ ባህል፣ ቋንቋ፣ ኃይማኖት፣ ብሔር፣ የቆዳ ቀለም፣ አካል ጉዳተኝነት፣ ኑሮ እና የኑሮ ደረጃ ልዩነቶች መኖር ነው(Liese፣2011)::

የህብረ-ባህላዊነት እና ልሳነ ብዙነት ትምህርት ዓላማ የባህል ልዩነትን በማክበር እና በማጠናከር በትምህርት ስርዓት ውስጥ ህብረ ባህላዊነት የባህል እኩልነትን መርህ መሰረት በማድረግ የሌሎችን የመቀበል፣ የማክበርና ልዩነቶችን የመገንዘብ የሞራል ዝግጅት የሚገልጽ የህብረ ባህላዊ ትምህርት ዘርፍ መሆኑን የዘርፉ ምሁራን ይስማሙበታል፡፡ (ለምሳሌ፡-Banks:2010፣ Scherba:2011፣ Liese:2011 …)

ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት የአንድን ሃገር የባህል፣ የኃይማኖት፣ የጎሳ፣ የብሔርና የቋንቋ ስብጥርን ለመግለጽ የሚውል ነው፡፡ ይህ ስብጥር ለማንነት አዎንታዊነት እንዲኖረው የሚደግፍ የለውጥ ሂደት እንደሆነ በመግለጽ ከላይ የቀረቡትን ሃሳቦች ለማጠናከር ብዙ የዘርፉ ባለሙያዎች በሚከተለው መልኩ ይገልፃሉ፡፡

የሰው ልጆች ካላቸው ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ አካባቢያዊና ኃይማኖታዊ ዳራ ልዩነት የተነሳ ከማህበረሰቡ የወጡ ተማሪዎች መካከል ልዩነት እንዲኖራቸው ምክንያት ሆኗል፡፡ በዚህ ምክንያት በተማሪዎች መካከል የሚፈጠር ልዩነት ደግሞ ህብረ-ባህልዊነትና ብዝሃነት ድምጽ ከተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች እንዲሰማ ምክንያት ሆኗል(Banks፣2006)::

Banks (2010) ሲያስረዱ የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ትምህርት ተማሪዎች በፆታቸው፣ በዘራቸው፣ በቀለማቸውና በማንነታቸው ልዩነት ሳይደረግባቸው በማንኛውም ትምህርት ቤት እኩል የመማር እድል እንዳላቸው ይገልፃሉ፡፡ ህብረ-ባህላዊና ብዝሃዊ ትምህርት በትምህርት ቤቶችና በትምህርት ተቋማት ከዩኒቨርሲቲ እስከ አንደኛ ደረጃ ያሉ ሁሉም

የትምህርት ድርጅቶች እሴቶችና፣ ህግጋቱ፣ ስርዓተ ትምህርቱና የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች መዋቅራዊ አደረጃጀታቸው ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን የሚያንጸባርቁ መሆን አለባቸው በማለት ያስቀምጣሉ፡፡

በማያያዝ Banks (2010) ሲያስረዱ ህብረ-ባህልዊነትና ብዝሃነት ቀጣይነት እንዲኖረው የትምህርት ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ በዚህም የትምህርት ስርዓት በየትኛውም የትምህርት ደረጃ ለሚማሩ ዜጎች ብሔራዊ ቋንቋን ጨምሮ ማህበረሰቡ የሚጋራቸው እሴቶችን መማር ያስችላል፡፡ በተጨማሪም የአፍ መፍቻ ቋንቋን በባህላዊ አውዱ መሰረት ለማጥናት ያግዛል፡፡ እንዲሁም ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ቋንቋና ባህል መልካም ነገሮችን ለመማር አጋጣሚን ይፈጥራል፡፡ ከዚህ የተነሳ ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ለማሕበረሰቡ ተገቢውን ዋጋ ለመስጠትና ለመረዳት፣ የተለያዩ ባህሎችን ለማድነቅ ብሎም ለመማር ያስችላል፡፡ እንዲሁም የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ትምህርት ከተለያዩ ማህበራዊ ቡድኖች (ለምሳሌ ብሔር ብሔረሰብ፣ ኃይማኖት፣ ጾታ፣ እድሜ ወዘተ) የተገኙ ተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለማሟላት ተግባራዊ የሚደረግ ቅንጅታዊና የእርስ በእርስ ትስስር ላይ የተመሰረተ የመማር ማስተማር አስተሳሰብ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

መልካም ባህሪ ወይም አስተሳሰብ ያለውን ማህበረሰብ መመስረት የሚቻለው በተቋማት፣ በባህል ማዕከላት፣ በትምህርት ቤቶች፣ በኮሌጆችና በዩኒቨርሲቲዎች አማካይነት በህዝቦች መካከል ያለውን ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን በተገቢው መንገድ ማንጸባረቅ ሲቻል ነው፡፡ የህብረተሰቡን አባላት ድምጽ፣ ንቅናቄ፣ ፍላጎትና ምኞት ማንጸባረቅ ያልቻለ የትምህርት ስርዓት በሀገሪቱ ዲሞክራሲያዊ የሆነ አንድነት ለማምጣት አያስችልም በማለት ያስረዳሉ(Banks፣2010)፡፡

እንዲሁም Scherba (2011) ሲያስረዱ የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ትምህርት ሚና የተለያየ ባህላዊ ዳራ ያላቸውን ተማሪዎች ወደ አንድ የትምህርት አውድ በማምጣት እኩል የትምህርት እድልና የመማር ተነሳሽነት እንዲኖራቸው ታስቦ የሚቀረጽ የትምህርት ፍልስፍና ነው፡፡ የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ትምህርት ሲቀረጽ ተማሪዎች በትምህርት ቤትም ግንዛቤው እንዲኖራቸው ተደርጎ ነው፡፡ የትምህርት አውዱም ለሁሉም ተማሪዎች እኩል እድል የሚሰጥ ነው፡፡ የተማሪዎችን የመማር ተነሳሽነትን

የሚጨምርና አድሏዊ አመለካከትን እንዲያስወግድ ተደርጎ የሚቀረጽ የትምህርት ፍልስፍና እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ እንዲሁም የተማሪዎችን ባህል፣ ሃይማኖት፣ ቋንቋ፣ ብሔረሰብና ፆታ ወዘተ… ከግምት በማስገባት ሚዛናዊ በሆነ መልኩ ተሰባጥረው መቅረብ ይኖርባቸዋል በማለት ያስረዳሉ፡፡

በሀገራችን ኢትዮጵያም ከተለያዩ ጎሳዎች፣ ዘሮች፣ ኃይማኖቶች፣ ጾታ፣ ብሔሮች እና ከተለያዩ የእድሜ ዳራ የመጡ ተማሪዎችን በአንድ ክፍል ውስጥ ማግኘት የተለመደ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ ምክንያት ትምህርታዊ ልምምዶቹ ተማሪዎች እነዚህን ልዩነቶችን በመቀበልና በማድነቅ፤ እንዲሁም ከጭፍን አስተሳሰቦች በማጽዳት የተማሪዎችን የህብረ-ባህዊነትና ብዝሃነት ግንዛቤን፣ እውቀትንና ክሂልን እንዲያጎለብቱ ሆነው መቀረጽ ይኖርባቸዋል፡፡

እንደ Campbell (2010) የመሳሰሉ የዘርፉ ባለሙያዎች ደግሞ የ21ኛው ክፍለ ዘመን የትምህርት ስርዓት ወደ ትምህርት ገበታ የሚመጡ ተማሪዎችን ማህበራዊ ዳራ፣ ጾታ፣ ኃይማኖት፣ ማህበራዊ መደብ፣ ቋንቋ፣ አካላዊና አዕምሯዊ ችግሮችን ከግምት ውስጥ ሊያስገቡ እንደሚገባ ያስረዳሉ፡፡

ይህም መምህራን የማስተማሪያ ዘዴዎቻቸውን ሊፈትሹ እንደሚገባ ይጠቁማል፡፡ የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ትምህርት ብቃቶችም የመምህሩ የማስተማር ጥረት ውጤቶች ናቸው፡፡ ለመምህሩ እንደመምሪያና አጋዥ የትምህርት መሣሪያዎች የሆኑት ዋንኞቹ ደግሞ መማሪያ መፃህፍት ናቸው፡፡ መማሪያ መፃህፍት በአንድ ሀገር ውስጥ ያለውን ስርዓት ተከትሎ ከሚፈጠሩ ፖሊሲዎች አንዱ ከሆነው የትምህርት ፖሊሲ ማስፈጸሚያ ከሚያገለግሉ ስርዓተ ትምህርት ስር በዋናነት ለትምህርት አገልግሎት ከሚቀርቡ ግብአቶች ዋንኞቹ ናቸው፡፡ ከእነዚህም መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ደግሞ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ተጠሰቃሽ ናቸው፡፡

ቀደም ሲል አጠቃላይ የትምህርት ዓላማ በትምህርት ፖሊሲው ከመካተቱም ባሻገር ስለተግባራዊነቱ በየወቅቱ መገምገምና ክፍተቶችን መሙላት ያስፈልጋል፡፡ የአንድን የትምህርት ዓላማ እንዲሳካ ለመማሪያነት የሚቀርበው የትምህርት ይዘት ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን የተከተለ ቢሆን ተገቢነት ይኖረዋል፡፡ ይህም ሲባል የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ትምህርት ራሱን ችሎ መሰጠት አለበት ማለት ሳይሆን በሁሉም

የትምህርት ዓይነቶች መካተት በሚችልበት ብዝሃነትን በጠበቀ መልኩ እንዲሆን የሚታመን ነው፡፡ ይህንን የትምህርት ስርዓት ከዝቅተኛው የትምህርት ደረጃ ጀምሮ እስከ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ድረስ በትምህርት ይዘት መረጣና አቀራረብ ቢካተት በተማሪዎች ዘንድ የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ግንዛቤያቸውን በማስፋትና መሰረታዊ እውቀት እንዲኖራቸው ያግዛል፡፡

ከእነዚህ ዓለም አቀፍ ዕይታዎች በመነሳት ይህ ህብረ-ባህላዊ እና ልሳነ ብዙነት ትምህርት በሃገራችን ኢትዮጵያ ህገ መንግስታዊ እውቅና ተሰጥቶት በትምህርት ፖሊሲው ተካቶ በክልሎች ብሔር-ብሔረሰቦች ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት ተቀርፆለት፤ መፃህፍት ተዘጋጅተው በመደበኛም ሆነ ቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ትምህርቱ እየተሰጠ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

Tomlinson (2001) ሲጠቅሱም መማሪያ መጽሃፍት አስፈላጊ ከሆኑ የማስተማሪያ ቁሶች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ውጤታማነትንና ቀጣይነትን ለማረጋገጥ ከመጥቀማቸውም በላይ ተማሪዎች በስርዓት እንዲመሩና መሻሻል እንዲያሳዩ ይረዳል፡፡ መምህራን በሚያስተምሩት ትምህርት መስክ እንዲዘጋጁና ተማሪዎችም የተማሩትን መከለስ እንዲችሉ ያግዛሉ በማለት የመማሪያ መጻህፍትን ጠቀሜታ ይገልፃሉ፡፡

የዚህ ጥናት አላማም በ2009 ዓ.ም ተዘጋጅተው በማስተማሪያነት እያገለገሉ ያሉትን የ7ኛና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍትን ተተኳሪ በማድረግ ለተማሪዎች ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን በማስገንዘብ ረገድ ያላቸውን ትኩረት ፈትሿል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በኦሮሚያ ክልል የተለያዩ ማህበረሰቦች ተሰባጥረው የሚገኙ በመሆኑ ለተማሪዎቹ ተዘጋጅቶ የሚቀርበው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሃፍ ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን ታሳቢ ያደረገ ሊሆን ይገባል፡፡ ስለሆነም በመፃህፍቱ ለማስተማሪያነት ሊካተቱ የሚገባቸው የቋንቋ ማስተማሪያ ምንባቦች፣ መመሪያዎችና መልመጃዎች ሲዘጋጁ ህብረ-ባህለዊነትና ብዝሃነትን ያካተቱ መሆኑ የተማሪዎችን የመማር ሂደት እንዲዳብር ያግዛል፡፡

አንበሳው (2009)፣ Thomas (2014) ጠቅሶ እንዳስቀመጠው ከሃገራችን ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት መምህራን እና ተማሪዎች የመማሪያ መፃህፍት ጥገኛ ናቸው፡፡ ከሃገራችን የእድገት ደረጃ አንፃርም ሌሎች ዘመናዊ የትምህርት መሳሪያዎች ለመጠቀም የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ባለመኖሩ መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች የመማሪያ መፃህፍት ጥገኛ ለመሆን ተገደዋል፡፡ በዚህም የተነሳ መማሪያ መፃህፍቱ መምህራን ምን እና እንዴት ማስተማር እንዳለባቸው አቅጣጫ አመልካች ዋነኛ የትምህርት መሳሪያዎች ስለሆኑ ከህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መገለጫዎች አኳያ እንዴት ተዘጋጅተው እንደቀረቡ መፈተሸ አስፈላጊ ነው ሲሉ ይገልፃሉ፡፡

አጥኚው በጅማ ዩኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ የአንደኛ ዓመት ድህረ-ምረቃ ተማሪ በነበረበት ወቅት ይሰጥ የነበረው የህብረ-ባህላዊነትና ልሳነ ብዙነት ትምህርት ለኮርሱ ማሟያነት በተሰጠው የግል ስራ ምክንያት የተነሳ በርዕሰ ጉዳዩ ላይ የተደረጉ ጥናቶችን ለማግኘት በጅማ ዩኒቨርሲቲ ቤተ መፃህፍት  እና በበይነ መረቦች ላይ ባደረገው ፍተሻ በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ላይ የክሂል አቀራረቦችን በተመለከተ በርካታ ጥናቶች ተደርገዋል፡፡ ነገር ግን በመማሪያ መፃህፍቱ ዝግጅት ከህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ጋር በተያያዘ የተደረጉ ጥናቶች በቂ አይደሉም፡፡

ከዚህ ጥናት ጋር በተያያዘ በ9ኛ እና በ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ላይ የተደረጉ ጥናቶች የተወሰኑ ሲሆን (አጥኚው ያገኘው) በአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል በ7ኛ እና በ8ኛ ክፍል አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መፃህፍት ላይ የተደረገው ጥናት በቂ ነው ብሎ ስለማያምን (በሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ላለመኖሩ እርግጠኛ አይደለም፡፡) በእነዚህ መማሪያ መፃህፍት ላይ ጥናት ማድረጉ አስፈላጊ እንደሆነ በማመኑ እና በ7ኛ እና በ8ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት በዚህ ርዕስ ረገድ የሚታዩ ክፍተቶችን ለመሙላት ነው፡፡

እንዲሁም አጥኚው የተዛማጅ ጥናቶችን ቅኝት ባደረገበት ወቅት ያገኛቸው ጽሁፎች በአንደኛ ደረጃ በሁለተኛ ሳይክል በ7ኛ እና በ8ኛ ክፍል የተጠኑ ጥናቶችን ብናይ በፍቃዱ እንዳለ (2012) "በኦሮሚያ ክልል ለ7ኛ እና ለ8ኛ ክፍል የተዘጋጁት የአማርኛ መማሪያ መጽሃፎች ህብረ-ባህላዊነትን በማስረፅ ረገድ ያላቸውን አስተዋጽዖ ፍተሻ" በሚል ርዕስ በጅማ ዩኒቨርሲቲ የተሰራ ሲሆን ጥናቱ የሚያተኩረውም ለማስተማሪያነት ከቀረቡት ግብዓቶች በምንባቦችና በመልመጃዎች ውስጥ የሚገኙት የብሔር ስሞችና

የፆታ አቀራረብ ምን ያህል ተገቢ ናቸው የሚል የቅርብ ጊዜ ጥናት በመሆኑና ከባህልና ከኃይማኖት አንፃር ጥናት የተደረገ ባለማግኘቱ(ላለመኖሩ እርግጠኛ አይደለም) ይህንን ክፍተት ለመሙላት በመታሰቡ ይህ ጥናት ትኩረት የሚያደርግባቸው ለማስተማሪያነት ከቀረቡት ምንባቦች፣ መመሪያዎችና መልመጃዎች የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መገለጫ ከሆኑት መካከል ከባህል፣ ከኃይማኖትና ከፆታ አንፃር የተሰጠውን ትኩረት በመፈተሽ ከባህልና ከኃይማኖት አኳያ ክፍተቱን ለመሙላት በመታሰቡ ለጥናቱ መነሻ ምክንያት ሆኖታል ፡፡

እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን ክፍተቶች ለመሙላት የተካሄደው ጥናት ለሚከተሉት መሪ ጥያቄዎች መልስ ሰጥቷል ተብሎ ይታሰባል፡፡

## 1.3 የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች

ይህ ጥናት በዋናነት በ2009 ዓ.ም የታተሙ የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ለተማሪዎች ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን ከማስገንዘብ አንፃር የሰጡት ትኩረት ምን ይመስላል? የሚለውን መሪ ጥያቄ በመመለስ ለሚከተሉትን ንዑሳን ጥያቄዎች መልስ ሰጥቷል፡፡

1. በመማሪያ መፃህፍቱ የቀረቡት ምንባቦች፣ መመሪያዎችና መልመጃዎች የተማሪዎችን ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ከማስገንዘብ አንፃር ለባህል የተሰጠው ትኩረት ምን ያህል ነው?
2. በመማሪያ መፃህፍቱ የቀረቡት ምንባቦች፣ መመሪያዎችና መልመጃዎች የተማሪዎችን ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ከማስገንዘብ አንፃር ለኃይማኖት የተሰጠው ትኩረት ምን ያህል ነው?
3. በመማሪያ መፃህፍቱ የቀረቡት ምንባቦች፣ መመሪያዎችና መልመጃዎች የተማሪዎችን ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ከማስገንዘብ አንፃር ለፆታ የተሰጠው ትኩረት ምን ያህል ነው?

## 1.4 የጥናቱ ዋና ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ አዘጋጅነት በ2009 ዓ.ም ታትሞ በስራ ላይ ያሉትን “አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች

የተዘጋጁትን የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መፃህፍት የትምህርት ይዘቶች ለህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት የሰጡትን ትኩረት መፈተሽ ሲሆን የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

### 1.4.1 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች

- በመማሪያ መፃህፍቱ የቀረቡት ምንባቦች፣ መመሪያዎችና መልመጃዎች የተማሪዎችን ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ከማስገንዘብ አንፃር ለባህል የሰጡትን ትኩረት መለየት፡፡
- በመማሪያ መፃህፍቱ የቀረቡት ምንባቦች፣ መመሪያዎችና መልመጃዎች የተማሪዎችን ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ከማስገንዘብ አንፃር ለኃይማኖት የሰጡትን ትኩረት መለየት፡፡
- በመማሪያ መፃህፍቱ የቀረቡት ምንባቦች፣ መመሪያዎችና መልመጃዎች የተማሪዎችን ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ከማስገንዘብ አንፃር ለፆታ የሰጡትን ትኩረት መፈተሽ፡፡

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

የጥናቱ ጠቀሜታ የመማሪያ መፃህፍት ላይ ጥናት መደረጉ ደካማና ጠንካራ ጎኖቹን በመለየት ደካማ ጎኖቹ መታረም እንዲችሉ ግብዓት በመሆን ያገለግላሉ፡፡ በመሆኑም በክልል ደረጃ የተዘጋጁት መማሪያ መፃህፍት በህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ላይ ያላቸውን ትኩረት መፈተሽ ወይም ጥናት ማድረግ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡፡

ለዩኒቨርሲቲው ከህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ጋር ተያያዥነት ላላቸው ጥናቶች አካዳሚው ትኩረት እንዲሰጥ እና ለውጤታማነቱ እገዛ ያደርጋል፡፡ ለመምህራንም የጥናቱ ውጤት መምህራን የትምህርት አሰጣጥ ዘዴአቸውን ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን በመጠበቅ እንዲያስተምሩ ያግዛቸዋል፡፡ ተማሪዎችም ቋንቋውን የመማር ፍላጎታቸው እንዲጨምር እና በህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ዙሪያ መልካም ግንኙነት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ እንዲሁም ትምህርታዊ መስተጋብራቸውን ያሳድጋል፡፡ በህብረ-ባህላዊነትና

ብዝሃነት ዙሪያ ጥናት ለሚያደርጉ አጥኚዎች እንደ ተጨማሪ መረጃ ምንጭነት ያገለግላል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

የዚህ ጥናት ወሰን በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ በ2009 ዓ/ም ተዘጋጅተው በስራ ላይ ያሉት አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ማስተማሪያነት በማገለገል ላይ ያሉት የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የተማሪው መማሪያ መፃህፍት እና የመምህሩ መምሪያ ላይ የሚያተኩር ሲሆን በመማሪያ መፃህፍቱ የቀረቡት ምንባቦች፣ መመሪያዎችና መልመጃዎች ለተማሪዎች ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን ለማስገንዘብ በባህልና በኃይማኖት ዙሪያ ጥናት ማድረጉ በክልሉ የተለያዩ ማህበረሰቦች በመኖራቸው የተለያየ ዳራ ያላቸው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ስለሚገኙና ከዚህ በፊት በተደረጉ ጥናቶች ውስጥ ያልተካተቱ በመሆኑ የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መገለጫ ከሆኑት መካከል ከባህል፣ ከኃይማኖትና ከፆታ አንፃር የተሰጠውን ትኩረት ፈትሿል፡፡ ጥናቱ የመማሪያ መፃህፍቱ ከክሂል ይዘት አንፃር የተሰጠውን ትኩረትና ከዚህ በፊት የታተሙትን አልተመለከተም፡፡

## 1.7 የጥናቱ ውስንነት

በዚህ ጥናት ላይ ተጽዕኖ አድርሷል ተብለው የሚታሰቡ ወይም የሚገመቱ የጥናቱ ውስንነቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

መማሪያ መፃህፍቱን ካዘጋጁት ባለሙያዎች እና መሰል የትምህርት ባለሙያዎች መረጃ አለመሰብሰቡ

ከዚህ ቀደም አማርኛ እንደሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች ከ2009 ዓ/ም በፊት የተዘጋጁ መማሪያ መፃህፍትን መዳሰስ አለመቻሉ

## 1.8 የቁልፍ ቃላትና ሀረጋት ብያኔ

በዚህ ጥናት ውስጥ በተደጋጋሚ የተጠቀሱ አጥኚው የተጠቀመባቸው ቃላትና ሀረጋት በጥናቱ ውስጥ ያላቸውን ትርጉም ወይም ብያኔ ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡ እነዚህም፡-

**ባህል፡-** የአንድ ማህበረሰብ አጠቃላይ ማንነትና አስተሳሰብ የሚንጸባረቅበት ማለት ነው፡፡

**ህብረ-ባህላዊ፡-** የባህል፣ የብሔር፣ የቋንቋ፣ የኃይማኖት ወዘተ ልዩነቶችን ማቻቻል ወይም ማስተናገድ የሚያስችል ማለት ነው፡፡

**ብዝሃነት፡-** የባህል፣ የብሔር፣ የቋንቋ፣ የኃይማኖት ወዘተ በአንድ ማህበረሰብ ወይም ሀገር ውስጥ መኖር ማለት ነው፡፡

**ኃይማኖት፡-** ፈጣሪ መኖሩን አምኖና ተቀብሎ የምስጋና፣ የአምልኮት እና የአከባበር ሂደት ያለው እምነት ወይም ተቋም ማለት ነው፡፡

**ፆታ፡-** በማህበረሰቡ ዘንድ ያለውን የወንድነትና የሴትነት አመለካከት ወይም ማህበረሰቡ ለወንድና ለሴት ፆታ የሚሰጠውን ግምት የሚመለከት ነው፡፡

**እንደሁለተኛ ቋንቋ፡-** በአፋን ኦሮሞ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ወይም አማርኛን በሁለተኛ (በተጨማሪ) ቋንቋነት የሚማሩ ማለት ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት፤ ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ምዕራፍ የጥናቱን ዓላማ መሰረት በማድረግ በጥናቱ የሚገኙ የሚሰበሰቡ መረጃዎችን ለመተንተን የሚያስችሉ ንድፈ ሃሳባዊ ጽንሰ-ሃሳቦች እና ከጥናቱ ርዕስ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ጥናቶች እንደሚከተለው ለመዳሰስ ሞክሯል፡፡

## 2.1. ንድፈ-ሃሳባዊ ቅኝቶች

### 2.1.1. የባህል ምንነት

ህብረ-ባህላዊነት የሚለውን ጽንሰ ሀሳብ ከመዳሰሳችን በፊት ባህል የሚለውን ጽንሰ ሀሳብ ማየት አስፈላጊ ነው፡፡

ባህል ለሚለው ጽንሰ ሃሳብ በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ያለው ወጥ የሆነ ብያኔ መስጠት አይቻልም፡፡ ቃሉ የተለያዩ ምሁራን እንደየሙያቸው የሚበይኑት በመሆኑ ቁርጥ ያለ ብያኔ መስጠት አስቸጋሪ ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል ቃሉ የያዘው ጽንሰ ሀሳብ ብያኔ በሙያ ብቻ ሳይሆን በጊዜና በቦታ ጭምር የተገደበ ነው፡፡ የተለያዩ ማህበራዊ አካባቢዎች እና ጊዜያትም የየራሳቸው የሆነ ባህል አላቸው፡፡ በያኒዎችም ቃሉን የሚበይኑት ካሉበትና በደንብ ከሚያውቁት ማህበራዊ አካባቢና ጊዜ ጋር በሚስማማ ሁኔታ ነው፡፡ በዚህ የተነሳ የሚሰጡትም ብያኔዎች የተለያዩ ናቸው፡፡

Taylor (1994) ስለ ባህል የተሰጡ የተለያዩ ብያኔዎችን እንደሚከተለው አስቀምጠዋል፡፡ እነሱም፡- ባህል ሰፊ እና ውስብስብ ሲሆን ልማድ፣ ወግ፣ ፀባይ፣ ዕምነት፣ ዕውቀትና ጥበብ ያካትታል፡፡ ባህል የአንድን ማህበረሰብ ማንነት የሚያንጸባርቅ፣ ማህበረሰቡ የሚጋራቸው እሴቶች፣ እምነትና የአስተሳሰብ ባህሪያዊ ሂደት ተዋጽኦ ነው፡፡ እንዲሁም ባህል የአሰራር ልምዶችን፣ አስተሳሰብን፣ ቁሳዊ ውጤቶችን ሁሉ ይመለከታል፡፡ በመሆኑም እነዚህ ነገሮች የማህበረሰቡ አባል በመሆን የሰው ልጅ የሚለምዳቸው ነገሮች ናቸው፡፡

የተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት (ዩኒስኮ) እ.ኤ.አ. በ1982 ሜክሲኮ ላይ ባደረገው ጉባኤ በተደረሰው ስምምነት ባህል የሰው ልጅ ሰብዓዊና ምክንያታዊ ፍጡር እንዲሆን ያስቻለው ወይም ከሌሎች ፍጡራን የተለየ እንዲሆን

ያደረጉት ዋንኛዎቹ አካላዊ፣ ስነምግባራዊና በአዕምሮ ዕውቀት ራስን የማሰልጠን ሂደቶችን የሚያጠቃልል ጽንሰ ሃሳብ የያዘ ነው፡፡ እንዲሁም የአንድ አካባቢ ማህበረሰብ ከሌላው ተለይቶ የሚታወቅባቸው የአነጋገር ዘይቤዎች፣ እምነቶች፣ ትውፊቶች፣ በአጠቃላይ ህሊናዊና ቁሳዊ ሀብቶችን የሚያካትትና የማህበረሰቡ የጋራ እሴት የሆነ የአስተሳሰብ፣ የአኗኗርና የአሰራር ይትበሃልን የሚያመላክት መሆኑ ነው፡፡

ባህል አንዱ ማህበረሰብ ከሌላው የሚለይበት አስተዳደራዊ፣ ኃይማኖታዊ፣ ስነልቦናዊ፣ ቋንቋዎች፣ ታሪክ እና ስነ-ቃሎቻቸውና ኃይማኖታዊ ክንዋኔዎቻቸው፤ እንዲሁም ከልደት፣ ከሰርግና ከሞት ጋር የተያያዙ ስርዓቶች፣ በማህበረሰቡ መካከል ያለው የመተጋገዝ ስርዓት፣ አስተዳደራዊ ዘዴዎች፣ ባህላዊ የጤና እንክብካቤ ስልቶች እና ሌሎችን የሚያጠቃልል ሰፊ ጽንሰ ሀሳብ ነው፡፡

ባህል ከሰው ልጅ ጋር እጅግ የጠበቀ ቁርኝት ያለው በመሆኑ የባህል መነሻው ግለሰብ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ማህበረሰቡ ሊቀበለው ይገባል፡፡ ይህም የሰው ልጅ ሀብት ብቻ ነው፡፡ የባህል ባለቤት ለመሆን በደም የሚተላለፍ ሳይሆን የማህበረሰቡ አባል መሆን አስፈላጊ ነው፡፡ የሰውን ልጅ ከባህል ለይቶ ማየት አይቻልም፡፡ ምክንያቱም በህሊና ውስጥ ያለው ነገር በተግባር ማለትም በሚሰራው ስራ ሲገለጽ ስለሚታይ ነው፡፡ እያንዳንዱ ማህበረሰብ የራሱ የሆነ ባህል አለው፡፡ ለእነዚህ የተለያዩ ባህሎች መኖር ለህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መከሰት ምክንያት ሆኗል፡፡

ባጠቃላይ ባህል የሰዎችን አመለካከት፣ ባህርይና እሴቶች ሁሉ ይቀርፃል፡፡ ይህንን ለማግኘት በማህበራዊ ህይወት ውስጥ ማለፍ ግድ ነው፡፡

### 2.1.2. ህብረ-ባህላዊነት

አስቀድመን ስለ ባህል የተወሰነ ግንዛቤ እንዲኖረን የተለያዩ መረጃዎች ተጠቅሰዋል፡፡ አሁን በመቀጠል ስለ ህብረ-ባህላዊነት ምንነት የተገለጹ እሳቤዎችን እናያለን፡፡

Ramsey, et al (2003) ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት የተለያዩ ባህሎች ስብጥር መኖር፣ ሁሉም ባህሎች በርዕዮተ ዓለማዊ አስተሳሰብ በእኩልነት የሚታዩ መሆናቸውን የሚያምን ፍልስፍና ነው በማለት ያስረዳሉ፡፡

በማያያዝም Richard (2011)፡፡ ህብረ-ባህላዊነት የባህላዊ እምነቶች፣ እሴቶችና ዝንባሌዎች መኖራቸውን እና የእነዚህን ሁነት የሚቃኝ ነው በማለት ይገልፃሉ፡፡ በተጨማሪም ህብረ-ባህላዊነት በተለያዩ ባህሎች ስርዓት ላይ የሚያተኩርና በርካታ ባህላዊ ክስተቶችን የማካተት ወይም የማዛመድ ጉዳይ ነው፡፡ ህብረ-ባህላዊነት ማህበረሰቡ ሊቀበለው የሚገባ ሃሳብ ነው፡፡ ይህ ማለት ሁሉም ባህል እኩል ማህበራዊ ደረጃ እንዳላቸው መቀበልን ያመለክታል፡፡ እንዲሁም የህብረ-ባህላዊነት ጽንሰ ሃሳብ የአንድን ሀገር የባህል እና የጎሳ ስብጥር ለመግለጽ የምንጠቀምበት ቃል ነው፡፡

ከላይ ለማየት እንደተሞከረው ህብረ-ባህላዊ የሚለው ጽንሰ ሃሳብ የተለያዩ ባህሎች ተጣጥመውና ተቻችለው መኖርን፣ አንዱ የሌላውን አክብሮ መቀበልን፣ ልዩነት በራሱ ውበት እንደሆነ የሚያምን፣ ባህሎችን ማወቅ የአመለካከትና የአስተሳሰብ አድማሳችን የሚያሰፋ ዓይነተኛ መንገድ እና የዘመናችን ፍልስፍና መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

### 2.1.3. ህብረ ባህላዊነትና ብዝሃነት

አስቀድመን ስለ ህብረ-ባህላዊነት የተወሰነ ግንዛቤ እንዲኖረን የተለያዩ መረጃዎች ተጠቅሰዋል፡፡ አሁን በመቀጠል ስለ ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት የተገለጹ እሳቤዎችን እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉ ልዩነቶችን የሚቀበል፣ የሚያከብርና ዕውቅና የሚሰጥ ፍልስፍና ነው፡፡ እኛ ሰዎች የተለያዩ ማንነት ቢኖረንም ከህብረተሰቡ ጋር እስካለን ድረስ በህብረተሰቡ ውስጥ የሚኖረንን ማንነት በማስተዋል በመተባበርና በመተጋገዝ ልዩነቶችን በማጥበብ አንድነትን በማስፋት ለህብረተሰቡ የድርሻችንን መወጣት እንድንችል የሚያጠና ነው፡፡

Taylor፣(1994)፡፡ ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ውስጥ ያሉ ልዩነቶችን፣ እኩልነትንና ማንነትን መሰረት በማድረግ የሰጡትን ብያኔዎች ከዚህ ቀጥለን እናያለን፡፡

## ሀ. ልዩነትን ማቀፍ

ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ልዩነትን የሚቀበል፣ የሚያከብርና እውቅና የሚሰጥ ነው፡፡ ልዩነትን በማቀፍ የሰዎች ግላዊም ሆነ ማህበራዊ ማንነት እንዳይጣስና የዳበረ ማህበራዊ አንድነት በጠንካራ መሰረት ላይ እንዲታነጽ የሚሚገታ ፍልስፍና ነው(Taylor፣1994)፡፡

Taylor (1994) ልዩነትን በቀላሉ መረዳት እንድንችል በሁለት ከፍለው እንደሚከተለው አስፍረዋል፡፡ እነሱም፡- አሉታዊ እና አዎንታዊ ናቸው፡፡

**አሉታዊ ልዩነት**፡- መልካም ያልሆነ አመለካከትን ያዘለ የኔነት ብቻ ላይ ያተኮረና ራስን የበላይ አድርጎ የማሰብ፣ ሌላውን የማግለልና የበታች አድርጎ የማየት አመለካከት ነው፡፡ እንዲሁም በማህበረሰባዊ ማንነት ውስጥ ያለው የመረዳትና አንዱ ቡድን ሌላውን የሚያይበት መልካም ያልሆነ አተያይ ነው፡፡

አንድ ማህበራዊ ቡድን በሌላው ላይ ባለው መልካም ያልሆነ አተያይ ላይ አባላቱም ያንን ይዘው መልካም ያልሆነ አተያይ እንዲኖራቸው አንዱ በአንዱ ላይ ተጽዕኖ እንዲፈጥር የሚያደርገው አሉታዊ ልዩነትን የሚያመለክት ነው፡፡ የዚህ ዓይነቱ ልዩነት በሰዎችና በማህበረሰቡ መካከል አለመግባባትና አለመቻቻል እንዲፈጠርና ለግጭቶች መንስኤ ይሆናል፡፡

**አዎንታዊ ልዩነት**፡- ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መሰረቱ አሉታዊ ልዩነቶችን ወደ አንድ ማምጣት ሳይሆን በልዩነቶች መካከል አለመግባባት የሚፈጥረውን አመለካከት በመቀየር በመቻቻልና በመግባባት አንዱ የአንዱን ልዩነት በማክበርና እውቅና በመስጠት አንድነትን የሚፈጥር ማለት ነው፡፡ አዎንታዊ ልዩነቶችን ስናነሳ ስለማንነትና በማንነቶች መካከል ስላለው መልካም ግንኙነትና መተሳሰብ ጭምር ማለታችን ነው ፡፡

## ለ. እኩልነት

ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት አስተሳሰብ ዋናው ነጥብ ልዩነት ተቀባይነትና እውቅና እንዲያገኝና ለሁሉም እኩል እድል የሚሰጥ አስተሳሰብ ነው፡፡ የሰው ልጆችን እኩልነት ለማረጋገጥ ለማንነቱ ክብር፣ እውቅናና ተቀባይነት መስጠት ስንል የሃይማኖት፣ የዘር፣

የቋንቋ፣ የዖታ፣ ማህበራዊ ማንነትና የመሳሰሉትን እውቅና መስጠትና መቀበል ማለት ነው ሲሉ ይገልፃሉ(Tayler፣1994)፡፡

## ሐ. ማንነት

የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ጥናት ዋናው ዓላማ በሀገራችን የተለያዩ ማንነት ያላቸው ቡድኖችና ግለሰቦች በመኖራቸው ብዝሃነት የሚመሰረትበት ማንነት ነው፡፡

ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ተቀባይነትና ተከባሪነት ማግኘቱና ማህበራዊ ፍትህ መንገሱ ላይ ነው አተኩሮ የሚሰራው፡፡ በምድራችን የተለያየ ማንነት ያላቸው ግለሰቦችና ቡድኖች መኖራቸው ደግሞ የብዝሃነት መሰረት ነው፡፡ ስለዚህ የህብረ-ባህላዊነት ጥናት አውራ ጉዳዩ ብዝሃነት የሚመሰረትበት ማንነት ነው በማለት ይገልፃሉ፡፡ ማንነት ተወልደው ባደጉበት ባህላዊ አካባቢ የሚገነባና የሚቀረጽ የግለሰብ ወይም የቡድን መታወቂያ ነው(Tayler፣1994)፡፡

እንደ Tayler አገላለጽ ማንነትን በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ማየት ይቻላል፡፡ እነሱም፡- ግለሰባዊ ማንነት እና ማህበራዊ ማንነት ናቸው፡፡

**ግለሰባዊ ማንነት**፡- ማንኛውም ሰው በተፈጥሮ ከወላጆቹ የሚወርሰው የዘር ሀረግ የእሱነቱ መለያ ነው፡፡ እንዲሁም ባደገበት ማህበረሰብ ውስጥ የሚጋራቸው ባህል፣ ልማድ፣ እምነትና ወግ ይዞ ያድጋል፡፡ ግላዊ ማንነት የእያንዳንዱ ሰው ግለሰባዊ ስብእና፣ ጠባይና ተፈጥሮ ጥምር ውጤት ነው፡፡

**ማህበራዊ ማንነት፡-** ማህበራዊ ማንነት ባለብዙ ገጽታ ነው ይባላል፡፡ ይህም አንድ ሰው የራሱ የሆነ የማንነቱ መገለጫ ስብዕና እና ጠባይ የተፈጥሮ ጥምር ውጤት ነው፡፡ ሰዎች ይህንን ግላዊ ማንነት እንደያዙ ከሚኖሩበትና ከሚሰሩበት ማህበረሰብ ጋር የሚያመሳስላቸው ማንነት ይኖራል፡፡ በቋንቋ፣ በስራ፣ በፆታ፣ በሙያ፣ በኃይማኖት፣ በባህላቸው፣ በሃገራቸው የተነሳ ማህበራዊ ማንነታቸው ይገነባል፡፡

ለማህበራዊ ማንነት መንስኤ የሆኑትን እንደሚከተለው እናያለን፡፡

*ሀ. **ሙያዊ ማንነት፡-** ሰዎች ኑሮን ለማሸነፍ በተለያየ የሙያ ዘርፍ ውስጥ ተሰማርተው የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎችን ያደርጋሉ፡፡ በዚህም የተነሳ ከተሰማሩበት ሙያ አንፃር ሙያዊ ማንነት ይኖራቸዋል፡፡*

*ምሳሌ፡- አንድ/ አንዲት ሰው/ ሴት መምህር ቢሆን ከሙያ አንፃር የመምህርነት ሙያ ማንነት ይኖራቸዋል፡፡*

*ለ. **ቋንቋዊ ማንነት፡-** ከሚገለገሉበት ቋንቋ አኳያ የቋንቋ ማንነት ወይም ከሚናገሩት ቋንቋ አኳያ የዚያ ቋንቋ ተናጋሪ ቡድን ማንነት ይኖራቸዋል፡፡*

*ሐ. **ኃይማኖታዊ ማንነት፡-** አንዲት ሴት ወይም አንድ ሰው ከምትከተለው/ከሚከተለው ኃይማኖት አኳያ ኃይማኖታዊ ማንነት ይኖራታል/ይኖረዋል፡፡*

*ምሳሌ፡- አንድ የክርስትና እምነት ተከታይ ከኃይማኖቱ/ከኃይማኖቷ አንፃር የክርስትና ማንነት አለው/አላት፡፡ አንድ/አንዲት የእስልምና እምነት ተከታይ ከኃይማኖቱ/ከኃይማኖቷ አንፃር የእስልምና ማንነት አለው/አላት፡፡*

*መ. **ባህላዊ ማንነት፡-** አንድ ሰው ከተወለደበት ወይም ካደገበት ማህበረሰብ ጋር በመሆን ከሚያከብረው ወይም ከተቀበለው ባህል አኳያ ባህላዊ ማንነት ይኖረዋል፡፡*

*ሠ. **ፆታዊ ማንነት፡-** ፆታዊ ማንነት መሰረት የሚያደረገው ተፈጥሯዊ ፆታን ነው፡፡ አንዲት ሴት ግላዊ ማንነቷን እንደያዘች ሴት በመሆኗ የሴት ፆታ ማንነት ተጋሪ ናት፡፡ አንድ ወንድ ግላዊ ማንነቱን እንደያዘ ወንድ በመሆኑ የወንድ ፆታ ማንነት ተጋሪ ነው፡፡*

*ረ. **ሀገራዊ ማንነት፡-** ዜጋ ከሆነባት /ከሆነችባት ወይም ከትውልድ ሀገሯ /ሀገሩ አንፃር ሀገራዊ ማንነቷ/ ማንነቱ፣ ወዘተ ይመሰረታል፡፡*

*በማህበራዊ ማንነት ረገድ ሰዎች በተለያዩ መንገዶች ከአንድ በላይ ከሆኑ ቡድኖች ጋር የሚጋሩት ነገር ስለሚኖራቸው ማንነታቸው ብዙ ገጽታ ያለው ይሆናል፡፡*

### 2.1.4. ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ትምህርት

የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ትምህርት ታሪካዊ አመጣጥ፣ ምንነት፣ ግቦች፣ ጥቅሞችና ባህርያት ተዳሰዋል(Banks፣2004)፡፡ እነሱም እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

#### 2.1.4.1. የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ትምህርት ታሪካዊ አመጣጥ

የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ትምህርት አስተሳሰብ የተጀመረው በምዕራቡ ዓለም በ1960ዎቹ ከተነሳው የሲቪል መብቶች ንቅናቄ ወቅት ነው፡፡ በዓለም ይኖሩ የነበሩ አፍሪካውያን መብታችን ይከበር የሚል መሰረታዊ ጥያቄ ይዘው ንቅናቄ ጀመሩ፡፡ ዋናው ጥያቄም መድልዎን ማስወገድና እኩል እድል የሚገኝበትን መብት ማረጋገጥ ነበር፡፡ በዚህ የመብት ንቅናቄ Banks (2004) ሲገልጹ፡-

ሀ. የትምህርት ተቋማት ስርዓተ-ትምህርታቸውን የህዝቦችን ታሪክ፣ ባህል፣ ልምድ፣ ወዘተ በሚያንጸባርቁበት ሁኔታ እንዲያሻሽሉ፤

ለ. ለሚማሩ ልጆቻቸው አርአያ መሆን ይችሉ ዘንድ አፍሪካውያን ከሆኑ ህዝቦች ውስጥ መምህራንንና አስተዳዳሪዎችን የትምህርት ተቋማት እንዲቀጥሩ፤

ሐ. ማህበረሰቡ የትምህርት ተቋማትን የሚከታተልበትና የሚደግፍበት ሙሉ መብት እንዲሰጠው፤

መ. የትምህርት ተቋማት የሚጠቀሙባቸው ማስተማሪያ መፃህፍት ብዝሃነትን በሚያንጸባርቅ አግባብ ተከልሰው እንዲዘጋጁ፣ በዚህ ክለሳ ወቅትም በማህበረሰቡ የሚወከሉ ሰዎች ሙሉና ነፃ ተሳትፎ የሚያደርጉበት መብት እንዲሰጣቸው፣ የሚሉ ዋና ዋና ጥያቄዎችን አንስቶ ነበር( Banks፣2004)፡፡

የሲቪል መብቶች ንቅናቄ በ1960ዎቹ ስለ ትምህርት ላነሳቸው ጥያቄዎች የተሰጠው መልስ በጥናት ያልተደገፈ ነበር፡፡ ምንም ዓይነት በቂ ዝግጅት ሳይደረግ ኮርሶች ተዘጋጁ፡፡ መርሃ-ግብሮች ተዘረጉ፡፡ ከተደረጉትም ውስጥ የህዝብ በዓላትን መጨመርና ህዝቡን ሊያስደስት ይችላል ያሉትን አካተው ትምህርት ቤቶች የማሻሻያ እንቅስቃሴ አደረጉ፡፡

በዛን ወቅት በነበረው እንቅስቃሴ የትምህርትና የፖለቲካ ምሁራን በተሟሟቀ ሁኔታ የህብረ-ባህላዊነት ትምህርት ሊያሳድጉ የሚችሉ ፍልስፍናዎችን ይዘው ብቅ አሉ፡፡ በወቅቱም ጉዳዩ ትኩረት አግኝቶ ስለነበር ለዛሬው ለህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ትምህርት መሰረት ሆኗል፡፡

### 2.1.4.2. የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ትምህርት ምንነት

ህብረ-ባህላዊና ብዝሃዊ ትምህርት አንድ ወጥ የሆነ ሁሉም በጋራ የሚስማማበት ውሳኔ የለውም፡፡ እንደየወቅቱ፣ እንደየዘመኑ፣ እንደየቦታውና እንደየሙያ ዘርፉ በተለያየ ሁኔታ ይነገራል፡፡

Banks (2004) ስለ ህብረ-ባህላዊና ብዝሃነት ትምህርት ምንነት የሚከተሉትን ይገልፃሉ፡፡ እነሱም፡-

ሀ. ስርዓተ ትምህርት ለማሻሻል የተደረገ ንቅናቄ ሳይሆን ሁሉም ተማሪዎች እኩል የመማር እድል እንዲያገኙና በመልካም አስተሳሰብ ተገንብተው ከመድልዖ ነፃ በመሆን ከህብረተሰቡ ጋር የመኖርና አለማቀፋዊ አስተሳሰብን እንዲያዳብሩ የሚያስችል የትምህርት ስርዓት ነው፡፡

ለ. ለተወሰነ ማህበራዊ ቡድን ብቻ የቆመ ሳይሆን ሁሉም ተማሪዎች በቀለም፣ በጾታ፣ በኃይማኖት፣ በእምነት፣ በቋንቋ፣ ወዘተ ምክንያት ከሚፈጠር መድልዖ ነፃ ሆነው እኩል የመማርና የመለወጥ ዕድል የሚያገኙበት የትምህርት ስርዓት ነው፡፡

ሐ. የሁሉም ተማሪዎች ግላዊም ሆነ ማህበራዊ ማንነታቸው የሚጠበቅበት፣ ብዝሃነት ክብርና ዕውቅና የሚያገኝበት የትምህርት ስርዓት ነው፡፡

ህብረ-ባህላዊ ትምህርት በብዝሃነት ውስጥ ላለ ህብረተሰብ ከማንነቱ አንፃር ክብርና ዕውቅና የሚሰጥ፣ ልጆች ከመድልዖ የፀዳ ዕኩል የመማር ዕድል አግኝተው ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያስችል መሰረት የሚጥልና በዴሞክራሲያዊ እሴቶች ላይ የተገነባ የትምህርት ስርዓት ነው፡፡ በሰዎች መካከል የመፈቃቀር፣ የመከባበር፣ የመደጋገፍ አስተሳሰብንና ተግባርን ያዳበረ ዓለምአቀፋዊ አመለካከት ያለው ትውልድ ለመፍጠር የሚያግዝ ነው፡፡

### 2.1.4.3. የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ትምህርት ግቦች

እንደ Scott (2001) አገላለጽ ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ትምህርት እንደ ትምህርት አማራጭ ጉዞውን ሲጀምር መነሻ ግቦቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡ እነሱም፡-

ሀ. ተማሪዎች ስለ ህብረ-ባህል ያላቸውን ዕውቀት ማሳደግ፤

ለ. መድልዎን ማስወገድ፤

መ. በሁሉም ተማሪዎች ዘንድ የመከባበርን ስሜት ማዳበር፤

ሰ. ልዩ ባህላዊ ማንነቶችን መንከባከብና መጠበቅ፤

ረ. ስለ ሰው ልጅ ሀላፊነት መሰማት፤

ሸ. ክብር ለማንኛውም የሰው ዘር የሚል አስተሳሰብ መገንባት፤

ቀ. ባህላዊ ብዝሃነትን መቀበልና ማድነቅ፤

በ. ዘረኝነትን፣ መድልዎን፣ ማግለል፣ ጥላቻን መከላከልና የዴሞክራሲያዊ ተግባር ክሂልን ማዳበር የሚሉት ናቸው፡፡

### 2.1.4.4. የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ትምህርት ጥቅሞች

ከዚህ ቀጥለው የተገለጹት ከህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ትምህርት የረጅም ጊዜ ጥቅሞች መካከል በዋና ዋናነት የሚወሰዱ ናቸው(Banks፣2010)፡፡ እነሱም፡-

ሀ. በሁሉም ዘንድ የአዕምሮ ግንዛቤን ያሳድጋል፡፡ ይህ ደግሞ አዕምሯዊ ሀብት እንዲኖር ያደርጋል፡፡

ለ. ችግሮችን የመፍታት ችሎታን ይጨምራል፡፡

ሐ. ለእኩልነት መከበር ልምድን በመሳደግ በልዩነት ውስጥ የጋራ ግቦች እንዲሳኩ በማድረግ እውቅና ይሰጣል፡፡

መ. መልካም ግንኙነቶችን በመፍጠር መለያየትንና ጥላቻን መቀነስ/ማስወገድ ያስችላል፡፡

ሠ. በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉ ባህሎችን በማሳደግ የህብረተሰቡን ታላቅነት ያጎላል፡፡

### 2.1.4.5. የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ትምህርት ባህሪያት

ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ትምህርት ባህሪያት ዓበይት ጉዳዮች ፅንሰ-ሀሳብ፣ የትምህርት ማሻሻያ ንቅናቄ እና ሂደት ናቸው፡፡ በዚህ ብያኔ ውስጥ ሶስት ዓበይት ጉዳዮች በማንሳት ይገልፃሉ(Banks፣2010)፡፡ እነሱም፡-

#### ሀ. ህብረ-ባህላዊና ብዝሃነት ትምህርት እንደ ፅንሰ ሀሳብ

ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ትምህርት በምንም ዓይነት ምክንያት ልዩነት ሳያደርግ ሁሉም ተማሪዎች እኩል የመማር መብት ሊኖራቸው ይገባል የሚል ፅንሰ ሃሳብ ነው፡፡

ተማሪዎች ልዩነታቸው ለግጭት መንስኤ ሳይሆን በመከባበርና በመቻቻል የሚማሩ አስተሳሰባቸውን አስፍተው ልዩነትን የሚቀበሉ፣ የሚያከብሩና በልዩነታቸው የሚኮሩ እንዲሆኑ ተደርጎ የተመሰረተ አስተሳሰብ ነው፡፡

#### ለ. ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ትምህርት እንደ ትምህርት ማሻሻያ

ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ትምህርት የትምህርት ማሻሻያ ንቅናቄ ነው ሲባል የትምህርት ተቋማት በብዝሃነት ውስጥ ያሉ ተማሪዎች እኩል የመማር እድል የሚያገኙበትን እድል መፍጠር እንደሚገባቸው የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ የትምህርት አማራጭ የሚተጋው በስርዓቱ ውስጥ ለውጥ በማምጣት ብቃትና የመተባበር ስሜት ያለው ትውልድ ለመፍጠር ነው፡፡ ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃዊነት ትምህርት፤ የትምህርት ተቋማት ባህልና ማህበራዊ መዋቅር ብዝሀነትን ያለ መድልዖ በሚያስተናግዱበት ሁኔታ እንዲሻሻል የሚጥር የትምህርት ስርዓት ነው፡፡

#### ሐ. ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ትምህርት እንደ ሂደት

ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ትምህርት እኩልነትን ባንድ ጊዜ የሚያመጣ ሳይሆን ቀስ በቀስ በዲሞክራሲያዊ መንገድ በመገንባትና የተረጋጋ አስተሳሰብ ያለው ትውልድ መፍጠር ነው፡፡ ሂደትም በመሆኑ በአጭር ጊዜ ውሰጥ የሚጠናቀቅ አይደለም፡፡ ቀስ በቀስ እያደገ የሚሄድ ነው፡፡

ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ትምህርት የጥናት መስክ ነው፡፡ ዋና ዓላማውም ከተለያዩ የዘር፣ የጎሳ፣ የቀለምና ባህላዊ ቡድኖች ለመጡ ተማሪዎች በብዝሃነትና ዲሞክራሲያዊ ህብረተሰብ ውስጥ ውጤታማ ሆኖ ሊሰራ የሚችል ዕውቀት፣ ዝንባሌና ክህሎት እንዲያገኙ ማድረግ ሲሆን ከተለያዩ ሰዎች ጋር በመስማማት ለጋራ ጥቅም የሚሰራ የሲቪክ ማህበረሰብን ለመፍጠር ነው(Banks፣2010)፡፡

## 2.1.5. የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መገለጫዎች

አንዲት ሃገር ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ያለባት ሀገር ናት ለማለት በሃገሪቱ የሚኖሩ ህዝቦች የተለያዩ ባህላዊ፣ መንፈሳዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ አካላዊ እና ስነ-ልቦናዊ ልዩነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ስለዚህ የአንድ ሃገር ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ለመኖሩ መገለጫዎች በማህበረሰቡ ውስጥ የተለያዩ ባህል፣ ቋንቋ፣ ኃይማኖት፣ ብሔረሰብ፣ አካል ጉዳተኝነት፣ የቆዳ ቀለም የኑሮና የትምህርት ደረጃ ልዩነቶች መኖራቸው ነው፡፡

የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መገለጫዎች በርካታ ቢሆኑም ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑትን ባህል፣ ኃይማኖትና ፆታ ብቻ የተመረጡበት ምክንያት ሁሉንም መጠቀሙ ጥናቱን የተንዛዛ ሊያደርገው ይችላል ተብሎ በመታሰቡ የተመረጡት ከዚህ ቀጥሎ ቀርበዋል፡፡

### ሀ. ባህል

ለህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ምክንያት ከሆኑት ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ባህል መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም የመማሪያ መፃህፍት በሚዘጋጁበት ወቅት የተማሪዎችን ባህላዊ ዳራ መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ባህሎች በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ በግብዓትነት ቢካተቱ የተማሪዎችን የትምህርት ፍላጎት ከማሳደጉም በላይ በመካከላቸው ያለው ግንኙነት በመግባባት እና በመከባበር ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ያደርጋቸዋል(Banks፣2010)፡፡ በመሆኑም ስለ ባህል ያለውን ሃሳብ በምዕራፉ መግቢያ ላይ በስፋት ለማየት ተሞክሯል፡፡

## ለ. ኃይማኖት

ኃይማኖት ለህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መገለጫ ከሆኑት ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ The World Book Encyclopedia(2001) እንደገለጸው ኃይማኖት የሚለውን ቃል ለመበየን የሚያስችል ቀላልና አንድ ወጥ የሆነ ብያኔ የለም ይላል፡፡ ኃይማኖት ሲባል ረቂቅና ሰፊ የሆነ ጽንሰ-ሃሳብ ያለው በመሆኑ አንድ ወጥ የሆነ ብያኔ ለመስጠት አዳጋች ቢሆንም የማህበራዊ ሳይንስ ምሁራን የሚጋሩት ሃሳብ ወይም ሊያግባባ የሚችል ፈጣሪ ተብሎ የሚታመን ሰማያዊ ኃይል በሚመለከት የሚደረግ የአምልኮ፣ የአከባበርና የምስጋና ሂደት እንደሆነ ነው፡፡

ስለሆነም መማሪያ መጽሃፍ በሚዘጋጅበት ወቅት ጥንቃቄ ሊደረግበት የሚገባው ጉዳይ ኃይማኖት ነው፡፡ በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ ኃይማኖታዊ ጽሁፎች ወይም ስዕሎች በስፋት ባይንጸባረቁም በተዘዋዋሪ ኃይማኖትን የሚመለከቱ ጉዳዮች አይኖሩም ብሎ መገመት ያዳግታል፡፡ በመሆኑም እነኚህ በቀጥታ ኃይማኖታዊ የማይመስሉ ነገር ግን ኃይማኖትን የመደገፍ ወይም የመቃወም አዝማሚያ የሚታይባቸውን ጉዳዮች መለየት እና ተገቢነታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል አንበሳው (2009) Thomas (2010) ጠቅሶ እንዳስቀመጠው::

## ሐ. ፆታ

ፆታ ለህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መገለጫ ከሆኑት ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ The World Book Encyclopedia(2001) እንደገለጸው ፆታ የሚለው ጽንሰ-ሃሳብ ማንኛውም ህይወት ባለው ነገር ሁሉ ዘንድ ያለ ወንድነትን ወይም ሴትነትን የሚመለከት ሆኖ በኢንግሊዘኛው ቋንቋ የተገለጹትን "Sex" እና "Gender" የሚሉትን ሁለት የተለያዩ ጽንሰ-ሃሳብ ያላቸውን ቃላት የሚወክል ነው፡፡ ፆታ ስነ-ህይወታዊ የሆነውን ወንድነት ወይም ሴትነት እንዲሁም በማህበረሰቡ ዘንድ ያለውን ፆታዊ አመለካከት ሁሉ ስርዓት-ፆታ(Gender) በወንድና በሴት ላይ የሚታየውን ስነ-ህይወታዊ ተፈጥሮ ከግምት ያስገባ ሳይሆን ማህበረሰቡ ከሚተዳደርበት ደንብና እምነት አንፃር የሚሰጥ ልዩነት ነው፡፡ በመሆኑም ስርዓት-ፆታ በአንድ ማህበረሰብ ባህል ውስጥ ለወንድና ለሴት ብቻ ተብለውና ተለይተው የተቀመጡ ተግባራትና አመለካከቶችን የሚመለከት ተፈጥሯዊ ያልሆነ ጽንሰ-ሃሳብ ነው(ሂሩት፣2006)፡፡

### 2.1.6. የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ለህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ትኩረት የመስጠት አስፈላጊነት

የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ለቋንቋ ትምህርት ዓላማ ግብ መድረስ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ከፍ ያለ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የአንድን ሃገር ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ሁኔታ ሳያገናዝቡ በዘፈቀደ የተዘጋጁ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ከጥቅማቸው ይልቅ በተማሪዎች ላይ የሚያደርሱት ተጽዕኖ ያመዝናል(ጥላሁን፣1990)፡፡

በማያያዝ አንበሳው (2009) Thomas (2010)ን ጠቅሶ እንዳስቀመጠው በመማሪያ መፃህፍት ለህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ትኩረት መስጠት የሚያስፈልግበትን ምክንያት በሁለት ዋና ዋና ምክንያት እንደሚከተለው ገልጸዋል፡፡

- የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ተማሪዎች ተገቢ፣ ትክክለኛና የራሳቸውን ማንነት በሚያንጸባርቁ የትምህርት ማሳሪያዎች ታግዘው በመማር ፍላጎታቸውን ማሟላት ስለሚፈልጉ በክፍል ውስጥ የሚነሱ ስሞች፣ ምሳሌዎችና ሌሎች ለቋንቋ ትምህርት ማስተማሪያነት የሚቀርቡ ጉዳዮች በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ ቀድመው ሊጠቆሙ ይገባል፡፡
- ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ያላቸው የክፍል ውስጥ ተግባራት፣ መሳሪያዎችና ተሞክሮዎች መኖራቸው የተማሪዎችን የልምድ ልውውጥ ስለሚጨምር ነው፡፡

በሌላ መልኩ የሀገሪቱን የትምህርት ፖሊሲና መርሃ-ትምህርት መሰረት በማድረግ ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን ጠብቀው በባለሙያዎች የሚዘጋጁ የቋንቋ መፃህፍት በሁሉም ተማሪዎች ዘንድ ተመሳሳይ የቋንቋ ይዘቶችን ለማስተማር የሚያስችሉ የክፍል ውስጥ ክንውንን የመወሰን አቅም ያላቸውና ከአንድ የትምህርት ተቋም እስከ ተገልጋዩ ህብረተሰብ ድረስ ላለው ቋንቋ ትምህርት ፍላጎት በተገቢው ሁኔታ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉ እንደሆኑ አንበሳው (2009) ዘውዱ (2007)ን በመጥቀስ ገልጸዋል፡፡

### 2.1.7. የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ባህርያት

የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መገለጫ የሆኑት በቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ በሚካተቱበት ወቅት የመማሪያ መፃህፍቱን ባህሪያት በጠበቀ መልኩ መሆን እንዳለበት ይታመናል፡፡

አንበሳው (2009) ዘውዴ (2007)ን ጠቅሶ እንዳስቀመጠው ለመማሪያ እንዲሆኑ ታስበው የሚዘጋጁ የመማሪያ መፃህፍት የሚከተሉት ባህርያት ሊኖራቸው እንደሚገባ ይገልፃሉ፡፡ እነሱም፡- ተገቢነት፣ እውነተኝነት፣ ግልጽነት እና ተለጣጣቂነት ናቸው፡፡

- ተገቢነት፡- ለቋንቋ ማስተማሪያነት ታስበው በሚዘጋጁ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የተካተቱ ጉዳዮች፤ ከተማሪዎች እድሜ፣ ባህል፣ የክፍል ደረጃ፣ ፆታ፣ ኃይማኖት፣ ብሔር፣ ወዘተ. ጋር የሚጋጩ ነገሮች መኖር የለባቸውም፡፡
- እውነተኝነት፡- በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚቀርቡ ይዘቶች ሁሉ ሰዋሰዋዊም ሆነ እውነታ(ሀቅ) ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ምንም እንኳን የቋንቋ ትምህርት ዓላማ የቋንቋ ትምህርት ክሂሎችን ሰዋሰውና ስነ-ጽሁፍን ማስተማር ቢሆንም ለትምህርቱ በግብዓትነት በሚውሉ ማናቸውም ጉዳዮች ወይም መረጃዎች (ምንባቦች፣ ታሪኮች፣ አሃዛዊ መረጃዎች፣ ስሞች፣ ወዘተ.) ትክክለኛነት ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
- ግልጽነት፡- ለትምህርት የቀረቡ ጉዳዮች ተማሪዎች በቀላሉ እንዲማሩባቸውና መምህራን ደግሞ በቀላሉ እንዲያስተምሩባቸው በማያሻማ መልኩ መዘጋጀት አለባቸው፡፡
- ተለጣጣቂነት፡- በአንድ የመማሪያ መፃህፍት ውስጥ ባሉ የተለያዩ ምዕራፎችም ሆነ አንድ የትምህርት ዓይነት ከተለያዩ የክፍል ደረጃዎች ጋር ያለው ቅደም ተከተል ሳይንሳዊ ሊሆን ይገባል፡፡

### 2.1.8. የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መማሪያ መፃህፍት አዘገጃጀት መርሆዎች

የመማሪያ መፃህፍት በማህበረሰቡ ውስጥ የተስተካከለ አመለካከት እንዲፈጠር ያስችላሉ፡፡ ለምሳሌ፡- ፆታን በተመለከተ ለወንዶችና ለሴቶች ያላቸው የተሳሳተ ግንዘቤ እንዲስተካከል በማድረግ ረገድ ያላቸው ሚና ከፍተኛ ነው(ሂሩት፣2006)፡፡

ከላይ የተገለጸውን ሃሳብ በመደገፍ አንበሳው (2009) Thomas (2014)ን በመጥቀስ የመማሪያ መፃህፍትን ጨምሮ የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት የትምህርት መሳሪያዎች ሲዘጋጁ ሊከተሏቸው የሚገቡ ሶስት መርሆዎችን እንደሚከተለው አስቀምጠዋል፡፡ እነሱም፡-

- በወንዶችም ላይ ሆነ በሴቶች ፆታን መሰረት ያደረጉ የጥላቻና የንቀት ወይም የድጋፍ አመለካከትን በሚያንጸባርቁ መልኩ መሆን የለባቸውም፡፡ ሁለቱም ፆታዎች በእኩልነት ሊገለጹ የሚችሉ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡
- በየትኛውም አቅጣጫ ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ለማህበረሰቡ ሊኖረው የሚችለውን ሁለንተናዊ ፋይዳ ሊያሳይ በሚችል መልኩ መቅረብ አለባቸው፡፡
- በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሚቀርቡ ምንባቦች፣ መመሪያዎችና መልመጃዎች የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ተማሪዎችን ማንነት ዝቅ የሚያደርጉ ጥላቻን የሚያንጸባርቁ፣ ባህላቸውን የሚነቅፉ፣ በአንፃሩ ደግሞ የተወሰኑ ቡድኖችን የበላይነት በሚያንፀባርቅ መልኩ መቅረብ የለባቸውም፡፡

## 2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ከዚህ ጥናት ጋር በተያያዘ የተደረጉ ጥናቶች የተወሰኑ በአንደኛ ደረጃ በ7ኛና በ8ኛ ክፍልና በሁለተኛ ደረጃ በ9ኛና በ10ኛ ክፍል ላይ ጥናቶች ተደርገዋል፡፡ አጥኚው ከህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ጋር በተያያዘ በበፍቃዱ እንዳለ (2012) በጅማ ዩኒቨርሲቲ ባደረገው ጥናት በ7ኛና በ8ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ላይ የተሰራ ጥናት ማግኘት ቢችልም ሌሎች ጥናቶችን ግን ማግኘት አልቻለም፡፡ ነገር ግን በሁለተኛ ደረጃ በ9ኛና በ10ኛ ክፍል በመማሪያ መፃህፍት ላይ የተደረጉ ጥናቶችን አግኝቷል፡፡ የዚህ ጥናት ዓላማም የ7ኛና የ8ኛ ክፍል ለመማሪያ መፃህፍትነት የተዘጋጁት ከህብረ-ባህላዊነትና

ብዝሃነት አኳያ መፈተሽ በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታ የሃሳብ ዝምድና ያላቸውን ጥናቶች ለመቃኘት ሞክሯል፡፡ በዚህ ጥናት የተቃኙ ሁሉም ጥናቶች የሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ጽሁፎች ናቸው፡፡

አንበሳው ፈንታ (2009) "የብዝሃ-ባህላዊነት አቀራረብ ፍተሻ በሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ተተኳሪነት፡፡" በጅማ ዩኒቨርሲቲ የተሰራ ሲሆን ጥናቱ የሚያተኩረው የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መገለጫ ከሆኑት ባህል፣ ብሔሰረብ፣ ፆታ፣ ኃይማኖትና አካል ጉዳተኝነትን መሰፈርት በማድረግ በመማሪያ መፃህፍቱ ሊኖር የሚገባው አቀራረብ ላይ ጥናት አድርጓል፡፡ የጥናቱ ዓይነትም ቅይጥ የምርምር ዘዴ የተከተለ ሲሆን በጥናቱ የተገኘው ውጤትም እንደሚከተሉት ናቸው፡፡ እነሱም፡-

ከባህል አኳያ በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ ትኩረት የተደረገባቸው ግብዓቶች የባህል አድልኦ ያልታየባቸው በመሆኑ የብዝሃ-ባህላዊ አቀራረብ ችግር እንደሌለባቸው አስፍሯል፡፡ ከብሔረሰብ አኳያ በመማሪያ መፃህፍቱ ግብዓቶች ከባህል ጋር በተያያዘ እንደተነሳው የብሔረሰባዊ አድልኦ አልታየባቸውም፡፡ ይሁን እንጂ በግለ-ታሪኮችና በተፀውኦ ስሞች ላይ የብዝሃ-ባህላዊ አቀራረብ ችግር ተስተውሏል፡፡ ከግለ-ታሪኮች ጋር በተያያዘ 60 በመቶ የሚሆኑት ግለ-ታሪኮች የአንድ ብሔረሰብ(ኦሮሞ) ግለሰቦች ታሪክ ሲሆኑ ከተፀውኦ ስሞች ጋር በተያያዘ ደግሞ አብዛኞቹ(78.13 በመቶ) የአማራ(የአማርኛ ቋንቋ) ስሞች ናቸው፡፡ በመሆኑም እነኚህ ሁለት የቋንቋ ትምህርት ግብዓቶች ላይ የብዝሃ-ባህላዊ አቀራረብ ችግር እንዳለ ጥናቱ ጠቁሟል፡፡ ከፆታ አኳያ በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ ግለ-ታሪኮች፣ በተፀውዖ ስሞች፣ በተናጠል በቀረቡ ፆታ ለይ ግሶችና ዐረፍተ ነገሮች፣ በፈሊጦችና የተለያዩ የቋንቋ ትምህርት ግብዓቶችን ለመማሪያ መፃህፍቱ ባበረከቱት ጸሃፊያን ዘንድ የወንድ ፆታ የበላይነት በጉልህ ተንፀባርቆ መታየቱንና በአንፃራዊነት ምንባቦች፣ የስነ-ጽሁፍ ስራዎች፣፣ አጫጭር ጽሁፎች፣ መልመጃዎች፣ በተናጠል የቀረቡ ፆታ ለይ ስሞች፣ ትዕዛዞች(መመሪያዎች) እና ስዕላዊ መገለጫዎች ከፆታ አንፃር የተሻለ ብዝሃ-ባህላዊ አቀራረብ እንደታየባቸው አስፍሯል፡፡

ከኃይማኖት አኳያ የተገኘ ውጤትም ግለ-ታሪኮችና ስሞች ከኃይማኖት አንፃር ትኩረት የተደረገባቸው የመማሪያ መፃህፍቱ ግብዓቶች ሲሆኑ አንድን ኃይማኖት ከፍ ሌላውን ደግሞ ዝቅ የሚያደርጉ ይዘቶች እንዳልተስተዋሉና ነገር ግን በግለ-ታሪኮች 100 በመቶ

እና በተፀውዖ ስሞች 75 በመቶ የክርስትና ኃይማኖት የበላይነት በጉልህ ተንጸባርቆ ተስተውሏል፡፡ በመሆኑም በሁለቱም የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሃፍት ውስጥ በቀረቡ የቋንቋ ትምህርት ግብዓቶች የተወሰኑት ላይ ብዝሃ-ባህላዊ የአቀራረብ ችግር ባይስተዋልም በተወሰኑ ግብዓቶች ላይ ሃይማኖት ብዝሃ-ባህላዊ ትኩረት እንዳልተሰጠው አስፍሯል፡፡ ከአካል ጉዳተኝነት አኳያ የተገኘው ውጤትም እንደሚያሳየውም በሁለቱ የመማሪያ መፃህፍቱ አካል ጉዳተኝነትን የሚመለከቱ አሉታዊ ይዘት ያላቸው ግብዓቶችን አለማቅረቡ የሚደገፍ ቢሆንም ከህብረ-ባህላዊነት አንፃር ስነ-ልቦናቸውን ሊገነቡና በራስ መተማመንን ሊጨምሩ የሚችሉ የቋንቋ ግብዓቶችን መጠቀም የሚደገፍ ቢሆንም በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ ግን ምንም የተሰጠው ትኩረት አለመኖሩን አመልክቷል፡፡

ክፍሌ ዳመነ (2010) "የሰዋሰው ክፍለ ትምህርት ይዘት ከጾታ አንፃር ያላቸው ህብረ-ባህላዊ አቀራረብ ፍተሻ በሁለተኛ ደረጃ እና መሰናዶ ትምህርት ቤት ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህ ፍት ተተኳሪነት፡፡" በሚል የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ ነው፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ ዋና ዓላማ አድርጎ የተነሳው የመማሪያ መፃህፍቱ በሰዋሰው ክፍለ ትምህርት ይዘት ውስጥ በግብዓትነት የዋሉ ይዘቶች ከስርዓተ ፆታ አንፃር ያላቸው ህብረ ባህላዊ አቀራረብን ቃኝቷል፡፡ በፍተሻዉ ግብዓት ሆነው የቀረቡት ፆታ አመልካች ምእላዶች፣ ዐረፍተ ነገሮች፣ አጫጭር ጽሑፎችና መመሪያዎች ሲሆኑ ለዚህ ጥናት ቅይጥ(Mixed) የምርምር ዘዴን እንዲሁም በዋናነት ሰነድ ፍተሻን ተጠቅሟል፡፡ የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው የመማርያ መጽሃፍቱ የሰዋሰው ክፍለ ትምህርት ይዘት ውስጥ በግብዓትነት በዋሉ ፆታ የሚለዩ ምእላዶች፣ ቃላት፣ ሐረጋት፣ ዐረፍተ ነገሮችና አጫጭር ጽሑፎች ላይ የወንድ ፆታ የበላይነት ተንጸባርቋል፡፡ ፆታዊ እኩልነት ዓለም አቀፋዊ ይዘትና ተቀባይነት ያለው ቢሆንም ከሌሎች የብዝሃ ባህላዊ መገለጫዎች የተለየ ትኩረት እንዳልተሰጠው የጥናቱ ውጤት ይጠቁማል፡፡

ቤተልሔም ከበደ (2011) "የብዝሃ-ባህላዊነት ጭብጦች ፍተሻ በ9ኛና በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ተተኳሪነት፡፡" በጎንደር ዩኒቨርሲቲ የተሰራ ሲሆን ጥናቱ የሚያተኩረው የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መገለጫ ከሆኑት መካከል ፆታን፣ ኃይማኖትና አካል ጉዳተኝነትን መስፈርት በማድረግ በመማሪያ መፃህፍቱ ሊኖር

የሚገባውን ጭብጦች ላይ ጥናት አድርጓል፡፡ በጥናቱ የተገኘው ውጤትም እንደሚከተሉት ናቸው፡፡ እነሱም፡-

ከፆታ አኳያ በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ ግለ-ታሪኮች፣ በተፀውዖ ስሞች፣ በተናጠል በቀረቡ ፆታ ላይ ግሶችና ዐረፍተ ነገሮች፣ በፈሊጦችና የተለያዩ የቋንቋ ትምህርት ግብዓቶችን ለመማሪያ መፃህፍቱ ባበረከቱት ጸሃፊያን ዘንድ የወንድ ፆታ ጎልቶ መታየቱን አስፍሯል፡፡ ከኃይማኖት አኳያ የተገኘ ውጤትም ግለ-ታሪኮችና ስሞች ከኃይማኖት አንፃር ትኩረት የተደረገባቸው የመማሪያ መፃህፍቱ ግብዓቶች ሲሆኑ ከኃይማኖት አንፃር አንድን ኃይማኖት ከፍ ሌላውን ደግሞ ዝቅ የሚያደርጉ ይዘቶች እንዳልተስተዋሉና ነገር ግን በግለ-ታሪኮችና በተፀውዖ ስሞች የክርስትና ኃይማኖት በበላይነት ተንጸባርቆ እንደታየ ተጠቅሷል፡፡ ከአካል ጉዳተኝነት አኳያ የተገኘው ውጤትም በመማሪያ መፃህፍቱ ከህብረ-ባህላዊነት አንፃር ስነ-ልቦናቸውን ሊገነቡና በራስ መተማመንን ሊጨምሩ የሚችሉ የቋንቋ ግብዓቶችን መጠቀም የሚደገፍ ቢሆንም በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ ግን ምንም የተሰጠው ትኩረት አለመኖሩን ተጠቁሟል፡፡

ሰለሞን ፍስሐ (2011) "የባህል ብዙነት ግንዛቤ ማስጨበጫ ይዘት ፍተሻ በ9ኛና በ10ኛ ክፍል በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ላይ ጥናት አድርገዋል፡፡ ጥናቱ ትኩረት ያደረገባቸው ነጥቦች፡- የዓለም አቀፋዊ መብቶች ጽንሰ-ሃሳቦችን ከማስገንዘብ አንፃር ምንም ነገር ግንዛቤን ለማስጨበጥ የሚችል የቀረበ ነገር አለመኖሩን፣ ከዲሞክራሲያዊ አመለካከቶች እና እሴቶች አንፃር ሲሆን በዚህ ርዕስ ዙሪያ ምንም ዓይነት ይዘት የቀረበ ነገር እንደሌለ፣ የማህበራዊ ፍትህ መርሆዎችን ከማስገንዘብ አንፃር ሲሆን በዚህ ርዕስ ዙሪያ ምንም ዓይነት ይዘት እንዳልቀረበ፤ ባህላዊ ስብጥርን ከማስገንዘብ አንፃር ሲሆን በዚህ ርዕሰ-ጉዳይ ዙሪያ ተማሪዎች ለራሳቸው አዎንታዊ እይታ እንዲያዳብሩ የሚያደርጉ የማህበረሰቡን ታሪክና ባህል በማሳወቅ ረገድ በ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሃፍ ላይ የተወሰነ ማብራሪያዎች የቀረቡ ሲሆን በ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሃፍ ውስጥ ግን ምንም ዓይነት ይዘት እንሌለ፣ መዋቅራዊ እኩልነትን ከማስገንዘብ አንፃር ሲሆን ባህላዊ ስብጥር ባላቸው ቡድኖች መካከል በስልጣን ረገድ ምንም ዓይነት ይዘት እንዳልቀረበ፣ ማህበራዊ ችግሮችን ከማስገንዘብ አንፃር በ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሃፍ ውስጥ ምንም ዓይነት ይዘት የለም፡፡ ነገር ግን በ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሃፍ ውስጥ ማህበራዊ ችግር ከሆኑት የመደብና በስልጣን፣ በክብር፣ በሀብትና

በሹመት መመካት የሚኖረውን ውጤት በግጥም መልክ የቀረበ ሲሆን ዘረኝነትና፣ የቋንቋ ችግሮች፣ ኃይማኖታዊ አመለካከቶችና የመሳሰሉት ማህበራዊ ችግሮችን ለማስገንዘብ የቀረበ ይዘት እንደሌለና ከባህል ብዙ ትምህርት መነሻ አስተሳሰብ አንፃር ያለውን የይዘት ዝግጅት በተመለከተ ለተማሪዎች ማንኛውም ባህላዊ መገለጫዎች ከሌላኛው ጋር እኩል እንደሆነ ለማስገንዘብ በሁለቱም መማሪያ መፃህፍት የቀረበ የይዘት ዝግጅት የለም፡፡

በጥቅሉ በተደረገው ጥናት የተገኘው ውጤት የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ ባህለ ብዙነት ግንዛቤን ከማስጨበጥ አንፃር ያላቸው የይዘት ዝግጁነት ዝቅተኛ መሆኑ ነው፡፡

በፍቃዱ እንዳለ (2012) “በኦሮሚያ ክልል ለ7ኛና ለ8ኛ ክፍል የተዘጋጁት የአማርኛ መማሪያ መፃህፍት ህብረ-ባህላዊነትን በማስረፅ ረገድ ያላቸውን አስተዋጽዖ ፍተሻ በሚል ርዕስ የተሰራ ሲሆን ትኩረት ያደረገውም ከህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መገለጫ ከሆኑት መካከል በስምና በፆታ ስብጥር ላይ ያለውን አስተዋጽዖ መፈተሽ ሲሆን በጥናቱ የተገኘው ውጤትም እንደሚከተሉት ናቸው፡፡ እነሱም፡-

ከፆታ አንፃር በሁለቱም የክፍል ደረጃ የተገኘው አማካይ መረጃ እንደሚያስረዳው ወንድ እና ሴት ፆታን በሚለዩ የተጸውኦ ስሞች መካከል ያለው ልዩነት 23 በመቶ ያህል በመሆኑ ለሁለቱም ፆታዎች ተመጣጣኝ ሽፋን እንዳልተሰጠና ለወንድ ፆታ ያደላ አቀራረብ እንደሆነ ማወቅ እንደተቻለና በተለይ በ7ኛ ክፍል የተካተቱት የተጸውኦ ስሞች ከግማሽ በላይ በሆነ መጠን ለወንድ ፆታ ያደሉ እንደሆነ የጥናቱ ውጤት ያስረዳል፡፡ እንዲሁም ከስም አንፃር በ7ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የተካተቱት ተውላጠ ስሞች 10 በመቶ የወንድ ፆታ በ8ኛ ክፍል ደግሞ 20 በመቶ የሴት ፆታን የሚወክሉት ብልጫ እንዳላቸው በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ ለሁለቱም ፆታዎች ተመጣጣኝ መጠን ያላችውን ተውላጠ ስሞች በመጠቀም ረገድ በሁለቱም የክፍል ደረጃ በተዘጋጁት የቋንቋ መማሪያ መጽሀፎች ክፍተት ያለባችው ሲሆን በተለይ ለ8ኛ ክፍል በተዘጋጀው ደግሞ ከፍተኛ ችግር እንዳለ የጥናቱ ውጤት ያስረዳል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ቅኝት የተደረገባቸው የተዛማጅ ጥናቶች በመማሪያ መፃህፍት(ሰነድ ፍተሻ) ላይ ትኩረት በማድረግ የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መገለጫዎች በመማሪያ

መጽሃፍቱ የተሰጣቸውን ትኩረት የሚዳስሱ በመሆናቸው ከዚህ ጥናት ጋር ያመሳስላቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ በተደረገው ቅኝት የአራቱም የአንበሳው፣ የክፍሌ፣ የቤተልሄምና የሰለሞን ጥናቶች ትኩረት የሚያደርጉት በሃገር አቀፍ ደረጃ የተዘጋጁ መማሪያ መፃህፍት (በ9ኛና በ10ኛ ክፍል) ላይ ሲሆን ይህ ጥናት ከእነዚህ ይለያል፡፡ ነገር ግን በፍቃዱ እንዳለ (2012) "በኦሮሚያ ክልል ለ7ኛ እና ለ8ኛ ክፍል የተዘጋጁት የአማርኛ መማሪያ መጽሃፎች ህብረ-ባህላዊነትን በማስረፅ ረገድ ያላቸውን አስተዋጽዖ ፍተሻ በሚል ርዕስ በጅማ ዩኒቨርሲቲ የተሰራ ሲሆን ጥናቱ የሚያተኩረውም ለማስተማሪያነት ከቀረቡት ግብዓቶች በምንባቦችና በመልመጃዎች ውስጥ የሚገኙት የብሔር ስሞችና የፆታ አቀራረብ ምን ያህል ተገቢ ናቸው የሚል በመሆኑ አጥኚው ከባህልና ከኃይማኖት አንፃር የተደረገ ጥናት ባለማግኘቱ(አለመኖሩን ማረጋገጫ የለውም) የዚህ ጥናት ዓላማም በኦሮሚያ ክልል አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጁትን የ7ኛና የ8ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ተተኳሪ ያደረገ መሆኑና የመማሪያ መፃህፍቱ የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መገለጫ ከሆኑት መካከል ከባህል፣ ከኃይማኖትና ከፆታ አንፃር የቀረቡት የቋንቋ ማስተማሪያ ምንባቦች፣ መመሪያዎችና መልመጃዎች ያላቸውን ትኩረት በመፈተሽ ከባህልና ከኃይማኖት አኳያ ክፍተቱን ለመሙላት በመታሰቡ ነው፡፡

## ምዕራፍ ሶስት፤ የጥናቱ ዘዴ እና አካሄድ

በዚህ ምዕራፍ የጥናቱ ንድፍ፣ የናሙና አመራረጥ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴና የመረጃ አተናተን ዘዴ በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡

### 3.1. የጥናቱ ንድፍ

ጥናቱ በዋነኛነት ዓይነታዊ ሆኖ ገላጭ የምርምር ስልትን ተጠቅሟል፡፡ ስለሆነም ይህ ጥናት ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን የተከተለ ሲሆን መረጃውም ከሰነድ ፍተሻ የተገኘ ነው፡፡ ከሰነድ ፍተሻ የተገኘውን መረጃ በገላጭ ስታስቲካዊ ዘዴ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

### 3.2. የናሙና አመራረጥ

#### 3.2.1. የመማሪያ መፃህፍቱ እና የክፍል ደረጃ አመራረጥ

በሀገራችን ትምህርት ፖሊሲ መሰረት የመማሪያ መፃህፍቱ ከ 9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ ያሉት የሚታተሙት በሀገር አቀፍ ደረጃ ሲሆን ከ 1ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ያሉት የመማሪያ መፃህፍት የሚታተሙት ደግሞ በክልል ደረጃ ነው፡፡ በ2009 ዓ/ም ተሻሽለው በክልል ደረጃ ታትመው በስራ ላይ ያሉት አማርኛ እንደሁለተኛ ቋንቋ ማስተማሪያነት የተዘጋጁት የ7ኛና የ8ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት የቅርብ ጊዜ ዕትም ከመሆናቸው ጋር ተያይዞና በ9ኛና በ10ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ላይ በተደጋጋሚ ጥናት የተደረገ ሲሆን በእነዚህ በ7ኛና በ8ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ላይ የተደረገው ጥናት በቂ ባለመሆኑና የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ለ9ኛ ክፍል ትምህርት የሚዘጋጁ በመሆናቸው መፃህፍቱ ምን ያህል የተማሪዎችን ዳራ ያገናዘቡ እንደሆኑ ለመለየት ጥናት ለማድረግ ነው፡፡ ስለሆነም ጥናት የተደረገባቸው የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የክፍል ደረጃው እና መማሪያ መፃህፍቱ የተመረጡበት የናሙና ዘዴ በወሳኝ ንሞና(Non-probability Sampling) ዘዴ ስር በሚገኘው በዓላማ ተኮር ንሞና ዘዴ ነው፡፡ በናሙናነት የተመረጡባቸው ዋና ምክንያት መማሪያ መፃህፍቱ በክልል ደረጃ የተለያዩ ባህል፣ ኃይማኖት፣ ቋንቋ፣ ልማድ ወዘተ ላላቸው ተማሪዎች የተዘጋጁ በመሆናቸው፤ ከህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት አንፃር መጠናት እንዳለባቸው በመታመኑ እና መረጃዎች በቀላሉ ስለሚገኙ ነው፡፡

## 3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ለጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያነት የሚውለው መሳሪያ የሰነድ ፍተሻ ነው፡፡ ምክንያቱም መረጃው የሚሰበሰበው ከመማሪያ መፃህፍቱ ስለሆነ ነው፡፡

### 3.3.1. የሰነድ ፍተሻ

የጥናቱ የመረጃ ምንጭ (የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ) የሰነድ ፍተሻ ነው፡፡ በሰነዶቹ (በመማሪያ መፃህፍቱ) ውስጥ ቋንቋን ለማስተማር ታስበው የቀረቡ የቋንቋ ትምህርት ዓላማን ከማሳካት ጎን ለጎን ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን በምን መልኩ እንዳስተናገዱ በዋናነት ፈትሿል፡፡ በመሆኑም በ2009 ዓ/ም ተሻሽለው የታተሙና አሁን በስራ ላይ ያሉ የአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል (የ7ኛና የ8ኛ ክፍል) አማርኛ እንደሁለተኛ ቋንቋ ማስተማሪያነት የተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የቀረቡ ምንባቦች፣ መመሪያዎች እና መልመጃዎች የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ትምህርት በቋንቋ መማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ የተሰጣቸውን ትኩረት ፈትሿል፡፡ ፍተሻውም ለህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መኖር ምክንያት ከሆኑት (ከባህል፣ ከኃይማኖትና ከፆታ) አኳያ ተገቢነቱ ተገምግሞ የተገኘው መረጃም ተተንትኗል፡፡

## 3.4. የመረጃ አተናተን

የመረጃ አተናተኑ ከሰነድ ፍተሻ የሚሰበሰቡ ወይም የሚገኙ መረጃዎች ዓይነታዊ ስለሆኑ መረጃዎቹ በገለፃ እና በስታስቲካዊ ዘዴ ተተንትነዋል፡፡

### 3.4.1. ከሰነድ ፍተሻ የተገኙ መረጃዎች አተናተን

በ2009 ዓ/ም የታተሙ በ7ኛ እና በ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ማስተማሪያነት በተዘጋጁት መፃህፍት ውስጥ የቋንቋ ማስተማሪያ ምንባቦች፣ መመሪያዎችና መልመጃዎች ለተማሪዎች ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን ለማስገንዘብ መገለጫ ከሆኑት ከባህል፣ ከኃይማኖትና ከፆታ አኳያ የተሰጠውን ትኩረት በመመርኮዝ ተተንትነዋል፡፡ እንዲሁም ተገቢነታቸው በገለፃ ተተንትነዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት፤ የመረጃ ትንተና እና የውጤት ማብራሪያ

በዚህ ምዕራፍ ስር ያሉት መረጃዎች በ2009 ዓ.ም. በኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ አዘጋጅነት አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጁትን የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መፃህፍት ለህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት የሰጡትን ትኩረት መማሪያ መፃህፍቱን በመፈተሽ የተገኙ መረጃዎች የሚተነተኑበትና ውጤቱም የሚብራራበት ክፍል ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ከመማሪያ መፃህፍቱ አደረጃጀት አንስቶ የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መገለጫ ከሆኑት ከባህል፣ ከሃይማኖት እና ከፆታ አኳያ ለማረጋገጥ ትኩረት ያደረገባቸው ምንባቦች፣ መመሪያችና መልመጃዎችን በመፈተሽ የተገኙት መረጃዎች እንደሚከተለው ተተንትነዋል፡፡

## 4.1. የመረጃ ትንተና

### 4.1.1. የመማሪያ መፃህፍቱ አጠቃላይ አደረጃጀት

አጥኚው በመማሪያ መፃህፍቱ ላይ ይህን ጥናት ሲያደርግ ለማስተማሪያነት እያገለገሉ ያሉ ሲሆን በመማሪያ መፃህፍቱ የተገኙት መረጃዎች ለህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት የሰጡትን ትኩረት ትንታኔ ከመደረጉ በፊት የመማሪያ መፃህፍቱን አጠቃላይ ይዘት መመልከቱ ተገቢ ነው የሚል እምነት አለው፡፡ መማሪያ መፃህፍቱም በውስጣቸው የያዙትን ለማስተማሪያነት የቀረቡትን ይዘቶች ከዚህ ቀጥሎ በቀረበው ሰንጠረዥ በማቅረብ ማብራሪያውም ተከትሏል፡፡

ሰንጠረዥ 4.1 የመማሪያ መፃህፍቱ አጠቃላይ አደረጃጀት

| የክፍል ደረጃ | የገጽ ብዛት | የምዕራፍ ብዛት | የመልመጃዎች ብዛት | የክሂል አደረጃጀት | | | | ሰዋሰው |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ማዳመጥ | መናገር | ማንበብ | መፃፍ | |
| 7ኛ | 106 | 10 | 81 | 10 | 10 | 10 | 10 | -- |
| 8ኛ | 131 | 10 | 68 | 10 | 10 | 10 | 10 | 1 |
| ድምር | 237 | 20 | 149 | 20 | 20 | 20 | 20 | 1 |

ከዚህ ሰንጠረዥ የምንረዳው የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሃፍ 106 ና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሃፍ 131 ገፆች እንዳሉት የሚያሳይ ነው፡፡

በእነዚህ ሁለቱ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ያሉት የምዕራፎች ብዛት እኩል 10 መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡ የመፃህፍቶቹ በእኩል ምዕራፎች መከፈላቸው እና መዘጋጀቱ ለተማሪቹ የትምህርት አቀባበል እና ስለመፃህፍቱ የምዕራፍ ይዘት በቀላሉ እንዲረዱና ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያስችላል፡፡

የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሃፍ በአስሩም(10) ምዕራፎች ውስጥ 81 መልመጃዎችን የያዘ ሲሆን እነዚህም መልመጃዎች የተለያዩ 140 መመሪያዎችና 673 ጥያቄዎች ያሉት መሆኑ ተለይቷል፡፡

የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሃፍ በአስሩም(10) ምዕራፎች ውስጥ 68 መልመጃዎችን የያዘ ሲሆን እነዚህም መልመጃዎች የተለያዩ 234 መመሪያዎችና 885 ጥያቄዎች ያሉት መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡

የሁለቱንም መማሪያ መፃህፍት የማዳመጥ ክሂል አደረጃጀት ስንመለከት የማዳመጥ ክሂልን በሚመለከት በየምዕራፎቹ አንድ ይዘት በማቅረብ በአስሩም(10) ምዕራፎች 10 የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር የሚረዱ ይዘቶች በሁለቱም መማሪያ መፃህፍት ውስጥ እኩል ቀርቧል፡፡

የሁለቱንም መማሪያ መፃህፍት የመናገር ክሂል አደረጃጀት ስንመለከት የመናገር ክሂልን በሚመለከት በየምዕራፎቹ አንድ ይዘት በማቅረብ በአስሩም(10) ምዕራፎች 10 የመናገር ክሂልን ለማዳበር የሚረዱ ይዘቶች በሁለቱም መማሪያ መፃህፍት ውስጥ እኩል ቀርቧል፡፡

የሁለቱንም መማሪያ መፃህፍት የማን በብ ክሂል አደረጃጀት ስንመለከት የማንበብ ክሂልን በሚመለከት በየምዕራፎቹ አንድ ይዘት በማቅረብ በአስሩም(10) ምዕራፎች 10 የማንበብ ክሂልን ለማዳበር የሚረዱ ይዘቶች በሁለቱም መማሪያ መፃህፍት ውስጥ እኩል ቀርቧል፡፡

የሁለቱንም መማሪያ መፃህፍት የመፃፍ ክሂል አደረጃጀት ስንመለከት የመፃፍ ክሂልን በሚመለከት በየምዕራፎቹ አንድ ይዘት በማቅረብ በአስሩም(10) ምዕራፎች 10 የመፃፍ ክሂልን ለማዳበር የሚረዱ ይዘቶች በሁለቱም መማሪያ መፃህፍት ውስጥ እኩል ቀርቧል፡፡

ሰዋሰውን አስመልክቶ በ8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሃፍ ውስጥ የቀረበ ሲሆን በ7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሃፍ ውስጥ ግን አልቀረበም፡፡ ይህም ደግሞ ከተማሪዎቹ የክፍል ደረጃ ተገናዝቦ የተዘጋጀ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ እንዲሁም የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የሚሸጋገሩና የ1ኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና (ሚኒስትሪ) የሚወስዱ በመሆኑና የ9ኛ ክፍል የቋንቋ ትምህርት በሚማሩበት ወቅት ለትምህርቱ ይዘት (የሰዋሰው ይዘት) አዲስና እንግዳ እንዳይሆንባቸው የሚያግዝ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በእነዚህ በ7ኛና በ8ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የስነ ጽሁፍ ይዘት በምንም መልኩ ያልቀረበ መሆኑን አጥኚው ተረድቷል፡፡

### 4.1.2. ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን ትኩረት ያደረጉ ምንባቦች

በመማሪያ መፃህፍቱና በመምህሩ መምሪያ የተዘጋጁ ምንባቦች ለህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን ትኩረት ቢያደርጉ ጥሩ ይሆናል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ምክንያቱም በክፍል ውስጥ የሚማሩት ተማሪዎች የተለያዩ ዳራ ካላቸው ማህበረሰብ የመጡ ስለሆኑ ነው፡፡ ይህም ሲባል ምንባቦቹ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ትኩረት ማድረጋቸው ተማሪዎች ቋንቋን ለመማር ያላቸው ትኩረት ሊጨምር ይችላል፡፡ በመሆኑም የሚቀርቡት ምንባቦች ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን በተለያየ ርዕሰ ጉዳይ ታሳቢ ተደርጎ ሊቀርቡ ይገባል፡፡ በዚሁ መሰረት በተማሪው መማሪያ መጽሃፍ የማንበብ፣ በመምህሩ መምሪያ ላይ የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር የቀረቡትን ምንባቦች በመዳሰስ ለህብ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ትኩረት የተደረገባቸው ምንባቦችን በመውሰድ ትንተና ተሰጥቶባቸዋል፡፡

ከላይ በቀረበው መሰረት በሁለቱም መማሪያ መፃህፍት በተማሪው መማሪያ መጽሃፍና በመምህሩ መምሪያ በ7ኛና በ8ኛ ክፍል የቀረቡት ምንባቦች ለህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት የሰጡትን ትኩረት የሚያንጸባርቁ ምንባቦችን በመለየትና አሳማኝ የሆኑ ጽንሰ

ሃሳቦችን ለማረጋገጫነት በመጥቀስ እንደሚከተለው በሰንጠረዥ በማቅረብ ማብራሪያው ተከትሏል፡፡

ሰንጠረዥ 4.2. በ7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሃፍ ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን የሚያንጸባርቁ ምንባቦች ማሳያ

| የመጽሃፉ ምዕራፍ | የምዕራፉ ርዕስ | ገጽ | የምንባቡ ርዕስ | ገጽ | የተንጸባረቀው ጽንሰ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|---|
| 2 | ጓደኛን ማፍራት | 16 | ጓደኛን መምረጥ (የመምህሩ መምሪያ) | 11 | ጓደኝነት ማለት በብዙ ጉዳዮች ላይ መስማማት፣ መቻቻልና በሃሳብ መቀራረብ ማለት እንደሆነ ቀርቧል፡፡ |
| 3 | አካል ጉዳተኝነት | 27 | አካል ጉዳተኝነት | 29 | አስፈላጊውን ድጋፍ ከተደረገላቸው እንደማንኛውም ማህበረሰብ አባል መማር፣ መስራት የሚችሉና በማንኛውም ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ በእኩልነት መሳተፍ የሚችሉ በመሆናቸው ሰብዓዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መብቶች ሊከበርላቸው ይገባል፡፡ |
| | | | መስማት የተሳናቸው (የመምህሩ መምሪያ) | 20 | |
| 5 | የህፃናት መብት | 45 | የህፃናት መብት | 49 | የህፃናት መብቶች ደንጋጌ በባህል በቋንቋ፣ በፆታ፣ በዘር፣ በሃይማኖትና በአካል ጉዳት ሁኔታ ልዩነት ሳይደረግ ሁሉንም ህፃናት በእኩልነት የሚመለከት መሆኑ ተገልጿል፡፡ |
| 6 | የሀገር ፍቅር | 52 | የሀገር ፍቅር (የመምህሩ | 41 | ለሀገራችን እድገት ባለን እውቀት፣ ገንዘብና ጉልበት ሁሉ መረባረብ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | መምሪያ) | | አለብን፡፡ ከሃገራችን ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ዝግጁ ከሆንን ድህነትን ማስወገድ ከባድ እንደማይሆን ተጠቅሷል፡፡ |
| 7 | ጠቃሚ ባህል | 63 | ጠቃሚ ባህል | 66 | ጥሩ ጥሩ ባህሎቻችንን መንከባከብ፣ መጠበቅና ለመጪው ትውልድ ማስተላለፍ እንዳለብን እና የአርሲ ሴቶች የሲንቄ የማስታረቅ ስርዓት ግጭትን ለመፍታት ያለውን አስተዋጽዖ ያስረዳል፡፡ |

ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ ላይ ለማሳየት እንደተሞከረው በኦሮሚያ ክልል አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ ማስተማሪያነት የተዘጋጁት የ7ኛ ክፍል የተማሪው መማሪያ መጽሃፍና በመምህሩ መምሪያ የተዘጋጁት ምንባቦችን ለማሳየት እንደተሞከረው በተማሪው የማንበብ ክሂልን ለማዳበር የቀረቡ 16 በመምህሩ መምሪያ የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር የቀረቡ 12 ምንባቦች በጥቅሉ 28 ምንባቦች ቀርበዋል፡፡ ከእነዚህ መካከል በተማሪው መማሪያ መጽሃፍ ከቀረቡት 16 ምንባቦች ውስጥ 3 በመምህሩ መምሪያ ከቀረቡት 12 ምንባቦች ውስጥ 3 በድምሩ 6 ምንባቦች ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን የሚያንጸባርቁ ምንባቦች የቀረቡ ሲሆን የተንጸባረቁበትንም ጽንሰ ሃሳብ ተቀንጭቦ በሰንጠረዡ ላይ ቀርቧል፡፡ በዚሁ መሰረት ትንተናው እንደሚከተለው ነው፡፡

በዚሁ መሰረት በተማሪው መማሪያ መጽሃፍ ምዕራፍ 2 ገጽ 16 የምዕራፉም ሆነ የምንባቡም ርዕስ ጓደኛን ማፍራትና በመምህሩ መምሪያ ገጽ 11 የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር የቀረበ ምንባብ ጓደኛን መምረጥ በሚል ርዕስ ስር የቀረቡት ምንባቦች ጽንሰ ሃሳብ ጓደኝነት በተለያዩ ነገሮች ላይ በሃሳብ መግባባት፣ መቻቻልና በሃሳብ ተቀራርቦ በጋራ ለመስራትም ሆነ ለማደግ ጠቃሚ በመሆኑ የምናፈራው ጓደኛ በእኛ ማግኘትና መስራት የሚደሰት መሆን እንዳለበትና በመረዳዳትና በመተጋገዝ የሚያምንና የሚደሰት ነገር ግን በማንነትና ባለን ደረጃ የማይርቀን፣ ልዩነትና ማንነትን አምኖ የሚቀበል መሆን እንዳለበትና እኛም በተመሳሳይ ለጓደኞችን ማድረግና መሆን እንደሚገባን

ከቀረበው ምንባብ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይህም ለማህበረሰቡ ባህል እውቅና የሚሰጥ ሃሳብ ነው፡፡

በተማሪው መማሪያ መጽሃፍ ምዕራፍ 3 ገጽ 29 የምንባቡም ሆነ የምዕራፉ ርዕስ አካል ጉዳተኝነት የሚል ሲሆን በመምህሩ መምሪያ ገጽ 11 የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር የቀረበው ምንባብ መስማት የተሳናቸው በሚል ርዕስ የቀረበ ምንባብ በህብረተሰቡ ውስጥ ለአካል ጉዳተኝነት ያለው ግንዛቤ በምንባቡ ቀርቧል፡፡ ይህም ማህበረሰቡ ለአካል ጉዳተኝነት ያለው ግንዛቤ የተሳሳተና የዕርግማን ውጤት ነው በሚል ጎጂ የሆነ ባህላዊ ግንዛቤ እንደሚንጸባረቅ ለማስገንዘብና አካል ጉዳተኝነት ከጤና ችግርና ከመኪና አደጋ ሊከሰት እንደሚችል ሲያብራራ ነገር ግን በዚህ መልኩ ጉዳት የደረሰባቸውን ግለሰቦች እንደየጉዳት ዓይነታቸው ጋር በማህበረሰቡ ውስጥ ገብተው (ተቀላቅለው) መስራትና መማር እንደሚችሉ እንዲሁም ለሀገር እድገት የራሳቸውን አስተዋጽዖ ማበርከት የሚችሉ በመሆኑ ማግለል እንደሌለብን በመፃህፍቱ በበቂ ሁኔታ ተብራርቶ ቀርቧል፡፡ ይህም የማህበረሰቡ ባህል በመደጋገፍ እና በመረዳዳት ላይ የተመሰረተ መሆኑን የሚያሳይ ሃሳብ ነው፡፡

በተማሪው መማሪያ መጽሃፍ ምዕራፍ 5 ገጽ 49 የምንባቡም ሆነ የምዕራፉ ርዕስ የህፃናት መብት በሚል በቀረበው ምንባብ ስለ ህፃናት መብት በሚገባ የተገለጸና ህፃናትም እንደ አቅማቸው ምን ዓይነት ስራዎችን በመስራት ወላጆቻቸውን መርዳት እንዳለባቸውና መስራት የሌለባቸውንም ስራዎች በዝርዝር ተቀምጠዋል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ ህፃናቱ በምንም ዓይነት መልኩ በባህል፣ በቋንቋ፣ በፆታ፣ በሃይማኖትና በአካል ጉዳት ሁኔታ ልዩነት ሳይደረግባቸው በእኩልነት ልንጠብቃቸውና ልንደግፋቸው እንደሚገባ በምንባቡ ውስጥ ቀርቧል፡፡ ይህም የማህበረሰቡ ባህልና ኃይማኖት ህፃናትን ልንጠብቃቸውና ልንንከባከባቸው እንደሚገባ የሚያስተምርና የሚደገፍ በመሆኑ ይህንን የሚያሳይ ሃሳብ ነው፡፡

የማንበብ ክሂል በተማሪው መማሪያ መጽሃፍና የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር የሚረዳ በመምህሩ መምሪያ ምዕራፍ 6 ገጽ 41 የምዕራፉም ሆነ የምንባቡ ርዕስ የሀገር ፍቅር በሚል በመፃህፍቱ ውስጥ ለማስተማሪያነት ቀርቧል፡፡ የምንባቡም ሃሳብ ማንኛውም ሰው በጉልበቱ፣ በሙያው፣ በገንዘቡም ሆነ በሚችለው መንገድ ለሀገሩ ከቆመና የሀገሩን ጥሪ

ሰምቶ የአቅሙን ያህል አስተዋጽኦ ካደረገ ሀገራችን ማደግ እንደምትችልና አሁን ካለንበት ድህነት መውጣት ወይም ድህነትን ማስወገድ እንደሚቻል በሚገባ ተብራርቶ ይገኛል፡፡ ይህም የማህበረሰቡ ባህል ለሃገር ቅድሚያ መስጠት እንደሚገባ የሚያስረዳ በመሆኑ ለሃገር መቆም እውቅና የሚሰጥ ሃሳብ ነው፡፡

በተማሪው መማሪያ መጽሃፍ ምዕራፍ 7 ገጽ 66 የምንባቡም ሆነ የምዕራፉ ርዕስ ጠቃሚ ባህል እንዲሁም በመምህሩ መምሪያ በዚሁ ምዕራፍ ባህል በሚል ርዕስ ቀርቧል፡፡ በዚህ ርዕስ ስር የቀረበ ምንባብ በተማሪው መማሪያ መጽሃፍ ስለ አርሲ ሴቶች የማስታረቅ ባህል በሁለት ወገኖች መካከል ግጭት ሲፈጠር መሃል በመግባት ሁለቱንም ወገኖች እንዲያቆሙ የሚያደርጉበትና ማህበረሰቡም ይህንን አክብሮና ጠብቆ ሲጠቀምበት የነበረ ባህል እንደሆነና ይህንን ባህል ልንጠብቀው፣ ልንንከባከበውና ለቀጣይ ትውልድ ማስተላለፍ እንደሚገባ ተቀምጧል፡፡ በመምህሩ መምሪያ ውስጥ ባህል በሚለው ርዕስ ስር የቀረበው ምንባብ ደግሞ የተለያዩ ማህበረሰቦች የተለያየ ባህል እንዳላቸውና አንዱ የአንዱን ጠብቆና አክብሮ የኖረ እንደመሆኑ መጠን አሁንም አንዱ የሌላውን ጠብቆና አክብሮ ሊኖር እንደሚገባ በስፋት ተብራርቷል፡፡ ከዚህ የምንረዳው በአርሲ ኦሮሞ ማህበረሰብ ዘንድ ያለውን ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በመከተል ሰላም እንዲኖር ወይም እንዲሰፍን ማድረግ እንደሚቻል ያስረዳል፡፡

በአጠቃላይ በኦሮሚያ ክልል አዘጋጅነት አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋን ለማስተማር በግብዓትነት የቀረቡት ምንባቦች ይዘት ከባህልና ከኃይማኖት አኳያ ሊደገፉ ወይም ሊበረታቱ የሚገባቸው ጽንሰ ሃሳቦችን የያዙ በመሆኑ ለህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ትኩረት የሰጡ ናቸው ተብለው የታመኑባቸውን ከዚህ በላይ ማባራሪያ ተሰቶባቸዋል፡፡ በተሰጠውም ማብራሪያ የምንባቦቹ ጽንሰ ሃሳብ ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መገለጫ ከሆኑት ከባህልና ከኃይማኖት አንፃር ትኩረት ያደረጉ ሲሆን ሌሎቹም የተቀሩት ምንባቦች ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን ትኩረት ያደረጉ ቢሆን የተሻለ ሊሆን እንደሚገባ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ሰንጠረዥ፡- 4.3. በ8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሃፍ ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን የሚያንጸባርቁ ምንባቦች ማሳያ

| የመጽሃፉ ምዕራፍ | የምዕራፉ ርዕስ | ገጽ | የምንባቡ ርዕስ | ገጽ | የተንጸባረቀው ጽንሰ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የቋንቋ ጥቅም | 1 | ቋንቋና የቋንቋ አገልግሎት | 5 | ቋንቋ አጠቃላይ ስሜታችንና ፍላጎታችንን የምንገልጽበት መሳሪያ እንደሆነና ማንነት ከሚገለጽባቸው መንገዶች አንዱ መሆኑን ያሳየናል፡፡ እንዲሁም የሰው ልጅ በመናገሩና መግባባት በመቻሉ ከሌሎች እንስሳት የሚለይበት መሆኑን ያሳየ ነው፡፡ |
| 2 | መከባበር | 16 | መከባበር | 20 | ማህበረሰቡ መከባበርና በመቻቻል ያለውን የተፈጥሮ ሀብት በጋራ የመጠቀምና ለግጭት መንስኤ በሚሆኑ ነገሮች ላይ የጋራ መግባባት እንዲኖር የመፍትሄ ሃሳብ ላይ በመመካከርና በመወያየት የጋራ ግንዛቤ እንዲፈጠር እንደሚያግዝ ያሳየናል፡፡ |
| | | | የቋንቋዎች እኩልነት (የመምህሩ መምሪያ) | 15 | የተለያዩ ህዝቦች በመከባበር አብረው ቢኖሩ ቋንቋዎቻቸውንም እኩል የማሳደግ እድል እንደሚያገኙና የአንዱ ቋንቋ ለሌላው ቋንቋ እድገት ያለው አስተዋጽዖ ከፍተኛና ወሳኝ መሆኑ ያስቀምጣል፡፡ |
| 3 | ኤች አይቪ/ኤድ | 27 | ኤች አይቪ/ኤድ | 32 | በበሽታው የተያዙ ሰዎችን ማግለሉ ተገቢ እንዳልሆነና በመደገፍና |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ስ | | ስ | | በመርዳት ልናግዛቸው እንደሚገባ ተብራርቷል፡፡ |
| | | | ሃላፊነትን መወጣት (የመምህሩ መምሪያ) | 22 | ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ያለባቸውን ሰዎች አስፈላጊውን ፍቅርና እንክብካቤ በማድረግ መድልዎ እንዳይደረግባቸው የበኩላችንን ድርሻ ልንወጣ እንደሚገባ ተብራርቷል፡፡ |
| 5 | ሴቶችን ማብቃት | 51 | ሴቶችን ማብቃት | 60 | ሴቶችን ብቁ ለማድረግ የፆታ ግንዛቤን ከፍ በማድረግ ህብረተሰቡ የፆታ እኩልነትን በሚመለከት አስፈላጊውን የአመለካከት ለውጥ እንዲያመጣ ጥረት መደረግ እንዳለበት ያስገነዝባል፡፡ |
| 9 | ባህል | 102 | ምንባብ (የገዳ ስርዓት) | 108 | በገዳ ስርዓት እንደ ሽምግልና፣ ሲንቄ እርቅና የሲንቄ ሃይል የሚሉትን በጥቂቱ ግንዛቤ ለማጨበጥ በሚችል መልኩ ተዘርዝሯል፡፡ |

ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ ላይ ለማሳየት እንደተሞከረው በኦሮሚያ ክልል አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ ማስተማሪያነት የተዘጋጁት የ8ኛ ክፍል የተማሪው መማሪያ መጽሃፍ የማንበብ ክሂልን በመምህሩ መምሪያ የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር የተዘጋጁት ምንባቦችን ለማሳየት እንደተሞከረው በተማሪው መማሪያ መጽሃፍ 16 ምንባቦች በመምህሩ መምሪያ 11 ምንባቦች በጥቅሉ 27 ምንባቦች ቀርበዋል፡፡ ከእነዚህ መካከል በተማሪው መማሪያ መጽሃፍ ከቀረቡት 16 ምንባቦች ውስጥ 5 በመምህሩ መምሪያ ከቀረቡት 11 ምንባቦች ውስጥ 2 በድምሩ 7 ምንባቦች ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን የሚያንጸባርቁ ምንባቦች የቀረቡ ሲሆን የተንጸባረቁበትንም ጽንሰ ሃሳብ ተቀንጭቦ በሰንጠረዡ ላይ በቀረበው መሰረት ትንተና ተሰጥቶበታል፡፡

በዚሁ መሰረት በተማሪው መማሪያ መጽሃፍ ምዕራፍ 1 ገጽ 5 ላይ ቋንቋና የቋንቋ አገልግሎት በሚል ርዕስ የቀረበ ምንባብ ሲሆን የቀረበውም ጽንሰ ሃሳብ አጠቃላይ ስሜታችንንና ፍላጎታችንን የምንገልጽበት መሳሪያ መሆኑ፤ እንዲሁም የማንነት መገለጫ እንደሆነና የመግባቢያ መሳሪያ መሆኑ በስፋት ተብራርቷል፡፡ ይህም በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን ብዝሃነት የሚያሳይ ሃሳብ ነው፡፡

በዚሁ መሰረት በተማሪው መማሪያ መጽሃፍ ምዕራፍ 2 ገጽ 20 ላይ የምዕራፉም ሆነ የምንባቡ ርዕስ መከባበር በሚል የቀረበ ሲሆን በዚህ ምንባብ ርዕስ ስለመከባበር ዘርዘር ያለ ሃሳብ ተቀምጧል፡፡ ቅድሚያ እኛ የሌላውን ስናከብር ሌላው ደግሞ የእኛንም ሊያከብር እንደሚችልና ተከባብረን በጋራ የምንኖር ከሆነ ተፈጥሮ የለገሰችንን ሀብት በጋራ መጠቀም እንደምንችል እንዲሁም ለግጭት መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮች ላይ መመካከር ጠቃሚ እንደሆነ ግንዛቤ እንዲኖር በስፋት ተዘርዝሯል፡፡ እንዲሁም በ8ኛ ክፍል በመምህሩ መምሪያ ውስጥ የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር እንዲረዳ በዚሁ በምዕራፍ 2 የምዕራፉ ርዕስ መከባበር ሆኖ የምንባቡ ርዕስ የቋንቋዎች እኩልነት በሚል ገጽ 15 ላይ ቀርቧል፡፡ የዚህ ምንባብ ጽንሰ ሃሳብ የተለያየ ቋንቋ የሚናገሩ ብሔር ብሔረሰቦች በመከባበር አብሮ በመኖራቸው ቋንቋዎች እኩል የማደግ እድል እንደሚኖራቸውና ለመግባቢያነት የምንገለገልባቸው መሳሪያዎች ስለሆኑ በቋንቋ መጠቀም የአንዱ ቋንቋ ለሌላው ቋንቋ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽዖ እንዳለው በሚገባ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ ይህም ሃሳብ ከባህልና ከኃይማኖት አኳያ ሊደገፉ ወይም ሊበረታቱ የሚገባቸው ጽንሰ ሃሳቦችን የያዙ ናቸው፡፡

በተማሪው መማሪያ መጽሃፍ ምዕራፍ 3 ገጽ 32 ላይ የምዕራፉም ሆነ የምንባቡ ርዕስ ኤች አይቪ/ኤድስ በሚል ቀርቧል፡፡ የምንባቡም ጽንሰ ሃሳብ በበሽታው የተያዙ ሰዎችን ማግለል አግባብ እንዳልሆነና እነዚህ ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ያለባቸው ሰዎችን በመደገፍና በማበረታታት ልናግዛቸው እንደሚገባ በስፋት ተዘርዝሯል፡፡ እንዲሁም በመምህሩ መምሪያ ውስጥ በዚሁ ምዕራፍ 3 ገጽ 22 ላይ ሀላፊነትን መወጣት በሚል ርዕስ ቀርቧል፡፡ የዚህ ምንባብ ጽንሰ ሃሳብ በኤች አይቪ/ኤድስ የተጠቁ (ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ያለባቸውን) ግለሰቦች አስፈላጊውን ፍቅርና እንክብካቤ ማድረግና መድልዖ ማድረግ እንደሌለብን መገለልና መድልዖ እንዳይደረግባቸው የበኩላችንን ድርሻ በመወጣት ድጋፍ ልናደርግላቸው እንደሚገባ በስፋት ተገልጿል፡፡ ይህም ሃሳብ

ከባህልና ከኃይማኖት አኳያ ሊደገፉ ወይም ሊበረታቱ የሚገባቸው ጽንሰ ሃሳቦችን የያዙ ናቸው፡፡

በተማሪው መማሪያ መጽሃፍ በምዕራፍ 5 ገጽ 60 ላይና በመምህሩ መምሪያ የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር የሚረዳ ምንባብ ገጽ 37 ላይ ሴቶችን ማብቃት በሚል ርዕስ ምንባብ ቀርቧል፡፡ የዚህ ምንባብ ጽንሰ ሃሳብም ሴቶችን ብቁ ለማድረግ ማህበረሰቡ ስለ ፆታ ያለውን ግንዛቤ ከፍ ማድረግና ሴቶችን ማስተማር ወይም ማብቃት ቤተሰብን ማብቃት ወይም ማስተማር እንደሆነና የሴቶች ተሳትፎ አስፈላጊ እንደሆነ ማህበረሰቡ ግንዛቤ እንዲኖረው ማድረግ እንደሚገባ ተዘርዝሮ ቀርቧል፡፡ ይህም ሃሳብ ከባህልና ከኃይማኖት አኳያ ሊደገፉ ወይም ሊበረታቱ የሚገባቸው ጽንሰ ሃሳቦችን የያዙ ናቸው፡፡

በተማሪው መማሪያ መጽሃፍ በምዕራፍ 9 ገጽ 108 ምንባብ በማለት ስለ ገዳ ስርዓት እንደ ሽምግልና በአካባቢው አዛውንቶች አማካይነት በባልና በሚስት ወይም በሁለት ሰዎች መካከል የተፈጠሩ ግጭቶች የሚፈቱበት፣ ሲንቄ እርቅ ከሴቶች መብትና ስልጣን ጋር ከፍተኛ የሆነ ትስስር እንዳለውና የሴቶችን መብት በማስከበር ረገድ ትልቅ ቦታ ያለውና ሲንቄ ሃይል ደግሞ ከፍተኛ ግጭት ተፈጥሮ ጦርነት ቢጀመር ሴቶች ተሰባስበው ሲንቄ ይዘው እልል እያሉ መሐል ቢገቡ ጦርነቱ ወዲያው እንደሚቆም በበቂ ሁኔታ ግንዛቤ ማስጨበጥ በሚችል መልኩ ቀርቧል፡፡ በመምህሩ መምሪያ የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር የሚረዳ በዚሁ ምዕራፍ ገጽ 69 ላይ የምዕራፉም ሆነ የምንባቡ ርዕስ ባህል በሚል ቀርቧል፡፡ በዚሁ ምንባብ ውስጥ ባህል በአንድ ሃገር ውስጥ ያለውን ሕዝብ ወይም ብሔር ከሌላው ለይቶ ለመግለጽም ሆነ የተለያዩ ብሔሮች የአንድ ሃገር ዜጋ መሆናቸው ለመረዳትና ባህሎች ተጣጥመው ተደጋግፈው እንዲበለጽጉ የየራሳቸው ባህል ያላቸው ብሔሮች ተፈቃቅረው፣ ተከባብረውና ተቻችለው መኖራቸው ወሳኝ መሆኑ ተዘርዝሮ ቀርቧል፡፡ ይህም ሃሳብ ከባህል አኳያ ሊደገፉ ወይም ሊበረታቱ የሚገባቸው ጽንሰ ሃሳቦችን የያዙ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ በኦሮሚያ ክልል አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋን ለማስተማር የተዘጋጁት የ8ኛ ክፍል በተማሪው መማሪያና በመምህሩ መምሪያ መጽሃፍ ከቀረቡት ምንባቦች ከባህልና ከኃይማኖት አኳያ ሊደገፉ ወይም ሊበረታቱ የሚገባቸው ጽንሰ ሃሳቦችን የያዙ በመሆኑ ለህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት

ትኩረት የተሰጠባቸው ምንባቦች ናቸው ተብለው የታመነባቸውን በምንባቦች ውስጥ የተንጸባረቁትን ጽንሰ ሃሳቦች በቅንጫቢ መልኩ የተገለጹትን ማብራራያ የተሰጠባቸው ሲሆን ሌሎች ቀሪ ምንባቦችም በዚሁ መልኩ ቢዘጋጁ ጥሩ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡

### 4.1.3. የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ጽንሰ ሃሳብ ያላቸው ምንባቦች ትንተና

የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ጽንሰ ሃሳብ አላቸው ተብሎ የታመነባቸውን ምንባቦች ከላይ የ7ኛ ክፍል በሰንጠረዥ 4.3 እና የ8ኛ ክፍል በሰንጠረዥ 4.4. የተጠቀሱትን ከሰነድ ፍተሻ የተገኙትን መረጃዎች በማጠቃለል በሰንጠረዥ መልክ በማቅረብ በአሃዝና በገለፃ መተንተን የዚህ ጥናት ስልት ነው፡፡ እንደዚሁም በ7ኛና በ8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሃፎች ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን የዳሰሱ ወይም ጽንሰ ሃሳቡን የሚያንጸባርቁ ምንባቦች ሲሆን በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ ያላቸውን ሽፋን የሚገለጽበት ነው፡፡ የምንባቦቹ ሽፋን ከመገለጹ በፊት በተማሪው መማሪያ መጽሃፍና በመምህሩ መምሪያ በ7ኛና በ8ኛ ክፍል ያሉትን ምንባቦች በሙሉ ብዛታቸው ተመዝግቦ ቀርቧል፡፡

ከዚህም ሰነድ ፍተሻ የተገኙትን ምንባቦች ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ጽንሰ ሃሳብ የተካተቱባቸው ናቸው ብሎ አጥኚው ያመነባቸው ተለይተው በአሃዝ ተገልጸዋል፡፡ እነዚህ የተለያዩ ምንባቦችም ከጠቅላላ ምንባብ አንፃር ያላቸውን ድርሻ በመቶኛ ተሰልቶ ተገልጿል፡፡ እንደዚሁም ካሉት ጠቅላላ ምንባቦች ውስጥ የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ጽንሰ ሃሳብ ያልተካተተባቸው ተለይተው በአሃዝ ተገልጸዋል፡፡ እነዚህ የተለያዩ ምንባቦችም ከጠቅላላ ምንባብ አንፃር ያላቸውን ድርሻ በመቶኛ ተሰልቶ ተገልጿል፡፡ በተገለጸው መሰረት የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ጽንሰ ሃሳብ የተካተተባቸውን እና ያልተካተተባቸው ምንባቦችን የማወዳደር ስሌት የተሰራ በተማሪው መማሪያ መጽሃፍና በመምህሩ መምሪያ ከቀረቡት ጠቅላላ ምንባቦች አንፃር እንጂ የተማሪው መማሪያ መጽሃፍና በመምህሩ መምሪያ የቀረቡትን ምንባቦች በተናጠል በማስላት አይደለም፡፡ የምንባቦቹን መጠን በተማሪው መማሪያ መጽሃፍና በመምህሩ መምሪያ የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር የቀረቡትን ምንባቦች በተናጠል ለማየት የተሞከረ ቢሆንም የመረጃ ትንተና ሲደረግ ግን በድምር እንጂ በተናጠል ትንተና ለመስጠት አልተፈለገም፡፡ በመሆኑም የተገኙ መረጃዎችን ከተማሪው መማሪያ መጽሃፍም ሆነ ከመምህሩ መምሪያ

የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር የቀረቡትን በጣምራ በተገኘ ውጤት መሰረት መተንተኑ ተመራጭ ሆኖ በመገኘቱ በጣምራ ተተንትኗል፡፡ በዚሁ መሰረት በቀጣዩ ሰንጠረዥ በቁጥርና በመቶኛ ተሰልተው የቀረቡ ሲሆን ትንተና ተሰጥቶባቸዋል፡፡

ሰንጠረዥ፡- 4.4 የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ጽንሰ ሃሳብ የተንጸባረቀባቸውና ያልተንጸባረቀባቸው ምንባቦች ማሳያ

| የክፍል ደረጃ | የምዕራፍ ብዛት | የምንባቦች ብዛት | | | ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን ያንጸባረቁ | | ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን ያላንጸባረቁ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በተማሪው መጽሃፍ | በመምህሩ መምሪያ | ድምር | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 7ኛ | 10 | 16 | 12 | 28 | 6 | 21.43 | 22 | 78.57 |
| 8ኛ | 10 | 16 | 11 | 27 | 7 | 25.93 | 20 | 74.07 |
| ድምር | 20 | 32 | 23 | 55 | 13 | 23.64 | 42 | 76.36 |

ከላይ በሰንጠረዡ የቀረበውን መረጃ ስንመለከት በ7ኛ ና በ8ኛ ክፍል በተማሪው መማሪያ መጽሃፍ የቀረቡት ምንባቦች እኩል መጠን ያላቸው መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡ እነዚህ አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የቀረቡት የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መፃህፍት በጠቅላላ የቀረቡት ምንባቦች በ7ኛ ክፍል 28 በ8ኛ ክፍል 27 በድምሩ 55 ምንባቦች ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ በ7ኛ ክፍል 6 በ8ኛ ክፍል 7 በድምሩ 13 ምንባቦች ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን የሚያንጸባርቁ ናቸው ተብሎ የታመነባቸው ሲሆን ከጠቅላላ ምንባቦች ውስጥ 13(23.64 በመቶ) ትኩረት የተጠሰባቸው ሲሆን 42(76.36 በመቶ) የሚሆኑት ደግሞ ትኩረት ያልተሰጠባቸው መሆኑን ለመረዳት በተቻለው መሰረት በምንባቦች ዝግጅት ወቅት ለህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት የተሰጠ ትኩረት አነስተኛ መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ በ7ኛና በ8ኛ ክፍል ለማስተማሪያነት ከተዘጋጁት መፃህፍት ውስጥ ከሰነድ ፍተሻ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው ለህብረ-ባህላነትና ብዝሃነት ትኩረት የሰጡትን

ምንባቦች በየክፍል ደረጃ በተናጠል የቀረቡትን በጣምራ ስናየው ለተማሪዎቹ የሚያስተላልፉት መልዕክት የመከባበር፣ የመደጋገፍ፣ በጋራ የመጠቀምና የመረዳዳት ባህልን ሊያጎለብቱ የሚችሉ ናቸው፡፡ እነዚህ ምንባቦችን መሰረት በማድረግ የተዘጋጁ መልመጃዎችም የምንባቡን ጽንሰ ሃሳብ ሊያዳብሩ በሚችል መልኩ ተዘጋጅተው የቀረቡ ናቸው፡፡

የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለማሳካት ያግዛሉ ተብለው የተዘጋጁ ምንባቦች፣ መመሪያዎችና መልመጃዎች ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነታቸው ምን ያህል ትኩረት እንደተሰጠው ተፈትሾ ቀርቧል፡፡ ስለሆነም ለዚህ ጥናት ዓላማ መሳካት በታሰበው መሰረት ለመረጃ መሰብሰቢያነት በዋለው ስልት ትርጉም ሊሰጡ በሚችል መልኩ ለዚሁ በተዘጋጁት መሪ ጥያቄዎች መሰረት መረጃዎቹ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ እነዚህ መረጃዎች የመማሪያ መፃህፍቱ አቀራረብ ለህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት የሰጡትን ትኩረት ተፈትሸው የተሰበሰቡ ሲሆን በሰንጠረዥ ተደርገው በአሃዝ የቀረቡና እንደ መረጃዎቹ ሁኔታ ስታትስቲካዊ በሆነ መንገድ በገለፃ ተተንትነዋል፡፡ ስለሆነም በ7ኛና በ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት አዘገጃጀት ለህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት የሰጡትን ትኩረት በተመለከተ የተገኙትን መረጃዎች ይህ ጥናት ትኩረት ካደረገባቸው መገለጫዎች መካከል ከባህል፣ ከሃይማኖትና ከፆታ አንፃር ያላቸውን ሽፋን የመፃህፍቱን በመፈተሽ ትንታኔ ተደርጎባቸዋል፡፡

በዚሁ መሰረት ትንተና የተደረገውም በመማሪያ መፃህፍቱ የአማርኛ ቋንቋ ክሂልን ሊያዳብሩ ይችላሉ ተብለው በግብዓትነት ከቀረቡት ምንባቦች፣ መመሪያዎችና መልመጃዎች ለህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መገለጫ ሊሆኑ የቻሉትን ለይቶ በመሰብሰብ የተጠቀሱት ብቻ ሲሆን መገለጫ ከሆኑት ጋር ግንኙነት የሌላቸው ላይ ትንተና አልተደረገም፡፡ ስለሆነም እነዚህ የተመረጡ የመረጃ ምንጮች ሲቀርቡ ከባህል፣ ከሃይማኖትና ከፆታ አንፃር የሰጡትን ትኩረት ለመፈተሽ ከቀረቡት መሪ ጥያቄዎች አንፃር ትንታኔ ተደርጓል፡፡

በዚሁ መሰረት የዚህ ጥናት መሪ ጥያቄዎች

1. በመማሪያ መፃህፍቱ የቀረቡት ምንባቦች፣ መመሪያዎችና መልመጃዎች ለተማሪዎቹ ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ከማስገንዘብ አንፃር ለባህል የተሰጠው ትኩረት ምን ያህል ነው?
2. በመማሪያ መፃህፍቱ የቀረቡት ምንባቦች፣ መመሪያዎችና መልመጃዎች ለተማሪዎቹ ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ከማስገንዘብ አንፃር ለኃይማኖት የተሰጠው ትኩረት ምን ያህል ነው?
3. በመማሪያ መፃህፍቱ የቀረቡት ምንባቦች፣ መመሪያዎችና መልመጃዎች ለተማሪዎቹ ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ከማስገንዘብ አንፃር ለፆታ የተሰጠው ትኩረት ምን ያህል ነው?

የሚሉ ጥያቄዎች ነበሩ፡፡ እነዚህን ጥያቄዎች ይመልሳሉ ተብለው የታሰቡትን ምንባቦች፣ መመሪያዎችና መልመጃዎችን ፍተሻ ተደርጎ ከተሰበሰበ በኋላ በተገኘው መረጃ ላይ ትንተና ተደርጓል፡፡ አስቀድመን ወደ መረጃ ትንተና ከመግባታችን በፊት በጥናቱ ትኩረት የተደረገባቸው የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መገለጫ የሆኑትን ከመማሪያ መፃህፍቱ በግብዓትነት የቀረቡትን በመለየት የሚኖራቸው ግንኙነት በሚከተለው መልኩ በሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ፡- 4.5 የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መገለጫዎችና የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ግብዓት ከሆኑት ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት ማሳያ

| ተ.ቁ. | ጥናቱ ያተኮረባቸው መገለጫዎች | መገለጫዎቹ ትኩረት ያደረጉባቸው ግብዓቶች |
|---|---|---|
| 1 | ባህል | - ምንባቦች<br>- መመሪያዎች<br>- መልመጃዎች |
| 2 | ሃይማኖት | - ግለ-ታሪኮች<br>- ስሞች<br>- ምሳሌያዊ አነጋገሮች |
| 3 | ፆታ | - ስሞች<br>- ግሶች<br>- ሀረጎች<br>- አረፍተ ነገሮች<br>- ምንባቦች (ግለ-ታሪኮች የምንባቦቹ ባለቤት) |

| | | - መመሪያዎች |
|---|---|---|

በሰንጠረዡ ላይ የቀረቡት መረጃዎች በምዕራፍ 3 ላይ በመረጃ ምንጭነት ከተጠቀሱት ሰነድ ፍተሻ ወይም በ7ኛና በ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጁት መፃህፍት ውስጥ የአማርኛ ቋንቋን ለማዳበር ይረዳሉ ተብለው በግብዓትነት ከቀረቡት ምንባቦች፣ መመሪያዎችና መልመጃዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች ከህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መገለጫ ከሆኑት አንፃር ከዚህ በታች እንደሚከተሉት ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

## 4.1.4. ከባህል አኳያ

ባህል ስንል የአንድ ማህበረሰብ መገለጫ ከሆኑት ውስጥ አንዱና ዋነኛው ነው፡፡ ባህል ከአባቶች የሚወረስ ቅርስ በመሆኑ በጎ የሆነውን የባህል ቅርስ ጠብቆ ለመጪው ትውልድ የማስተላለፍ ሃላፊነትና ግዴታም ነው፡፡ በመማሪያ መጽሃፎቹ የቀረቡት የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ግብዓት ከሆኑት የምንባቦች፣ የመመሪያዎችና የመልመጃዎች አቀራረብ ባህላዊ ይዘታቸው ምን እንደሚመስልና ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን በጠበቀ መልኩ መቅረባቸውን በመፈተሽ ትንተና ተደርጓል፡፡

### 4.1.4.1. ምንባቦች

በእነዚህ በ7ኛ እና በ8ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የቀረቡትን ምንባቦች ባህል ነክ የሆነ ጽንሰ ሃሳብ ያላቸው ወይም የዳሰሱና ባህልን ያልጠበቁትን ብቻ ትኩረት በመስጠት በመማሪያ መጽሃፍቱ ውስጥ ያሉት ምንባቦች ተፈትሸው የተሰበሰቡት መረጃዎች በአሃዝ መልክ በሰንጠረዥ ቀርበው ትንታኔ ተደርጎባቸዋል፡፡ ይህም ሲባል ባህላዊ ይዘት ኖሯቸው ነገር ግን ምንባቦች፣ መመሪያዎችና መልመጃዎችን በመፈተሽ ባህልን ያልጠበቁትን ለይቶ በማውጣት ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ በአሃዝ መልክ የቀረቡት መረጃዎች ጠቅላላ ከቀረቡ ምንባቦች ውስጥ በማውጣት በመቶኛ በማስላት ያለውን ሽፋን ማየት ነው፡፡ ይህም እነዚህ የመረጃ ምንጭ የሆኑትን ምንባቦች፣ መመሪያዎችና መልመጃዎች ላይ በመመርኮዝ ያላቸውን ሽፋን በተናጠል ገልጿል፡፡ ለዚህም ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ በማቅረብ ትንተናው ቀጥሎ ተደርጓል፡፡

ሰንጠረዥ፡- 4.6 በ7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሃፍ ባህልን ያልጠበቁ(ማህበረሰቡ ብዙም የማይደግፋቸው) ሃሳብ ያላቸው ምንባብ ማሳያ

| ምዕራፍ | የምዕራፉ ርዕስ | ገጽ | የምንባቡ ርዕስ | ገጽ | በምንባቡ የተንጸባረቀው ጽንሰ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|---|
| 2 | ጓደኛን ማፍራት | 16 | የአንበሳ፣ የነብር፣ የጅብና የአህያ ጓደኝነት | 20 | በኑሮም ሆነ በባህሪ የማይመጣጠኑ ጓደኝነት መመስረት ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ እንደሚያመዝንና በምንም መልኩ ሊገናኙ የማይችሉ (የማይሆን ጓደኝነት መመስረት) መጨረሻው ውድቀት (ጉዳት) መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ |
| | | | የዝንጀሮና የአይጥ ጓደኝነት (ርዕስ የሌለው) | 24 | በጋራ ሰርተው ለመጠቀም ተስማምተው ሳለ አንደኛው ከኋላ በመሆን አንደኛውን ሲጎዳ የሚያሳይ ነው፡፡ (መካካድን አመልካች ታሪክ) |
| 6 | የሃገር ፍቅር | 52 | የአንበሳና የጅብ ጓደኝነት | 58 | ያለ እኩያ መዋል (ከማይመስል ጋር መዋል) አግባብ እንዳልሆነ ያመለክታል፡፡ |
| 9 | ሱሰኝነት | 84 | ሱሰኝነት | 87 | ሱስ አምጪ ነገሮች በየዕለቱ በብዛት በተወሰዱ መጠን የአካል ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ አላስፈላጊነቱ ላይ የተገለጸ ነገር የለም፡፡ |
| | | | ጫት የመቃም ሱስ | 65 | ጫት መቃም ላልተፈለገ ድርጊት ሊዳርግ እንደሚችልና ከቃሙ በኋላ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ነገሮችን ለማሳየት ሞክሯል፡፡ |

ከላይ በሰንጠረዡ ላይ ለማየት እንደተሞከረው የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሃፍ ከቀረቡት 10 ምዕራፎች ውስጥ 3ቱ በጠቅላላ ከቀረቡት 28 ምንባቦች ውስጥ 5ቱ የኦሮሞ ባህል መረዳዳት፣ መተጋገዝና አብሮነትን ያቀፈ ሲሆን የቀረቡት ግን ባህሉን ያልጠበቁ መሆናቸውን በሰንጠረዡ ላይ የተንጸባረቁበትን ጽንሰ ሃሳብ በማየት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በመማሪያ መጽሃፉ በምዕራፍ 2 ገጽ 20 የምዕራፉ ርዕስ ጓደኛን ማፍራት የሚል ሲሆን የምንባቡ ርዕስ የአንበሳ፣ የነብር፣ የጅብና የአህያ ጓደኝነት በሚል ስር የቀረበ ሲሆን በመሃከላቸው መካካድና ምክንያት ፈልጎ ጥቃት ማድረስ ከምንባቡ ጽንሰ ሃሳብ መረዳት ተችሏል፡፡ እንደ ባህል ስንመለከተው በክልሉ ያሉ ብሔር ብሔረሰቦች በመቻቻል፣ በመከባበርና አንዱ ለሌላው እውቅና ሰጥቶ በሚኖርበት /እየኖረ ባለበት የዚህ ዓይነት መልዕክት(ግርታ ሊፈጥር በሚችል መልኩ) መልዕክት ማስተላለፍ የሚችል ምንባብ ነው፡፡ የአንድ ምንባብ ይዘት ሊያስተላልፍ የተፈለገውን መልዕክት ሲያስተላልፍ የማህበረሰቡን ባህልና ወግ እንዲሁም ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን በጠበቀ መልኩ ቢሆን የተሻለ ነው፡፡ ምክንያቱም በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚገኙት ተማሪዎች ከተለያየ ማህበረሰብ የመጡ እንደመሆናቸው መጠን ይህንን የተማሪዎችን ዳራ ያገናዘበ ቢሆን የተሻለ ነው፡፡

በዚሁ ምዕራፍ 2 ጓደኛን ማፍራት በሚል ገጽ 24 ምንባቡ ርዕስ የሌለው ነገር ግን ስለ ዝንጀሮና አይጥ የተፃፈ ታሪክ እናገኛለን፡፡ የዚህ ታሪክ ሃሳብም ሁለቱ በጋራ ሰርተው ያገኙትን አስቀምጠው በችግራቸው ጊዜ ሊጠቀሙበት ተስማምተው ሳለ አንደኛው ግን ስምምነቱን በማፍረስ በጋራ ያስቀመጡትን በድብቅ በመውሰድ እንደተጠቀመበትና መልሶ በመጮህ (ጅራፍ ራሱ ገርፎ ራሱ ይጮሃል እንደሚባለው) ለማስመሰል እንደሞከረ ያሳየናል፡፡ የዚህ ምንባብ መልዕክት ከኦሮሞ ባህል ጋር የማይሄድ ማለትም ኦሮሞ በባህሉ አብሮና አካፍሎ የሚበላ እንጂ በዚህ ዓይነት የክህደት ምግባር ላይ እንደማይታይ ይታመናል፡፡ በመሆኑም መልዕክቱ ብዙም አቃፊ ባለመሆኑ ለማስተማሪያነት የሚቀርቡት ምንባቦችም ሆነ አጫጭር ታሪኮች ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነታቸው ተጠብቆ ቢዘጋጁ የተሻለ ነው፡፡ አባሪ አራትን ይመልከቱ፡፡

በዚሁ መማሪያ መጽሃፍ በምዕራፍ 6 የምዕራፉ ርዕስ የሃገር ፍቅር ሲሆን በገጽ 58 ላይ የቀረበ የምንባቡ ርዕስ የአንበሳና የጅብ ጓደኝነት በሚል ቀርቧል፡፡ በዚህ ምንባብ አንበሳና ጅብ በጓደኝነት ሲኖሩ አንዱ የሌለውን አንደኛው ስላለው በማንነቱ ምክንያት የሌላውን ለመውሰድ መፈለግና ከራስ በላይ ንፋስ የሚል አመለካከት ያዘለ ነው፡፡ ይህም ታሪክ ከህብረተሰቡ ባህልና ልማድ አንፃር የቀረበው መልዕክት የተማሪዎችን ዳራ ያልጠበቀ መሆኑን ያሳየናል፡፡

በዚሁ መማሪያ መጽሃፍ በምዕራፍ 9 ገጽ 87 ላይ የምዕራፉም የምንባቡም ርዕስ ሱሰኝነት በሚል የቀረበና እንዲሁም በመምህሩ መምሪያ መጽሃፍ በዚሁ ምዕራፍ ገጽ 65 ላይ ጫት የመቃም ሱስ የሚል ምንባብ ቀርቧል፡፡ በዚህ ርዕስ ስር የቀረበ ከቅንጫቢው ጽንሰ ሃሳብ ለመረዳት እንደተቻለው ሱስ አምጪ ነገሮችን አብዝቶ መጠቀም ለጉዳት እንደሚዳርግ የተጠቀሰ ቢሆንም መጠቀም እንደሌለባቸውና ከሱስ ጋር የተያያዙ ሃሳቦችን ማቃረቡ አግባብ እንዳልሆነ አጥኚው ያምናል፡፡ ከባህል አንፃር በሱስ መጠመድ የማይደገፍና መልካም እንዳልሆነ የሚታመን ሲሆን በዚህ ሁኔታ በምንባብ መልክ ቀርቦ መልዕክት ማስተላለፉ አግባብነት የሌለውና ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን ያልጠበቀ መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡

ሰንጠረዥ፡- 4.7 በ8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሃፍ ባህልን ያልጠበቁ (ማህበረሰቡ ብዙም የማይደግፋቸው) ሃሳብ ያላቸው ምንባብ ማሳያ

| ምዕራፍ | የምዕራፉ ርዕስ | ገጽ | የምንባቡ ርዕስ | ገጽ | በምንባቡ የተንጸባረቀው ጽንሰ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|---|
| 2 | መከባበር | 16 | መከባበር | 20 | በአንቀጽ 3 ውስጥ ድንጋይ ሲወረወርበት በቸልታ አያልፍም ያቅሙን ያህል ጥቃቱን ለመከላከል ይውተረተራል እንጂ የሚል ዐረፍተ ነገር ተጠቅሷል፡፡ |
| 10 | ውሳኔ መስጠት | 114 | አንበሳና ጅብ | 123 | የማይገባ ጓደኝነት አላስፈላጊ ዋጋ ሊያስከፍል እንደሚችልና ከሚመስል ጋር እንደሚሻል እንጂ በመተባበርና |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | በመከባበር በጋራ መኖሩ አግባብ እንዳልሆነ ያሳያል፡፡ (ቡድናዊነት የተንጸባረቀበት ነው) |
| | | | የዳኛ ውሳኔ (በግጥም መልክ የቀረበ (በመምህሩ መምሪያ)) | 76 | አንዲት ልጅ ከቢጤዋ ጋር ወደድኩሽ ወደድኩህ በሚል ወሲባዊ ግንኙነት ውስጥ ገብታ ውላ ስታድር በመጸጸት ለቤተሰቦቿ በሐሰት ተደፈርኩ ብላ ፍርድ ቤት በመቅረብ በቀረበባት መስቀለኛ ጥያቄ መረታቷን ያስረዳል፡፡ |

ከላይ በሰንጠረዡ ለማየት እንደተሞከረው በ8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሃፍ ከቀረቡት 10 ምዕራፎች ውስጥ 2 ባህልን ያልጠበቁ ምንባቦች ቀርበዋል፡፡ በተማሪው መማሪያ መጽሃፍ ምዕራፍ 2 ገጽ 20 ላይ የምንባቡ ርዕስ መከባበር በሚል የቀረበ ሃሳብ አንቀጽ 3 ላይ ድንጋይ ሲወረወርበት በቸልታ አያልፍም፤ ያቅሙን ያህል ጥቃቱን ለመከላከል ይውተረተራል የሚል ዐረፍተ ነገር ተጠቅሷል፡፡ ይህ ሃሳብ ርዕሱን(መከባበር) ሊቃረን የሚችል ሃሳብ እንደሆነና አንድ ሰው በወቅታዊ ስሜት ለሚከሰቱ ነገሮች ጉዳዩን በመረጋጋት ማየትና ምላሽ ከመስጠት ይልቅ በመከላከል ነገሩን ማስተካከል ሲቻል ተመሳሳይ ምላሽ መስጠት መከባበርንና መቻቻልን ያላገናዘበና ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን ያልጠበቀ ሃሳብ መሆኑን ማየት ተችሏል፡፡

በዚሁ መጽሃፍ በምዕራፍ 10 የምንባቡ ርዕስ አንበሳና ጅብ የሚል በገጽ 123 የቀረበ ምንባብ የማይገባ ጓደኝነት መመስረቱ ትክክል እንዳልሆነና ራስን ከሚመስል ጋር በቡድን በመሆን መንቀሳቀስ እንደሚገባ ይገልፃል፡፡ ይህም ጅቦች ከጅቦች ጋር ቡድን መፍጠር እንዳለባቸው ያስቀምጣል፡፡ ይህ ሃሳብ ደግሞ የአንድ ወገን ቡድናዊ ግንኙነት(ቡድን መመስረት) በመፍጠር ራስን መከላከል የሚል ሃሳብ ያለውና አብሮነትን፣ መረዳዳትን፣ መቻቻልንና መተጋገዝን እንዲሁም ብዝሃነትን የዘነጋ ሃሳብ ያለው ነው፡፡ በመሆኑም ለህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት የተሰጠው ትኩረት እንደሌለ ያሳያል፡፡

በዚሁ ክፍል በመምህሩ መምሪያ መጽሃፍ ውስጥ በምዕራፍ 10 ገጽ 76 ላይ የዳኛ ውሳኔ የሚል በግጥም መልክ የቀረበ ምንባብ ይገኛል፡፡ የዚህ ምንባብ ሃሳብ አንዲት ወጣት ከአንድ ወጣት ጋር ወደድኩሽ ወደድከሁ በሚል ሃሳብ ወሲባዊ ግንኙነት ውስጥ ገብተው ውላ ስታድር ተመልሳ ተጸጽታ ለቤተቦቿ ተደፈርኩ ብላ በሐሰት በመናገር ፍርድ ቤት ቀርበው በቀረበላት መስቀለኛ ጥያቄ ውሸቷን(ፈልጋ እንጂ ተገዳ ድረጊቱን እንዳልፈጸመች) መሆኑን ዳኛው ተረድቶ ተከሳሹን በነፃ አሰናብቷል፡፡ ከዚህ ምንባብ የምንረዳው ሃሳብ የኦሮሞ ባህል ራሱን የቻለ የጋብቻ ስርዓት ያለው ሲሆን በዚህ መልኩ ያልተገባ ግንኙነትን የሚያስተላልፍ መልዕክት ያለው ሃሳብ መቅረቡና እንዲሁም ውሸትና ክህደት አላስፈላጊ ሆኖ እያለ በውሸት ለክስ መጋበዟ በተወሰነው ውሳኔ ራሷንም ሆነ ቤተሰቦቿን ያሳፈረ ሆኖ ቀርቧል፡፡ ይህ ምንባብ ባህላዊ ይዘትን ያልጠበቀ በመሆኑ ቢታሰብበት የተሻለ ነው፡፡

በአጠቃላይ በሁለቱም መማሪያ መፃህፍት ለማስተማሪያነት የቀረቡትን ምንባቦች መልዕክት ስናጠቃልል የኦሮሞ ብሔረሰብ ባህልን ያልጠበቁ (ማህበረሰቡ ብዙም የማይደግፋቸው) በመሆናቸው እንደዚህ ዓይነት ምንባቦች ከመቅረባቸው በፊት ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነታቸው ቢጤን የተሻለ ነው፡፡

### 4.1.4.2. መመሪያዎች

በሁለቱም በ7ኛና በ8ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የአማርኛ ቋንቋን ለማስተማር የቀረቡት መመሪያዎች ባህላዊ ይዘት የሌላቸውና ሊኖራቸው የማይችል መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡ ምክንያቱም መምሪያዎች ሲዘጋጁ የሚቀርቡትን ጥያቄዎች ተማሪዎቹ እንዴት መስራት እንዳለባቸው አመልካች እንጂ ከባህል ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት አለመኖሩ አግባብነት ያለው ነው፡፡

### 4.1.4.3. መልመጃዎች

በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን ሊያዳብሩ ይችላሉ ተብለው በግብዓትነት ከሚቀርቡት ይዘቶች ውስጥ የተለያየ ይዘት ያላቸው መልመጃዎች ቀርበዋል፡፡ በመልመጃዎቹ ውስጥ የቀረቡት ምሌያዊ አነጋገር፣ በምክንያትና መንስኤ አስተያየት ስጡ የሚሉ መመሪያዎች በዐረፍተ ነገሮች መልክ የቀረቡትን

ከመልመጃዎቹ ውስጥ ለይቶ በማውጣት የተሰበሰቡ መረጃዎች ባህላዊ ይዘታቸውን በመለየት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

በ7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሃፍ ገጽ 51 በንዑስ ርዕስ 2.2 መፃፍ በሚለው ርዕስ ምሳሌ ላይ "ልጅ ደረሰ ቤት ፈረሰ" የሚል ሃሳብ ይገኛል፡፡ ይህ ሃሳብ በልጆች አዕምሮ ውስጥ ጫና ሊያሳድር የሚችል ያልተገባ አባባል ነው፡፡ ስለዚህ የልጆቹን አዕምሮ ብስለት ያላገናዘበ በመሆኑ ቢታይ መልካም ነው፡፡ እንዲሁም በ8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሃፍ ውስጥ በ 4 መመሪያዎች ስር 5 ባህልን ያልጠበቁ ዐረፍተ ነገሮች ቀርበዋል፡፡ እነዚህም፡-

በገጽ 24 መልመጃ 1 መመሪያ ለ ስር ጥያቄ 4 እና 5

- ልጁ በእግሩ ጠልፎ አሰናከላት፡፡
- ባለጌ ልጆች መጥፎ ስራ ሲሰሩ ይውላሉ፡፡

እነዚህ ከላይ የቀረቡት ዐረፍተ ነገሮች ባህልን ያልጠበቁ ሃሳቦች ናቸው፡፡ ምክንያቱም አጥኚው ከማህበረሰቡ ባህል አኳያ አግባብነት ያላቸው ቃላት ሆኖ ያላመነበት እና ሴት ልጅን ማክበር ሲገባ በእግሩ ጠልፎ ማሰናከሉን የሚያሳይ ሃሳብ መቅረቡ ተገቢነት የለውም የሚል እምነት አለው፡፡ ሌላው ደግሞ አንድን ልጅ ባለጌ የሚያስብለው ምን ዓይነት ስራ እንደሆነ ቢጠቀስ መልካም ነው፡፡ ካልሆነም በልጆች አዕምሮ ሌላ ትርጉም እንዳይኖረው ዝርዝር ሃሳቡ ቢቀመጥ የተሻለ ነው፡፡ እነዚህ ከላይ የቀረቡት ሁለቱ ዐረፍተ ነገሮች ከስነ ምግባር ውጭ የሆነ ሃሳብ ያላቸው በመሆኑና የማህበረሰቡን ተቻችሎና ተከባብሮ የመኖር ባህል ያልጠበቁ በመሆኑ በዚህ መልኩ ባይቀርቡ የተሻለ ነው፡፡

በገጽ 37 ተግባር 2 መመሪያ ሀ ምሳሌ ስር

- ቀልቤሳ ጥንቃቄ የጎደለው ወሲብ ፈጽሞ ለበሽታ ተጋለጠ፡፡

በዚህ ዐረፍተ ነገር የቀረበው ሃሳብ ከጋብቻ በፊት የግብረ ስጋ ግንኙነት ማድረግ እንደሚቻልና ተማሪዎቹም በዚህ ምክንያት ያልተፈለገ አመለካከት ውስጥ እንዲገቡና ምንም ችግር የለም የሚል ስሜት ሊፈጥርባቸው የሚችል በመሆኑ፣ የተማሪዎቹም

እድሜ በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ በቂ ግንዛቤ ላይኖራቸው ስለሚችል በዚህ መልኩ ባይቀርብ የተሻለ ነው፡፡

በገጽ 99 መመሪያ ለ ጥያቄ ተራ ቁጥር 4 ላይ

- መረርቱ የ4ኛ ክፍል ተማሪ እያለች ትምህርቷን አቋርጣ በቤተሰብ ግፊት ለአባቷ ጓደኛ ልጅ ተዳረች፡፡

በዚህ ዐረፍተ ነገር የቀረበው ሃሳብ ያለእድሜ ጋብቻ፣ ትምህርቷን እንድታቋርጥና ያለፍላጎቷ ለትዳር እንደበቃች ያሳያል፡፡ ከዚህ መልዕክት የምንረዳው ሴቶች ልጆች ትምህርታቸውን አቋርጠው ትዳር መያዝ እንደሚችሉ፣ ትዳር እድሜን እንደማይወስን፣ ቤተሰብም ልጆቹን ያለእድሜና ያለፍላጎት ትዳር እንዲይዙ እንደሚያስገድድ የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ ሃሳብ ከባህል አንፃር ሴት ልጅ ለጋብቻ እድሜ መድረስ እንዳለባትና የሷን ፍቃደኝነት የዘነጋ ሃሳብ ነው፡፡ እንዲሁም ሴቶች ከትምህርት ይልቅ ለትዳር ቅድሚያ እዲሰጡ የሚያሳይ መልዕክት ያለው በመሆኑ በዚህ መልኩ ባይዘጋጅና የማህበረሰቡን ዳራ የጠበቀ ቢሆን የተሻለ ነው፡፡

በገጽ 121 መመሪያ ቀ ስር ጥያቄ ቁጥር 3 ላይ

- ገንዘብ ስትጠይቁ ቤተሰብ ፍቃደኛ ሆኖ አይሰጣችሁም፡፡ በዚህ ፍራቻ ለብርቱ ጉዳይ የተቀመጠውን ብር ተደብቃችሁ ወሰዳችሁ፡፡ የሚል ዐረፍተ ነገር ተቀምጧል፡፡

የዚህ ሃሳብ መልዕክት ቤተሰብን ገንዘብ ከመጠየቅ ይልቅ በስርቆት መልክ መውሰድ የተሻለ ነው የሚል ሃሳብ ያለው ነው፡፡ ስርቆት ደግሞ ከባህል አንፃር የተጠላና የማይደገፍ በመሆኑ ይህ መልዕክት መስተካከል እንዳለበት አጥኚው ተገንዝቧል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በመልመጃ መልክ የቀረቡት 5 ጥያቄዎች የማህበረሰቡን ባህልና ወግ ያልጠበቁ በመሆኑ ባህልን በጠበቀና የተማሪዎቹን ዳራ ባገናዘበ መልኩ ማቅረብ ቢቻል የተሻለ መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡

### 4.1.5. ከኃይማኖት አኳያ

በ7ኛና በ8ኛ ክፍል አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መፃህፍት ኃይማኖታዊ ይዘት ይንጸባረቅባቸዋል ብሎ አጥኚው ካሰባቸው የመማሪያ መፃህፍት ግብዓቶች ውስጥ ስሞች፣ ምንባቦች(ግለ-ታሪኮች)ና ምሌያዊ አነጋገሮች ናቸው፡፡ ጥናቱ በሚደረግበት ወቅት ኃይማኖታዊ ይዘት ያላቸዉ ምንባቦችና ግጥሞች የሉም፡፡ በመሆኑም ከኃይማኖት አኳያ ትንታኔ የተደረገባቸው /የተካሄደባቸው ስሞች፣ ግለ ታሪኮችና ምሌያዊ አነጋገሮች ሲሆኑ ዝርዝሩን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

#### 4.1.5.1. ስሞች

የስሞች አሰያየም ብሔረሰባዊ፣ ባህላዊ ወይም ኃይማኖታዊ ሊሆኑ ይችላል፡፡ ብሔረሰባዊ ስንል ማንኛውም ማህበረሰብ በኃይማኖት ልዩነት ሳይኖር የብሔረሰቡ የስም አሰያየም በመከተል የስም ስያሜ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ይህ ዓይነቱ የስም አሰያየም ኃይማኖታዊ ይዘት የለውም፡፡ ባህላዊ የስም አሰያየም ስንል አንድ ማህበረሰብ የአካባቢውን ባህልና ወግ በጠበቀ መልኩ ባህሉን ለመግለጽ የሚጠቀምበት የስም አሰያየም ነው፡፡ ይህ ባህላዊ አሰያየም ኃይማኖታዊ ይዘት የሌለውና የኃይማኖት ልዩነትን የማያንጸባርቅ ስም ሊሆን የሚችል ነው፡፡ ኃይማኖታዊ የስም አሰያየም ደግሞ ብሔርንም ሆነ ባህልን ያልተከተለ ሆኖ ኃይማኖታዊ ይዘት ያለው የስም አሰያየም ነው፡፡ በዚህ ኃይማኖታዊ አሰያየም የግለሰቡን ኃይማኖት በቀላሉ ማወቅ ያስችላል፡፡

በሁለቱም መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የተጠቀሱትን ጠቅላላ ስሞች በመሰብሰብ የተለዩ ሲሆን በእርግጠኝነት እነዚህ ስሞች በትክክል ኃይማኖታዊ ናቸው ለማለት አያስደፍርም፡፡ ምክንያቱም በጥናት የተለየ ነገር ባለመሆኑ ነው፡፡ ነገር ግን ከአካባቢው የስም አሰያየም አኳያ የተወሰዱና የእስልምና ስሞች ደግሞ በብዛት የዓረብኛ ስሞች በመሆናቸው ከአካባቢያዊ አሰያየም አኳያ ለመለየት ተችሏል፡፡ እንዲሁም የቀረቡት ግለ-ታሪኮች ኃይማኖታዊ ይዘት ያላቸው ከሆኑ ከታሪኩ ሃሳብ በመነሳት የቀረቡትን ስሞች ለመለየት ተችሏል፡፡ በዚህ ሃሳብ መነሻነት የ7ኛና የ8ኛ ክፍል አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች ለማስተማሪያነት የቀረቡት መማሪያ መፃህፍት

በምንብቦች፣ በመመሪያዎችና በመልመጃዎች ውስጥ የቀረቡትን ስሞች ከኃይማኖት ጋር ያላቸውን ግንኙነት ተለይተው ቀርበዋል፡፡

ከዚህ ሰነድ ፍተሻ የተገኙትን የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መገለጫ ከሆነው ከኃይማኖት አኳያ የተሰበሰቡት መረጃዎች የስሞች አቀራረብ በአሃዝ ተገልጿል፡፡ እነዚህ የተለያዩ ስሞችም ከጠቅላላ ስሞች አኳያ የያዙትን ድርሻ በመቶኛ ተሰልቶ ቀርበዋል፡፡ እንደዚሁም ካሉት ጠቅላላ ስሞች ውስጥ ኃይማኖታዊ የሆኑና ያልሆኑ ስሞችን ተለይተው በአሃዝ ተገልጸዋል፡፡ ይህም የተደረገው ኃይማኖታዊ የሆኑ ስሞችን የየትኛው ኃይማኖት ከየትኛው ኃይማኖት ስም በአብላጫ ተጠቅሷል በሚል የቀረቡ ስሞችን የማወዳደር ስሌት የተሰላው በተማሪው መማሪያ መጽሃፍና በመምህሩ መምሪያ ከቀረቡት ጠቅላላ ስሞች አኳያ እንጂ በተማሪው መማሪያ መጽሃፍና በመምህሩ መምሪያ የቀረቡ ስምችን በተናጠል በማስላት አይደለም፡፡ በዚሁ መሰረት በቀጣዩ ሰንጠረዥ በቁጥርና በመቶኛ ተሰልተው ቀርበው ትንተና ተሰጥቶባቸዋል፡፡

ሰንጠረዥ፡- 4.8 የስሞች አቀራረብ ከኃይማኖት አኳያ

| የክፍል ደረጃ | ጠቅላላ ስሞች | ኃይማኖታዊ ያልሆኑ ስሞች | | ጠቅላላ ኃይማኖታዊ ስሞች | | ኃይማኖታዊ ስሞች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | ክርስትና | | እስልምና | |
| | | ቁጥር | በመቶኛ | ቁጥር | በመቶኛ | ቁጥር | በመቶኛ | ቁጥር | በመቶኛ |
| 7ኛ | 26 | 13 | 50 | 13 | 50 | 8 | 30.77 | 5 | 19.23 |
| 8ኛ | 53 | 33 | 62.26 | 20 | 37.74 | 16 | 30.19 | 4 | 7.55 |
| ድምር | 79 | 46 | 56.23 | 33 | 41.77 | 24 | 30.38 | 9 | 11.39 |

ከላይ በሰንጠረዡ የተገለጹት አሃዛዊ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ከሁለቱም መማሪያ መፃህፍት(የ7ኛና የ8ኛ ክፍል) የተሰበሰቡ ስሞች በ7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሃፍ ውስጥ የቀረቡት ስሞች 26 በ8ኛ ክፍል ደግሞ 53 ሲሆኑ በድምሩ 79 ስሞች ተጠቅሰዋል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ከ7ኛ ክፍል ኃይማኖታዊ ያልሆኑ 13 ከ8ኛ ክፍል 33 በድምሩ 46

ኃይማኖታዊ ያልሆኑ ስሞች ናቸው፡፡ ኃይማኖታዊ ያልሆኑ ሲባል አሻሚ በመሆናቸው የተተው ናቸው፡፡ እንዲሁም ኃይማኖታዊ ስሞች ናቸው ብሎ አጥኚው የለያቸው ስሞች ከሁለቱም መማሪያ መፃህፍት 33 ሲሆኑ ከ7ኛ ክፍል 13 ከ8ኛ ክፍል 20 እንደሆኑ ከላይ በሰንጠረዡ ላይ የተገለጸው አሃዝ ያስረዳል፡፡ ከእነዚህ 33 ኃይማኖታዊ ስሞች ውስጥ 24 የክርስትና ኃይማኖት አመልካች ሲሆኑ 9 ደግሞ የእስልምና ኃይማኖት አመልካች ስሞች ናቸው፡፡ ከዚህ እንደምንረዳው የክርስትና ኃይማኖት አመልካች ስም ከፍተኛ ሲሆን ከጠቅላላ 24(30.38 በመቶ) ሲሸፍን የእስልምና ኃይማኖት ደግሞ ከጠቅላላ ስሞች 9(11.39 በመቶ) የሸፈነ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህ ደግሞ 15(18.99 በመቶ) የክርስትና ኃይማኖት አመልካች ስሞች ብልጫ አሳይቷል፡፡ ይህንን ስሌት ስናይ ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን በጠበቀ መልኩ ኃይማኖት አመልካች ስሞች አልቀረቡም፡፡ አባሪ አንድን ይመልከቱ፡፡

### 4.1.5.2. ምንባብ(የግል ታሪክ)

የምንባቦች አቀራረብ ከኃይማኖት አኳያ ምን ሊመስል እንደሚችል በተደረገው የሰነድ ፍተሻ ግለ-ታሪኮች በምንባብ መልክ ቀርበዋል፡፡ በዚህ መሰረት በ7ኛ ክፍል በመምህሩ መምሪያ መጽሃፍ 2 በ8ኛ ክፍል በተማሪ መማሪያ መጽሃፍ ውስጥ 1 በዚሁ ክፍል በመምህሩ መምሪያ መጽሃፍ ውስጥ 2 በድምሩ የ8ኛ ክፍል 3 ሲሆን ለማስተማሪያነት የቀረቡት ግለ-ታሪኮች በጠቅላላ 5 ናቸው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ 3 ሴትና 2 ወንድ ባለታሪኮች ናቸው፡፡ እነዚህ የግለ-ታሪኮች የባለታሪኮቹን ስኬት፣ ትዝታና ልጆችን የመከሩበት ዘዴ ያመለከተ ነው፡፡ ከእነዚህ ግለ-ታሪኮች ውስጥ የተማሪው መማሪያ መጽሃፍ 8ኛ ክፍል ምዕራፍ 6 ገጽ 70 ላይ የምንባቡ ርዕስ አስቴር ገኖ የሚል ምንባብ የግለሰቧን ታሪክ የያዘ ሲሆን የምንባቡን ይዘት ለማየት እንደተቻለው ግለሰቧ የታወቁበት(ታዋቂ የሆኑበት) ታሪክ በተለያዩ ቋንቋዎች የተፃፉትን የዕምነት መፃህፍትን ወደ አፋን ኦሮሞ(ኦሮምኛ ቋንቋ) ይተረጉሙ እንደነበርና ከተተረጎሙትም መፃህፍት ውስጥ አዲስ ኪዳን፣ የእግዚአብሔር ምህላና መጽሐፍ ቅዱስን ተርጉመው ለማህበረሰቡ(ለኦሮሞ ብሔረሰብ) እንዳበረከቱ በምንባቡ ውስጥ ተጠቅሷል፡፡ ይህም ስራ (መፃህፍትን መተርጎም) መልካምና ለማህበረሰቡ ያበረከቱትን አስተዋጽዖ ሌሎችም ፈለጋቸውን እንዲከተሉ እየተመኘን በመማሪያ መጽሃፉ የሚጠቀሙ ተማሪዎች የተለያየ

ኃይማኖት ተከታዮች በመሆናቸው የምናቀርባቸው ግለ-ታሪኮች ከኃይማኖት ነፃ የሆኑና ቢጤኑ እንዲሁም ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን የጠበቁ ቢሆን መልካም ነው፡፡

### 4.1.5.3. መመሪያዎች

የመማሪያ መፃህፍቱ ከኃይማኖት አኳያ ያላቸውን ሽፋን ለመለየት በ7ኛና በ8ኛ ክፍል የተማሪው መማሪያ መጽሃፍና በመምህሩ መምሪያ ለማስተማሪያነት ከቀረቡት ግብዓቶች ውስጥ መመሪያዎች የራሳቸው ድርሻ አላቸው፡፡ በመሆኑም በመማሪያ መጽሃፍቱ ውስጥ በ7ኛ ክፍል የተማሪው መማሪያ መጽሃፍ 140ና በ8ኛ ክፍል የተማሪው መማሪያ መጽሃፍ 234 በድምሩ በ2ቱም መማሪያ መጽሃፍት ውስጥ 374 መመሪያዎች ያሉ ሲሆን በእያንዳንዳቸው ኃይማኖታዊ አቀራረብ እንደሌላቸው በተደረገው ፍተሻ የተለየ ሲሆን የመመሪያዎች አቀራረብ ከህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት አኳያ ጥሩ ነው፡፡ በዚህ ዙሪያ ክፍተቶች አልታዩም፡፡

### 4.1.5.4. መልመጃዎች

ከኃይማኖት አኳያ የመልመጃዎች አቀራረብ ምን እንደሚመስል በተደረገው ሰነድ ፍተሻ በ7ኛና በ8ኛ ክፍል የተማሪው መማሪያ መጽሃፍና የመምህሩ መምሪያ በተደረገው ፍተሻ በ7ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ምንም ዓይነት ኃይማኖታዊ ይዘትም ሆነ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ያልቀረቡ ሲሆን የመልመጃዎቹ አቀራረብ ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን በጠበቀ መልኩ የተዘጋጁ መሆናቸውን አጥኚው ተረድቷል፡፡ በ8ኛ ክፍል ለማስተማሪያነት የቀረቡት መልመጃዎች ይዘት ኃይማኖታዊ ያልሆኑና መሆን እንደሌለባቸው የሚታመን ቢሆንም በዚሁ መጽሃፍ ምዕራፍ 5 የምዕራፉ ርዕስ ሴቶችን ማብቃት በሚል የተዘጋጀውን የምዕራፉን ትምህርት ግንዛቤ ለማስጨበጥ በቀረቡት መልመጃዎች በገጽ 58 ተግባር አራት ስር ምሳሌያዊ አነጋገሮች በሚለው በመመሪያ ሐ ስር ጥያቄ 2 ላይ "የቅርብ ጠበል የልጥ መንከሪያ ይሆናል፡፡" የሚል ምሳሌያዊ አነጋገር ተጠቅሶ ይገኛል፡፡ ይህ ሃሳብ ኃይማኖታዊ ይዘት ያለው በመሆኑ ለማስተላለፍ የተፈለገውን ሃሳብ ለማሳየት በአግባቡ ያስተላልፋል ለማለት ያዳግታል፡፡ በመሆኑም ኃይማኖታዊ ይዘት ያላቸውን ሃሳብ ከመጠቀም ይልቅ ሌላ ከኃይማኖት ነፃ የሆነ ወይም የጋራ ይዘት ያለው ሃሳብ ቢጠቀስ የተሻለ ይሆናል፡፡

ለምሳሌ፡- "ነቢይ በሃገሩ አይከበርም፡፡" ቢባል የተሻለ ይሆን ነበር፡፡

### 4.1.6. ከፆታ አኳያ

የ7ኛና የ8ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍቱ የአማርኛ ቋንቋን ለማስተማር (ለማዳበር) ይረዳሉ ተብለው በግብዓትነት የቀረቡት ምንባቦች፣ መመሪያዎችና መልመጃዎች ከፆታ አኳያ ምን ያህል ትኩረት ተሰጥቶባቸው እንደተዘጋጁና ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን በጠበቀ መልኩ መዘጋጀታቸውን ለማወቅ የሰነድ ፍተሻ ተደርጓል፡፡ በተደረገውም ፍተሻ በመማሪያ መፃህፍቱ በይዘትነት የቀረቡትን ምንባቦች፣ መመሪያዎችና መልመጃዎች በተናጠል በመጥቀስ መረጃዎቹ ተሰብስበዋል፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎች ከመቅረባቸው በፊት በተማሪው መማሪያ መጽሃፍና በመምህሩ መምሪያ ፆታ ነክ የሆኑ የስሞች አቀራረብ፣ የግሶች አቀራረብ፣ የሀረጎች አቀራረብና የዐረፍተ ነገሮች አቀራረብ መሰረት በማድረግ በሙሉ ተመዝግበው በአሃዝ ቀርበዋል፡፡ እንደአቀራረባቸውም ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ እነዚህን ፆታ ነክ የስሞች አቀራረብ ከጠቅላላ ስሞች፣ የግሶች አቀራረብ ከጠቅላላ ግሶች፣ የሀረጎች አቀራረብ ከጠቅላላ ሀረጎችና የዐረፍተ ነገሮች አቀራረብ ከጠቅላላ ዐረፍተ ነገሮች ያላቸው ድርሻ ተሰልቶ በመቶኛ ተገልጸዋል፡፡ እንዲሁም ከጠቅላላው የወንድ ፆታ አመልካች ምን ያህል እንደሆነና የሴት ፆታ አመልካችም ከጠቅላላው በማወዳደር ተሰልተው በመቶኛ ቀርበዋል፡፡ ይህም ስሌት የ7ኛ ክፍል የተማሪው መማሪያ መጽሃፍና የመምህሩ መምሪያ ላይ ያሉትን በጣምራ እንዲሁም የ8ኛ ክፍል የተማሪው መማሪያ መጽሃፍና የመምህሩ መምሪያ ላይ ያሉትን በጣምራ እንዲሰሉ ተደርጓል፡፡ የተማሪው መማሪያ መጽሃፍና የመምህሩ መምሪያ በተናጠል በማስላት አይደለም፡፡ በዚሁ መሰረት በቅደም ተከተል የምንባቦች፣ የመመሪያዎችና የመልመጃዎች አቀራረብ ከፆታ አኳያ ምን እንደሚመስል እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

#### 4.1.6.1. ምንባቦች

በ7ኛና በ8ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ውስጥ በግብዓትነት የቀረቡትን ምንባቦች ከፆታ አኳያ ምን እንደሚመስል በተደረገው ፍተሻ የምንባቦቹ ይዘት ፆታ ተኮር ያልሆኑ መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ በምንባብ መልክ ከቀረቡት ውስጥ የግለሰቦችን

ታሪክ የሚያንጸባርቁና ለማስተማሪያነት ይረዳሉ ተብለው የቀረቡ ምንባቦች ይዘት ስንመለከት ያላቸውን/ባለታሪኮቹን ስናይ ከወንድም ከሴትም የተውጣጡ ሆኖ ነገር ግን የሴቶች ሽፋን ይበልጣል፡፡ ለዚሁም ቀጥሎ በሰንጠረዥ የቀረበ ሲሆን ማብራሪያውም ተከትሎ ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ፡- 4.9. የምንባቦች (የግል ታሪኮች) ከፆታ አኳያ ያላቸውን ሽፋን ማሳያ

| የክፍል ደረጃ | በመጽሃፍቱ የቀረቡት ታሪኮች | ገጽ | የባለታሪኮች ስም | እውቅና ያገኙበት ስራ | ፆታ |
|---|---|---|---|---|---|
| 7 | ትዝታ | 35 | አልተገለጸም | የልጅነት ትዝታ | ወንድ |
| | የመልካም አባት ኑዛዜ | 42 | አልተገለጸም | ልጆቹን የመከረበት ዘዴ | ወንድ |
| 8 | አስቴር ገኖ | 70 | አስቴር ገኖ | በመጽሃፍ ትርጉም | ሴት |
| | ደራርቱ ቱሉ | 44 | ደራርቱ ቱሉ | ሩጫ | ሴት |
| | ጌጤ ዋሚ | 47 | ጌጤ ዋሚ | ሩጫ | ሴት |

በ7ኛ ክፍል ለማስተማሪያነት ከቀረቡት ምንባቦች ውስጥ 2 ምንባብ ግለ-ታሪክ በ8ኛ ክፍል ለማስተማሪያነት ከቀረቡት ምንባቦች ውስጥ 3 ግለ-ታሪኮች ቀርበዋል፡፡ በሁለቱም መማሪያ መፃህፍት የቀረቡት ግለ-ታሪኮችን ያዘሉ 5 ምንባቦች የቀረቡ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ 2 የቀረቡት ምንባቦች የባለታሪኮቹ ስም ያልተገለጸ ቢሆንም የዐረፍተ ነገሮቹ ማሰሪያ አንቀጽ የወንድ ፆታ አመልካች በመሆናቸው የወንዶች ሲሆኑ 3 ደግሞ የሴቶች ናቸው፡፡ ይህም ከቀረቡት ግለ-ታሪኮች ከጠቅላላው ውስጥ 2(40 ከመቶው) የወንዶች ታሪክ እንዲሁም 3(60 ከመቶው) የሴቶች ታሪክ ነው፡፡ ይህ አቀራረብ የሴቶች ከወንዶቹ የ 20 በመቶ ብልጫ ያለው ሆኖ ታይቷል፡፡ ይህ አቀራረብ ከህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት አኳያ ትኩረት ያልተሰጠው መሆኑን ያሳያል፡፡ አባሪ አምስትን ይመልከቱ፡፡

### 4.1.6.2. መመሪያዎች

በ7ኛና በ8ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የአማርኛ ቋንቋን ለማስተማር በግብዓትነት የቀረቡትን መመሪያዎች ከፆታ አኳያ ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን በጠበቁ መልክ መዘጋጀታቸውን ለማየት በተደረገው የሰነድ ፍተሻ የመመሪያዎቹ ይዘት አቀራረብ ፆታ ተኮር አይደሉም እንዲሆኑም አይመከርም፡፡ ነገር ግን አልፎ አልፎ የቀረቡትን መመሪያዎች በሚከተለው ሰንጠረዥ የቀረቡ ሲሆን ማብራሪያዉም ተከትሎ ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ፡- 4.10 የመመሪያዎችና የፆታ ግንኙነት ማሳያ

| የክፍል ደረጃ | ጠቅላላ መመሪያዎች | በአንድ ፆታ የተነገሩ መመሪያዎች | |
|---|---|---|---|
| | | በወንድ ፆታ የተነገሩ | በሴት ፆታ የተነገሩ |
| 7 | 140 | 2 | -- |
| 8 | 234 | 5 | -- |
| ድምር | 374 | 7 | -- |

ከላይ በሰንጠረዡ ላይ እንደተመለከተው በ7ኛ ክፍል የተማሪው መጽሃፍ ውስጥ 2 መመሪያዎች በ8ኛ ክፍል የተማሪው መጽሃፍ ውስጥ 5 መመሪያዎች በድምሩ 7 መመሪያዎች ቀርበዋል፡፡ እነዚህ መመሪያዎች ከጠቅላላው መመሪዎች 374 ውስጥ 7(1.87 በመቶኛ) መመሪያዎች በወንድ ፆታ አምልካች የቀረቡ ሲሆን ከቀሪዎቹ ውስጥ ምንም ዓይነት መመሪያ በሴት ፆታ አመልካች የቀረበ የለም፡፡ ይህንን ስንመለከት የፆታ እኩልነትን ያልጠበቀ ነው ለማለት ያስችላል፡፡ ለዚሁም ከመማሪያ መጽሃፍቱ የተወሰዱ አስረጅዎችን በሚከተለው መልኩ በማሳየት ማብራሪያም ተሰጥቶበታል፡፡

አስረጅ፡-1

በ7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሃፍት ውስጥ የቀረቡት መመሪያዎች

ገጽ 6 መልመጃ 2 ስር መመሪያ መ ጥያቄ ቁጥር 2

2. "በቅድሚያ ከዕጽዋት ውጤቶች ከሚዘጋጁ ምግቦች መካከል አንዱን ምረጡ ከዚያም ስለአዘገጃጀቱ የሚያውቅ ሰው በመጠየቅ ያገኛችሁትን ማብራሪያ በክፍል ውስጥ አቅርቡ፡፡"

አስረጅ ፡-2

ገጽ 26 መልመጃ 2 መመሪያ 2

2. "ከእናንተ ርቆ ሌላ አካባቢ ለሚኖር ጓደኛችሁ ወይም ዘመዳችሁ የሰላምታ ደብዳቤ ፃፉና የፃፋችሁትን ደብዳቤ ለክፍላችሁ ተማሪዎች አንብቡ፡፡"

አስረጅ፡- 3

በ8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሃፍት ውስጥ የቀረቡት መመሪያዎች

ገጽ 104 መመሪያ ሐ

ሐ. "ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላትና ሀረጋት የአገባብ ፍቺ ስጡና ዓረፍተ ነገር መስርቱባቸው፡፡ የመሰረታችሁትን ዓረፍተ ነገር በቃላችሁ ተናገሩ፣ ሌሎቻችሁ አንዱ ተማሪ የተናገረውን አዳምጡና መልሳችሁ በማለት አዳምጦ የመናገር ክሂላችሁን አዳብሩ፡፡

አስረጅ፡- 4

ገጽ 107 መመሪያ ሀ ንዑስ መመሪያ

1. ከስዕል አንድ ስለኦሮሞ ባህላዊ ጋብቻ ስርዓት የሚያውቅ ተማሪ በስዕሉ ላይ ተመስርቶ ስለጋብቻ ስርዓቱ ይተርክላችሁ፣ የተቀራችሁት በጥሞና አዳምጡ፡፡
2. በስዕል ሁለት ክብ ሰርተው የተቀመጡ ሽማግሌዎች ምን እያደረጉ ነው? ስለዚህ ባህል የሚያውቅ ተማሪ ሲያስረዳ የተቀራችሁት አዳምጡ፡፡
3. በስዕል ሦስት የምታዩዋቸው ሴቶቹ የያዙዋቸው ምን ይባላሉ? ባህላዊ አገልግሎታቸውስ ምንድነው?

4. በስዕል አራት ስለምትመለከቱት የባህል ጭፈራ የሚያውቅ ተማሪ ወይም ሌላ ሰው/እንግዳ ጋብዙና መቼና የት፣ ለምን ጊዜ እንደሚከወን ሲያስረዳ አዳምጡ፡፡ አባሪ ስድስትን ይመልከቱ፡፡

አስረጅ፡- 5

ገጽ 111 ቅድመ ጽሁፍ ትግበራ ስር

- "ሃሳቡ አንድ ቢሆንም የቡድናችሁ ተወካይ በቃሉ ባቀረበውና እናንተ በጽሁፍ ባቀረባችሁት ጽሁፍ መካከል ያለውን ልዩነት አስተውላችሁ ከየቡድናችሁ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ ተራ መሰረት ሁለት ሁለት ተማሪዎች አቅርቡ፡፡"

ከላይ በአስረጅ ከ1-5 የቀረቡት መመሪያዎች 8 ሲሆኑ የመመሪያው መግቢያ በብዙ ቁጥር ይጀምርና ወደ ነጠላ ቁጥር ይመልሳል፡፡ ከቀረቡት ውስጥ 7(87.5 በመቶ) የሆኑት በወንድ ፆታ የተነገሩ መመሪያዎች ሲሆን ከዚህ ውስጥ በሴት ፆታ የተነገረ አንድም መመሪያ የለም፡፡ ከዚህ በላይ ከቀረቡት አስረጅዎች በወንድ ፆታ የተነገሩ ለመሆናቸው የተሰመረባቸውን ቃላት ወይም ሀረጋት በማየት መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ እንደምንረዳው ፆታዊ አድልኦ መኖሩን ነው፡፡ መመሪያዎች በሚቀርቡበት ወቅት ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን በጠበቀ መልኩ ቢዘጋጁ የተሻለ ነው፡፡ ከቀረቡት ጠቅላላ መመሪያዎች አኳያ ሲነፃጸር መልካም ነው፡፡ ከላይ የቀረቡት መመሪያዎች በሴት ፆታ ቢነገሩ ምንም ዓይነት የትርጉም ለውጥ ሳያመጡ ማስተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት ማስተላለፍ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ፡-

አስረጅ 2

2. "ከእናንተ ርቃ ሌላ አካባቢ ለምትኖር ጓደኛችሁ ወይም ዘመዳችሁ የሰላምታ ደብዳቤ ፃፉና የፃፉችሁትን ደብዳቤ ለክፍላችሁ ተማሪዎች አንብቡ፡፡"

አስረጅ 4

1. ከስዕል አንድ ስለኦሮሞ ባህላዊ ጋብቻ ስርዓት የምታውቅ ተማሪ በስዕሉ ላይ ተመስርታ ስለጋብቻ ስርዓቱ ትተርክላችሁ፣ የተቀራችሁት በጥሞና አዳምጡ፡፡

2. በስዕል ሁለት ክብ ሰርተው የተቀመጡ ሽማግሌዎች ምን እያደረጉ ነው? ስለዚህ ባህል የምታውቅ ተማሪ ሲታስረዳ የተቀራችሁት አዳምጡ፡፡

### 4.1.6.3. መልመጃዎች

በ7ኛና በ8ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የአማርኛ ቋንቋን ለማስተማር በግብዓትነት የተለያዩ መልመጃዎች ተዘጋጅተው ቀርበዋል፡፡ በዚሁ መሰረት በጠቅላላ የቀረቡት መልመጃዎች በ7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሃፍ ውስጥ 81 በ8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሃፍ ውስጥ 68 በድምሩ 149 መልመጃዎች ቀርበዋል፡፡ እነዚህ መልመጃዎች እንደ አቀራረባቸው በውስጣቸው የቀረቡ ስሞች፣ ግሶች፣ ሀረጎችና ዐረፍተ ነገሮችን መሰረት በማድረግ በተናጠል የተዘጋጁ ናቸው፡፡

#### 4.1.6.3.1. ስሞች

በ7ኛና በ8ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የአማርኛ ቋንቋን ለማስተማር በግብዓትነት የተለያዩ መልመጃዎች ተዘጋጅተው ቀርበዋል፡፡ በእነዚህ መልመጃዎች ውስጥ የተለያዩ ስሞች ተጠቅሰው ይገኛል፡፡ የእነዚህ ስሞች አቀራረብ የማህበረሰቡን የስም አሰያየም ለወንድ መጠሪያነት የሚጠቀመውን እንዲሁም ለሴት መጠሪያነት የሚገለገልባቸውን ስሞች መሰረት በማድረግ በመማሪያ መጽሃፎቹ ውስጥ የቀረቡትን ስሞች ተጠቅሟል፡፡

በ7ኛና በ8ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋን ለማስተማር የቀረቡትን መልመጃዎች በተደረገው ፍተሻ በመማሪያ መጽሃፎች ውስጥ ፆታ አመልካች የሆኑ ስሞች ተሰብስበው በአሃዝ ተገልጸዋል፡፡ እነዚህ በአሃዝ የተገለጹትን በመቶኛ ማስቀመጥ የተቻለ ሲሆን የወንድና የሴት ስሞች መጠን ለመለየት እነዚህ በጠቅላላ የተሰበሰቡትን ስሞች በመጠቀም የወንድና የሴት ስሞችን ሽፋን በማወዳደር ቀርቧል፡፡ በዚሁ መሰረት ፆታ አመልካች የሆኑ ስሞችን ቀጥሎ በቀረበው ሰንጠረዥ በማቅረብ ማብራሪያውም ተከትሎ ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ፡- 4.11 የስሞች አቀራረብ ከፆታ አኳያ

| የክፍል ደረጃ | ጠቅላላ የተጠቀሱ ስሞች ብዛት | የወንድ ስሞች ብዛት | | የሴት ስሞች ብዛት | | የጋራ ስሞች ብዛት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ቁጥር | በመቶኛ | ቁጥር | በመቶኛ | ቁጥር | በመቶኛ |
| 7 | 26 | 18 | 69.23 | 7 | 26.92 | 1 | 3.85 |
| 8 | 53 | 28 | 52.83 | 24 | 45.28 | 1 | 1.89 |
| ድምር | 79 | 46 | 58.23 | 31 | 39.24 | 2 | 2.53 |

በዚህ ሰንጠረዥ ውስጥ የቀረቡት ስሞች በሁለቱም ለማስተማሪያነት በተዘጋጁት መጽሃፍት ጠቅላላ የስሞች ብዛት በ7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሃፍ 26 በ8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሃፍ 53 በድምሩ 79 ስሞች ቀርበዋል፡፡ በዚሁ መሰረት በሁለቱም ክፍሎች መማሪያ መጽሃፎች ውስጥ ከቀረቡ ጠቅላላ 79 ስሞች ውስጥ 46 የወንድ ስሞች 31 ደግሞ የሴት ስሞች ናቸው፡፡ እነዚህን ስሞች በመቶኛ ስናሰላቸው ከጠቅላላ 79 ስሞች ውስጥ 58.23 በመቶ የወንድ ስሞች ሲሆኑ 39.24 በመቶ ደግሞ የሴት ስሞች ናቸው፡፡ ከመረጃው እንደምንረዳው የወንድ ስሞች 18.99 በመቶ ከሴት ስሞች ብልጫ አሳይቷል፡፡ በመሆኑም በመማሪያ መጽሃፍቱ የቀረቡት ስሞች የፆታ እኩልነትን ያላገናዘቡ እና ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን ያልጠበቁ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ ከሁለቱም መማሪያ መጽሃፍት 2(2.53) የጋራ ስሞች የቀረቡ ሲሆን ይህም የጋራ ስም ፀሐይ የሚለው ነው፡፡ አባሪ አንድን ይመልከቱ፡፡

እነዚህ ከላይ ተለይተው በመረጃነት የተሰበሰቡት ስሞች በመልመጃዎች ውስጥ የቀረቡት ብቻ ሲሆን ከዚህ ውጭ ያሉትን ስሞች አልተካተቱም፡፡ እነርሱም፡-

የመጽሃፎቹን አዘጋጆች፣ ጸሃፊዎች፣ አርታኢ፣ ገምጋሚዎች እንዲሁም ለማስተማሪያነት የቀረቡ ምንባቦች፣ ግለ-ታሪኮችና አጫጭር ጽሁፎች የደራሲያኑ ወይም የጸሃፊዎቹን ስሞች ይህ ጥናት አላካተተም፡፡

#### 4.1.6.3.2. ግሶች

የሰነድ ፍተሻው ትኩረት ካደረገባቸው በ7ኛና በ8ኛ ክፍል ተዘጋጅተው የቀረቡት በመማሪያ መጽሃፍት ውስጥ ግሶች ለማስተማሪያነት የቀረቡት ምንባቦች፣ ሀረጎች፣ ምሳሌያዊ አነጋገሮችና ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ በመግባት ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ይህ ጥናት ለየብቻ የቀረቡትን ግሶች ብቻ ከመማሪያ መጽሃፍቱ በመሰብሰብ መረጃው ተጠናክሮ በአሃዝ የተቀመጠ ሲሆን ከፆታ አኳያ ያላቸውን ሽፋን በተናጠል ከቀረቡ ግሶች የወንድና የሴት ፆታን አመልካች ግሶችን ከጠቅላላው በማስላት በመቶኛ ተቀምጧል፡፡ እነዚህም ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ በማቅረብ ማብራሪያዉም ተከትሎ ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ፡- 4.12 የግሶች አቀራረብ ከፆታ አኳያ

| የክፍል ደረጃ | ጠቅላላ ግሶች | የጋራ ግሶች | | ፆታ አመልካች ግሶች | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ወንድ | | ሴት | |
| | | ቁጥር | በመቶኛ | ቁጥር | በመቶኛ | ቁጥር | በመቶኛ |
| 7 | 37 | 4 | 10.81 | 30 | 81.08 | 3 | 8.11 |
| 8 | 25 | 6 | 24 | 17 | 68 | 2 | 8 |
| ድምር | 62 | 10 | 16.13 | 47 | 75.81 | 5 | 8.06 |

ከላይ በሰንጠረዡ ላይ ለማሳየት እንደተሞከረው በ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መጽሃፍ ውስጥ በተናጠል የቀረቡ 37 ግሶች፤ በ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መጽሃፍ ውስጥ በተናጠል የቀረቡ 25 ግሶች ናቸው፡፡ በድምሩ በሁለቱም መማሪያ መጽሃፍ ውስጥ የቀረቡት ግሶች 62 ሲሆን የጋራ ግሶች ደግሞ 10 ናቸው ፡፡ ከቀረቡት ጠቅላላ ግሶች ውስጥ የወንድ ፆታ አመልካች ግሶች 47፤ የሴት ፆታ አመልካች ግሶች 5 በድምሩ 52 ግሶች ፆታ ለይ የሆኑ ናቸው፡፡ ከተገለጹት ጠቅላላ 62 ግሶች ውስጥ 47(75.81 በመቶኛ) የሚሆኑት የወንድ ፆታ አመልካች ግሶች ሲሆኑ 5(8.06 በመቶኛ) የሚሆኑት ደግሞ የሴት ፆታ አመልካች ግሶች ናቸው፡፡ ይህም የሚያሳየን ከቀረቡት 52 ፆታ አመልካች ግሶች 42(67.74 በመቶ) የሚሆኑት የወንድ

ፆታ አመልካች ግሶች ከሴት ፆታ አመልካች ግሶች ብልጫ አላቸው፡፡ ይህ የሚያሳየን በሁለቱም መማሪያ መጽሃፎች ውስጥ የግሶች አቀራረብ የፆታ እኩልነትን ያላገናዘቡና ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን ያልጠበቁ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ አባሪ ሁለትን ይመልከቱ፡፡

#### 4.1.6.3.3. ሀረጎች

የአንድን ሀረግ የተነገረበትን ፆታ ለማወቅ የሀረጉን ግስ በማየት መለየት ይቻላል፡፡ ይህም ሲባል የሀረጉን ገላጭ ተውሳከ ግሱን በማየት መለየት ይቻላል፡፡ ጥናቱ የተካሄደባቸው የ7ኛና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ለቋንቋ ትምህርት ዓላማ መሳካት የቃላትና የሀረጋት እንዲሁም የዐረፍተ ነገር አመሰራረት ለተማሪዎቹ ማስተማሪያነት ይረዳ ዘንድ የተለያዩ ትርጉም ሊኖራቸው የሚችሉ ሀረጎች በመማሪያ መጽሃፍቱ ቀርበዋል፡፡ ነገር ግን ይህ ጥናት ለየብቻ የቀረቡትን ሀረጎች ብቻ ከመማሪያ መጽሃፍቱ በመሰብሰብ መረጃው ተጠናክሮ በአሃዝ የተቀመጠ ሲሆን ከፆታ አኳያ ያላቸውን ሽፋን በተናጠል ከቀረቡ ሀረጎች የወንድና የሴት ፆታን አመልካች ሀረጎችን ከጠቅላላው በማስላት በመቶኛ ተቀምጧል፡፡ እነዚህም በተናጠል የቀረቡት ሲባል በአዛምድ መልክ፣ ተቃራኒ ወይም ተመሳሳይ ትርጉማቸውን ፈልጉ፣ በምንባቡ ውስጥ ያላቸውን አገባባዊ ትርጉም/ፍቺ ተናገሩ/ስጡ/ግለጹ በሚል መልኩ የቀረቡትን ብቻ እንጂ በምንባብ፣ በአጫጭር ጽሁፍና ለምርጫ ጥያቄ የቀረቡትን አልተመለከተም፡፡ በዚሁ መሰረት ከሰነድ ፍተሻ የተገኙትን መረጃዎች ከዚህ በታች በቀረበው ሰንጠረዥ የተቀመጠ ሲሆን ማብራሪያዉም ተከትሎ ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ፡- 4-13 የሀረጎች አቀራረብ ከፆታ አኳያ

| የክፍል ደረጃ | ጠቅላላ ሀረጎች | የጋራ ሀረጎች | | ፆታ አመልካች ሀረጎች | | በወንድ ፆታ የተነገሩ | | በሴት ፆታ የተነገሩ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ቁጥር | በመቶኛ | ቁጥር | በመቶኛ | ቁጥር | በመቶኛ | ቁጥር | በመቶኛ |
| 7 | 108 | 3 | 2.78 | 9 | 8.33 | 8 | 7.41 | 1 | 0.93 |
| 8 | 36 | 4 | 11.11 | 10 | 27.78 | 5 | 13.89 | 5 | 13.89 |
| ድምር | 144 | 7 | 4.86 | 19 | 13.19 | 13 | 9.03 | 6 | 4.17 |

ከላይ በሰንጠረገዡ ላይ ለማሳየት እንደተሞከረው በ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መጽሃፍ ውስጥ በተናጠል የቀረቡ 108 ሀረጎች ናቸው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ 3 የጋራ ሀረጎች፣ በወንድ ፆታ የተነገሩ 8 እና  በሴት ፆታ የተነገሩ 1 ናቸው፡፡ የጋራ ሀረጎች ስንል ለወንድም ለሴትም መነገር የሚችሉ ናቸው፡፡ እነሱም፡- የክፍላችን አለቃ፣ የሰርጌ ቀንና አርብቶ አደር ናቸው፡፡ በ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መጽሃፍ ውስጥ በተናጠል የቀረቡ 36 ሃረጎች ናቸው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ 4 የጋራ ሀረጎች፣ 5 በወንድ ፆታ የተነገሩ እና 5 በሴት ፆታ የተነገሩ ሀረጎች ናቸው፡፡ የጋራ ሀረጎች ስንል ለወንድም ለሴትም መነገር የሚችሉ ናቸው፡፡ እነሱም፡- ቤተሰብ ኃላፊነት፣ የቡድን ተወካይ፣ ጎዳና ተዳዳሪና በጭንቅላቱ ባመላልስ የሚሉት ናቸው፡፡ በሁለቱም መማሪያ መጽሃፍት ውስጥ ጠቅላላ 144 ሀረጎች የቀረቡ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ የጋራ ሀረጎች 7(4.86 ከመቶ)፣ በወንድ ፆታ የተነገሩ 13(9.03 ከመቶ)ና በሴት ፆታ የተነገሩ ደግሞ 6(4.17 ከመቶ) ናቸው፡፡ ይህም እንደሚያሳየን ከቀረቡት ፆታ አመልካች ሀረጎች ከተነገሩት 7(4.86 በመቶኛ) በሴት ከተነገሩት ሀረጎች ብልጫ አለው፡፡ እነዚህ የቀረቡት ሀረጎች የፆታ እኩልነትን ያላገናዘቡና ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን ያልጠበቁ መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡ አባሪ  ሶስትን ይመልከቱ፡፡

#### 4.1.6.3.4. **ዐረፍተ ነገሮች**

*አንድ ዐረፍተ ነገር ከፆታ አኳያ ያለውን ይዘት ለመለየት ባለቤቱን ወይም ማሰሪያ አንቀጹን በማየት የትኛውን ፆታ እንደሚገልጽ ማወቅ ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽ አንድ ዐረፍተ ነገር ሲዋቀር የማይቀሩ በመሆናቸው ነው፡፡ ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገባቸው በመማሪያ መጽሃፍቱ በመልመጃ መልክ የቀረቡ እውነት ሀሰት፣ የቀረቡትን ቃላት በማስገባት ዐረፍተ ነገሩን አሟሉ፣ የቀረቡትን ዐረፍተ ነገሮች በማንበብ እርስ በእርስ አስተያየት ተሰጣጡ/ሃሳብ ተለዋወጡ/ተወያዩ/አብራሩና ተናገሩ በሚሉ መመሪያዎች አማካኝነት የቀረቡትን ዐረፍተ ነገሮች የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መገለጫ ከሆኑት ከፆታ አኳያ ያላቸውን ሽፋን ለመለየት ተሰብስበዉ በአሃዝ መልክ ቀርበዋል፡፡ የተሰበሰቡትም መረጃዎች ትንተና ተሰጥቶባቸዋል፡፡ እንዲሁም በመቶኛ ተሰልቶ ቀርቧል፡፡ ስሌቱም በመረጃነት የቀረቡ ጠቅላላ ዐረፍተ ነገሮችን መሰረት በማድረግ በፆታ የተለዩትን በመቶኛ በማስላት ተገልጸዋል፡፡ ጥናቱ የተመለከታቸው በተናጠል የቀረቡትን እንጂ በምንባብም ሆነ በአንቀጽ መልክ የቀረቡትን አልተመለከተም፡፡ እነዚህም መረጃዎች ያላቸውን ሽፋን በሚቀጥለው ሰንጠረዥ በማቅረብ ማብራሪያዉም ተከትሎ ቀርቧል፡፡*

ሰንጠረዥ፡- 4.14 በተናጠል የቀረቡ ዐረፍተ ነገሮችና የፆታ ግንኙነት ማሳያ

| የክፍል ደረጃ | ጠቅላላ የቀረቡ ዐረፍተ ነገሮች | ፆታን የማይለዩ ዐረፍተ ነገሮች | | ፆታ አመልካች ዐረፍተ ነገሮች | | በወንድ ፆታ የተገለጹ ዐረፍተ ነገሮች | | በሴት ፆታ የተገለጹ ዐረፍተ ነገሮች | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ቁጥር | በመቶኛ | ቁጥር | በመቶኛ | ቁጥር | በመቶኛ | ቁጥር | በመቶኛ |
| 7 | 138 | 120 | 86.96 | 18 | 13.04 | 16 | 11.59 | 2 | 1.45 |
| 8 | 146 | 141 | 96.58 | 5 | 3.42 | 5 | 3.42 | 0 | 0 |
| ድምር | 284 | 261 | 91.90 | 23 | 8.1 | 21 | 7.4 | 2 | 0.70 |

ከላይ በሰንጠረዡ ለማሳየት እንደተሞከረው በሁለቱም መማሪያ መጽሃፍት ውስጥ በተናጠል ከቀረቡ 284 ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ 261(91.90 በመቶኛ) የሚሆኑት ፆታን የማያንጸባርቁ ሲሆን 23(8.10 በመቶኛ) የሚሆኑት የተገለጹበትን ፆታ የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ፆታን አመልካች ከሆኑት 23(8.10 በመቶኛ) ከሚሆኑት ውስጥ 21(7.40 በመቶኛ) የሚሆኑት በወንድ ፆታ የተገለጹ ሲሆን ቀሪዎቹ 2(0.70 በመቶኛ) ደግሞ በሴት ፆታ የተገለጹ ናቸው፡፡ ከቀረቡት መረጃዎች ለመረዳት እንደተቻለው በወንድ ፆታ የተገለጹት ዐረፍተ ነገሮች 19(6.70 በመቶኛ) በሴት ፆታ ከተገለጹት ብልጫ ያሳያል፡፡ ይህ የዐረፍተ ነገሮች አቀራረብ የፆታን እኩልነት ያላገናዘበ ሆኖ ቀርቧል፡፡

በሁለቱም መማሪያ መጽሃፎች ውስጥ በአስሩም ምዕራፎች የተለያዩ መልመጃዎች ስር የሚገኙ ዐረፍተ ነገሮች የተወሰኑትን በአስረጅነት እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

አስረጅ፡- 6

በ7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሃፍ ውስጥ የቀረቡት ዐረፍተ ነገሮች

ገጽ 22 2.2 መፃፍ በሚለው ስር አያያዥ ቃላት ቀርበው ምሳሌ ስር

ሀ. ቱሉና ጫላ መጡ፡፡

ለ. ቶሎሳ ሁልጊዜ ያጠናል፤ ነገር ግን ጥሩ ውጤት አያመጣም፡፡

አስረጅ፡- 7

ገጽ 23 መልመጃ አንድ መመሪያ ቁጥር 1 ስር

1. ባዶ ቦታዎችን በተገቢ አያያዥ ቃላት በመሙላት ቀጥሎ የቀረቡትን አጫጭር ዐረፍተ ነገሮች አሟልታችሁ ፃፉ፡፡
    1. ሃሊማ ቁርሷን በልታ ወደ ትምህርት ቤት ሄደች፤ ጋዲሴ -------- አልበላችም፡፡
    2. ረቡማ በጠዋት ወደ ትምህርት ቤት ሄዷል፤ ------- ክፍል አልገባም፡፡
    3. ሕፃኑ በጣም ታሟል፡ --------- ወደ ሐኪም ቤት መሄድ አለበት፡፡
    4. ስለሺ በጣም ጎበዝ ሯጭ ነው፤ ---------- ቀነኒሳ ይቀድመዋል፡፡

5. ብዙ ስላጠናሁ ደክሞኛል፤ ------ ማረፍ አለብኝ፡፡
6. የሒሳብ ትምህርትን በጣም እወዳለሁ፤ --------- አይገባኝም፡፡
7. ከአማርኛ ንባብ -------- ከአማርኛ ንግግር የትኛው ይከብዳል?
8. በመጀመሪያ ጽሁፉን አነበበ፤ ------- ጠረጴዛው ላይ አስቀምጦ ወጥቶ ሄደ፡፡
9. ጀማል መማር ይፈልጋል፤ ወንድምዬው --------- መማር አይፈልግም፡፡
10. አበበ ዛሬ መጥቶ ነበር፤ ------ ከከበደ ጋር አልተገናኙም፡፡

በአስረጅ 6 እና 7 ስር የቀረቡትን ዐረፍተ ነገሮችን ስንመለከት አብዛኛዎቹ ጠቅላላ ከቀረቡት 12 ጥያቄዎች ውስጥ 8 (66.67 በመቶ) የሚሆኑት በወንድ ፆታ የተነገሩ ሲሆን 1(8.33 በመቶ) የሚሆነው ደግሞ በሴት ፆታ የተነገረ ነው፡፡ እነዚህ የቀረቡትን ዐረፍተ ነገሮች አቀራረባቸውን ስንመለከት በሴት ፆታ ቢነገሩ ምንም የሚያመጡት የትርጉም ለውጥ የለም፡፡ ለምሳሌ፡-

አስረጅ 6

ሀ. ቶልቱና ጫልቱ መጡ፡፡

አስረጅ፡- 7

5. ሕፃኗ በጣም ታማለች፡ --------- ወደ ሐኪም ቤት መሄድ አለባት፡፡
8. በመጀመሪያ ጽሁፉን አነበበች፤ ------- ጠረጴዛው ላይ አስቀምጣ ወጥታ ሄደች፡፡

ሌሎች የቀረቡትንም አስረጅዎች እንመልከት፡፡

አስረጅ፡- 8

ገጽ 46 መልመጃ መመሪያ ለ ስር

ለ. መምህራችሁ ሲያነቡ ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት የሚከተሉትን ሀሳቦች እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልሱ፡፡

1. ባለታሪኩ ቅቤና ወተት ይወዳል፡፡
2. የልጅነት ህይወታችን ስናድግ ለሚኖረን ህይወት አስተዋጽኦ አለው፡፡
3. የልጅነት ጊዜ ትዝታዎች አይረሴ ናቸው፡፡

4. ባለታሪኩ ወደ ትምህርት ቤት የገባው በራሱ ፍላጎት ነው፡፡
5. የባለታሪኩ የመጨረሻ ህይወት ውጤታማ አልሆነም፡፡

አስረጅ፡- 9

ገጽ 73 መልመጃ አራት መመሪያ ሀ

ሀ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች የተሰጡትን አያያዥ ቃላት በመጠቀም አያይዙ፡፡ ነገር ግን፣ እና፣ ስለሆነም፣ ቢሆንም፣ ሆኖም፣ ደግሞ

1. ጀማል ወደ ትምህርት ቤት ሄደ፡፡ አይሻ ወደ ትምህርት ቤት ሄደች፡፡
2. ፍየሎች ቅጠል ይበላሉ፡፡ ግመሎች ቅጠል ይበላሉ፡፡
3. አበበ ብዙ አያጠናም፡፡ አበበ በፈተና ጥሩ ውጤት ያመጣል፡፡
4. ተማሪዎች የመንገዱን ግራ ጠርዝ ይዘው ይሄዳሉ፡፡ መምህራን የመንገዱን ግራ ጠርዝ ይዘው ይሄዳሉ፡፡
5. ጉንፋን ተላላፊ በሽታ ነው፡፡ ቲቢ (የሳንባ ነቀርሳ) ተላላፊ በሽታ ነው፡፡
6. ነመራ ከእንቅልፉ የሚነሳው በጠዋት ነው፡፡ ነመራ ትምህርት ቤት የሚደርሰው አርፍዶ ነው፡፡
7. አልማዝ እናቷን ቀላል ቀላል ሥራዎችን በመስራት ታግዛለች፡፡ ፀሐይ እናቷን አታግዝም፡፡
8. ቀልቤሳ ትምህርት መማር አይወድም፡፡ ጀቤሳ ትምህርት መማር ይወዳል፡፡
9. አምቦ ከፊንፊኔ ይርቃል፡፡ ሰበታ ለፊንፊኔ ቅርብ ነው፡፡
10. አብደላ የሐረርን ግንብ ማየት ይፈልጋል፡፡ መሐመድ የጅማ አባ ጅፋር ቤተ መንግስትን ማየት ይፈልጋል፡፡

በአስረጅ 8 እና 9 ስር የቀረቡትን ዐረፍተ ነገሮችን ስንመለከት አብዛኛዎቹ ጠቅላላ ከቀረቡት 15 ጥያቄዎች ውስጥ 8(53.33 በመቶ) የሚሆኑት በወንድ ፆታ የተነገሩ ሲሆን 2(13.33 በመቶ) የሚሆኑት ደግሞ በሴት ፆታ የተነገሩ ናቸው፡፡ እነዚህ የቀረቡትን ዐረፍተ ነገሮች አቀራረባቸውን ስንመለከት በሴት ፆታ ቢነገሩ ምንም የሚያመጡት የትርጉም ለውጥ የለም፡፡ ለምሳሌ፡-

አስረጅ፡- 8

1. ባለታሪኩ ቅቤና ወተት ይወዳል፡፡

አስረጅ፡- 9

8. ፈይሴ ትምህርት መማር አትወድም፡፡ ቦንቱ ትምህርት መማር ትወዳለች፡፡

ሌሎች የቀረቡትንም አስረጅዎች እንመልከት፡፡

አስረጅ፡- 10

በ8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሃፍት ውስጥ የቀረቡት ዐረፍተ ነገሮች

ገጽ117ና 118 መመሪያ ሠ ጥያቄ 1-5

ሠ. ቀጥለው የቀረቡትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ክርክር መሰረት መልሱ፡፡

1. አንድ ተከራካሪ ክርክር ሊጀምር ሲል እንደ መግቢያ የሚጠቀመው ምንድን ነው?
2. ክርክሩን ሲያበቃ ምን ብሎ ይሰናበታል?
3. ታዳሚዎች የሚባሉት ምኖቹ ናቸው?
4. ዳኞቹን ውሳኔ እንዲሰጡ የሚያስችሏቸው መነሻ ነጥቦች ምን ምን ሊሆኑ ይችላሉ?
5. አንድ ተከራካሪ የተቃራኒውን ቡድን ተከራካሪ ሀሳብ የሚያጣጥለው ለምንድን ነው፡፡

አስረጅ፡- 11

ገጽ 121 መመሪያ በ

በ. በትምህርት አንድ የቀረበላችሁን ናሙና ክርክር በማስታወስ ቀጥሎ በቀረበው የመከራከሪያ ርዕስ ተከራከሩ፡፡

1. ለሃገር እድገት የበለጠ አስተዋጽኦ የሚያደርገው፤ መምህር ወይስ ወታደር?

2. ለሃገር እድገት የበለጠ አስተዋጽኦ <u>የሚያደርገው፣</u> የጤና ባለሙያ ወይስ የትምህርት ባለሙያ?

በአስረጅ 10 እና 11 ስር የቀረቡትን ዐረፍተ ነገሮችን ስንመለከት አብዛኛቹ ጠቅላላ ከቀረቡት 7 ጥያቄች ውስጥ 5(71.43 በመቶ) የሚሆኑት በወንድ ፆታ የተነገሩ ሲሆን በሴት ፆታ የተነገረ ምንም ዐረፍተ ነገር የለም፡፡ እነዚህ የቀረቡትን ዐረፍተ ነገሮች አቀራረባቸውን ስንመለከት በሴት ፆታ ቢነገሩ ምንም የሚያመጡት የትርጉም ለውጥ የለም፡፡ ለምሳሌ፡-

አስረጅ፡- 10

2. ክርክሩን ሲያበቃ ምን <u>ብላ ትሰናበታለች</u>?

አስረጅ፡- 11

2. ለሃገር እድገት የበለጠ አስተዋጽኦ <u>ማድረግ የምትችለው፣</u> የጤና ባለሙያ ወይስ የትምህርት ባለሙያ?

ከዚህ ዐረፍተ ነገር የምንረዳው ለወንድ ፆታ ያደላ መሆኑን እና ለሴት ፆታ የተሰጠው ትኩረት እምብዛም መሆኑን ያሳየናል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በአስረጅ 6 - 11 የቀረቡት 34 ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ 21(61.76 በመቶ) የሚሆኑት በወንድ ፆታ የተነገሩ ሲሆን ከቀረቡት ውስጥ 3(8.82 በመቶ) የሚሆኑት ደግሞ በሴት ፆታ የተነገሩ ዐረፍተ ነገሮች ናቸው፡፡ ከላይ የቀረቡት ዐረፍተ ነገሮች የፆታ እኩልነትን በጠበቀ መልኩ ቢዘጋጁ ማስተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት ይዘት ሳይለወጥ ማዘጋጀት ይቻላል፡፡ ይህንም ከላይ በአስረጅ ስር በቀረበው ምሳሌ መሰረት በሴት ፆታ አመልካች ቢቀርብ ምንም ዓይነት የትርጉም ለውጥ እንደሌለው ለማየት ተችሏል፡፡ ይህ አቀራረብ ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን በጠበቀ መልኩ እንዳልቀረበና ማስተካከያ ቢደረግበትና ቢቀርብ የተሻለ መሆኑን ያሳየናል፡፡

## 4.2. የውጤት ማብራሪያ

አጥኚው በ7ኛና በ8ኛ ክፍል በኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ አዘጋጅነት አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ ማስተማሪያነት 2009 ዓ/ም የተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሃፎች የመማር ማስተማሩን ሂደት ውጤታማ ለማድረግ ይረዳሉ ተብለው የተዘጋጁት ምንባቦች፣ መመሪያዎችና መልመጃዎች አቀራረብ ከባህል፣ ከሃይማኖትና ከፆታ አኳያ ምን ያህል ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነታቸውን ጠብቀው እንደተዘጋጁ ለመለየት አጥኚው ባደረገው የሰነድ ፍተሻ አጠቃላይ የተገኘውን መረጃ በሁለቱም መማሪያ መፃህፍት 55 ምንባቦች የቀረቡ ሲሆን፤ ከእነዚህ ውስጥ 13(23.64 በመቶ) የሚሆኑት ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን የሚያንጸባርቅ ወይም የሚዳስስ ጽንሰ ሃሳብ ያላቸውና ትኩረት የሰጡ መሆኑ ከጥናቱ ውጤት ማወቅ ተችሏል፡፡ ከዚህ ውስጥ 7(12.73 በመቶ) የተለያየ መልዕክት ያላቸው የቀረቡት ምንባቦች የማህበረሰቡን ባህል ያላገናዘቡና ያልጠበቁ ወይም ማህበረሰቡ ብዙም የማይቀበላቸው ናቸው፡፡ ይህም በቡድን መከፋፈልንና ያልተፈለገውን ማግለልን የሚያንጸባርቅ ሃሳብ ያላቸው በመሆኑ ለማስተማሪያነት የሚዘጋጁት ምንባቦች የተማሪውን ባህላዊ ዳራ ያገናዘቡና ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን በጠበቀ መልኩ ቢዘጋጁ የተሻለ ይሆናል፡፡ በመማሪያ መጽሃፍቱ ለማስተማሪያነት የቀረቡት መልመጃዎች የሚሰሩት በመመሪያዎች አማካይነት ሲሆን የቀረቡት መመሪያዎች ባህላዊ ይዘት የሌላቸው መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ እንዲሁም በመጽሃፍቱ የቀረቡት መልመጃዎች በስራቸው ከሚገኙት ጥያቄዎች ውስጥ ከማህበረሰቡ ባህል አኳያ ተገቢነት የሌላቸው 5 ጥያቄዎች መቅረባቸው አግባብ ባይሆንም እንደ ጥያቄዎቹ ብዛት በጣም ጥቂት ስለሆኑ የተዘጋጁት መልመጃዎች ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን በከፊል በጠበቀ መልኩ የተዘጋጁ ናቸው ማለት ያስችላል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የመማር ማስተማር ሂደቱን ከግብ ያደርሳሉ ተብለው ከተዘጋጁት ውስጥ ከሃይማኖት አኳያ የምንባቦች፣ የመመሪያዎችና የመልመጃዎች አቀራረብ በተደረገው ፍተሻ በሁለቱም መማሪያ መጽሃፍት ውስጥ በግብዓትነት ከቀረቡት ምንባቦች ውስጥ ያለውን ሽፋን ለመለየት በተደረገው የሰነድ ፍተሻ በ8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሃፍ ውስጥ ሰለአንዲት ታዋቂ ሴት አስቴር ገኖ የሚባሉ የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ ለማሳደግ ያደረጉትን የትርጉም ስራ በሰፋት ያብራራ ሲሆን ይህም ከትርጉም ስራቸው መሃከል የኃይማኖት መጽሃፍ የሆኑትን አዲስ ኪዳን፣ የእግዚአብሔር ምህላና መጽሐፍ ቅዱስን እንደተረጎሙ

በምንባቡ ውስጥ ተብራርቷል፡፡ ይህ ለማህበረሰቡ ያበረከቱት ትልቅ ስራ እሰየው የሚያሰኝ ቢሆንም ከተማሪዎቹ ዳራ አኳያ ሃይማኖት አመልካች የሆኑ ስራዎች ባይቀርቡ የተሻለ መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡ እንዲሁም የመመሪያዎችና መልመጃዎች አቀራረብ ላይ በተደረገው ፍተሻ ምንም ዓይነት ነገር ከኃይማኖት ጋር ሊያያዝ የሚችል ይዘት እንደሌለ ለማወቅ ተችሏል፡፡ የስሞች አቀራረብ ከኃይማኖት አኳያ ያለውን ሽፋን ለመለየት በተደረገው ዳሰሳ የክርስትና ስም 18.99 በመቶ ከእስልምና ኃይማኖት ብልጫ እንዳለው የሚያሳይ በመሆኑ የስሞች አቀራረብ ለክርስትና ኃይማኖት ያደላ መሆኑን አጥኚው ተገንዝቧል፡፡ በአጠቃላይ የመመሪያዎችና መልመጃዎች ከኃይማኖት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ይዘቶች አሉ ለማለት ባያስደፍርም ከስም አቀራረብ አኳያ ግን ፍትሃዊነት የጎደለው ነው፡፡ በመሆኑም ከኃይማኖት አንፃር የመመሪያዎችና የመልመጃዎች አቀራረብ ፍትሃዊነትና ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን በጠበቀ መልኩ የተዘጋጁ መሆኑን አጥኚው ተረድቷል፡፡

በሶስተኛ ደረጃ የዚህ ጥናት ትኩረት የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መገለጫ ከሆኑት ከፆታ አኳያ የሁለቱም መማሪያ መጽሃፍት ያላቸውን ሽፍን ለማወቅ መገለጫዎቹ ትኩረት ያደረገባቸው በግብዓትነት የቀረቡት ስሞች፣ ግሶች፣ ሀረጎች፣ ዐረፍተ ነገሮችና ምንባቦች(ግለ-ታሪኮች) አቀራረብ ሲሆን ከዚህም የተገኘው ውጤት ከቀረቡት ግለ-ታሪክ አዘል ምንባቦች 5 ሲሆኑ ከነዚህ ውስጥ 3(60 በመቶኛ) የሚሆኑት የሴቶችን ታሪክ ያዘሉ ሲሆን 2(40 በመቶኛ) ደግሞ የወንዶችን ታሪክ ያዘሉና 20 በመቶ የሴት ፆታ ብልጫ ያሳየ ነው፡፡ የመመሪያዎች አቀራረብ 1.87 በመቶኛ የመልመጃዎችን አቀራረብ ስናይ የስም አቀራረብ ከፆታ አኳያ 18.99 በመቶኛ የወንድ ብልጫ ያሳየ፣ የግሶች አቀራረብ 67.74 በመቶኛ የወንድ ፆታ ብልጫ ያሳየ፣ የሀረጎች አቀራረብን ስናይ 4.86 በመቶኛ አሁንም የወንድ ፆታ ብልጫ ያሳየና የዐረፍተ ነገሮች አቀራረብ ደግሞ አሁንም 6.70 በመቶኛ የወንድ ፆታ ብልጫ አሳይቷል፡፡ በዚህ ጥናት የተገኘውን አጠቃላይ ውጤት ስንመለከት በአማካይ 20.03 በመቶኛ የወንድ ፆታ አመልካች ብልጫ እንዳለው በተደረገው ፍተሻ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን የፆታ እኩልነትን ያላገናዘበና ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ከፆታ አኳያ ትኩረት ያልተሰጠው መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ ቀደምት በተደረጉት ጥናቶች በፍቃዱ እንዳለ(2012) የህብረ-ባህላዊነትን ከማስረጽ ረገድ መገለጫ ከሆኑት የብሔር ስምና ከፆታ አንፃር ሲሆን የጥናቱ ውጤትም

እንደሚያሳየው የወንድ ፆታ አመልካች ስሞች 23 በመቶኛ ብልጫ እንዳለውና ለወንድ ፆታ ያደላ መሆኑን የተገኘው ውጤት ያሳያል፡፡ በዚህኛው ጥናት የተገኘው ውጤት ከላይ እንደተገለጸው ከባህል፣ ከሃይማኖትና ከፆታ አኳያ ጥናት የተደረገ ሲሆን በተገኘው ውጤትም 7(12.73 በመቶ) የሚሆኑት ባህልን ያልተበቁ ሆኖ ተገኝተዋል፡፡ ከሃይማኖት አኳያ አንድ ምንባብና አንድ ምሳሌያዊ አነጋገር ከተማሪዎቹ ዳራ አንፃር መታየት ቢኖርበትም ከጠቅላላው ይዘት አኳያ መልካም እንደሆነ የተገኘው ውጤት ያሳረዳል፡፡ ቀደምት በተደረገው ጥናት በፍቃዱ እንዳለ በጥናቱ ያልተካተቱ በመሆናቸው ከፆታ አንፃር በተደረገው ጥናት የዚህኛው አማካይ ውጤት 20.03 በመቶኛ የወንድ ፆታ አመልካች ብልጫ ያለው ነው፡፡ የሁለቱም ጥናት ውጤት ከፆታ አኳያ የተገኘው ውጤት ተቀራራቢ በመሆኑ የፆታ እኩልነት ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ስሞች፣ ግሶች፣ ሀረጎችና ዐረፍተ ነገሮች ለማስተማሪያነት በሚዘጋጁበት ውቅት ትኩረት ሊደረግባቸው ይገባል፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት ውጤት የጥናቱን ዓላማ ያሳካሉ ተብለው የቀረቡትን መሪ ጥያቄዎች መሰረት በማድረግ ክፍተቱን ይሞላሉ ተብለው የቀረቡት የህብ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መገለጫ ከሆኑት ከባህልና ከኃይማኖት አኳያ ክፍተቱን ሞልቷል፡፡

# ምዕራፍ አምስት፤ ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና የመፍትሄ ሃሳብ

## 5.1. ማጠቃለያ

ይህ ክፍል በኦሮሚያ ክልል አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች ማስተማሪያነት በ2009 ዓ/ም የተዘጋጁት የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሃፍት ለህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት የሰጡትን ትኩረት መፈተሽ ዓላማው በማድረግ የተሰራው ጥናት ክፍተቶችን ይሞላል በሚል ታሳቢነት የተካሄደ ነው፡፡ ከጥናቱ የተገኘው ውጤት መረጃው የተሰበሰበው(የተቀናጀው) ከህብ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መገለጫ ከሆኑት ከባህል፣ ከሃይማኖትና ከፆታ አኳያ ሲሆን ትኩረት ካደረገባቸው ከምንባቦች፣ ከመመሪያዎችና ከመልመጃዎች አቀራረብ አንፃር መረጃዎቹ ተሰብስበው በገላጭና እስታስቲካዊ ዘዴ ትንተና ተሰጥቶባቸዋል፡፡

ጥናቱ በተካሄደባቸው የ7ኛና የ8ኛ ክፍል የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የማስተማሪያ ግብዓት ከሆኑት ምንባቦች፣ መመሪያዎችና መልመጃዎች ምን ያህል ለህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ትኩረት እንደሰጡ በተደረገው ፍተሻ የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው በሁለቱም መማሪያ መጽሃፍትና የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር ይረዳሉ ተብለው በመምህሩ መምሪያ የቀረቡት ምንባቦች በጥቅሉ 55 ሲሆኑ ከእነዚህ ውስጥ 13(23.64 በመቶ) የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ፅንሰ-ሃሳብ ያላቸው ሲሆኑ 7(12.73 በመቶ) የሚሆኑት ደግሞ ከማህበረሰቡ ባህልና ልማድ ያልጠበቁ ሃሳብ ያላቸው በመማሪያ መጽሃፎቹ ውስጥ እንዳሉ የተገኘው ውጤት ያሳያል፡፡ የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ጽንሰ-ሃሳብ ያላቸው ምንባቦች መቅረባቸው አግባብነት ያለውና የተማሪዎቹን ዳራ የጠበቀ መሆኑና አቀራረቡም ለህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት የተሰጠውን ትኩረት ጥሩ እንደሆነ ከጥናቱ ውጤት ለማወቅ ተችሏል፡፡ ከጠቅላላው ውስጥ የማህበረሰቡን ባህልና ልማድ ያልጠበቁ ምንባቦች ከሚያስተላልፉት መልዕክት አኳያ ባህልን ያላገናዘቡና ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን ያልጠበቁ መሆናቸው የጥናቱ ውጤት ጠቁሟል፡፡

ከጥናቱ ውጤት እንደተገኘው አንዳንድ ጥያቄዎች ለመወያየትና ሃሳብን ለመስጠት ይረዳሉ ተብለው የቀረቡ ጥያቄዎች ውስጥ አልፎ አልፎ አንዳንድ ዐረፍተ ነገሮች የቀረቡ ሲሆን እነዚህ የቀረቡት ጥያቄዎች ባህልን ያልጠበቀ ሃሳብ የሚያንጸባርቁ

መሆናቸውን ከውጤቱ መረዳት የተቻለ ቢሆንም ለህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት የተሰጠው ትኩረት ክፍተት እንዳለበት የሚያሳይ ነው፡፡

በሁለቱም መማሪያ መጽሃፍት ውስጥ ከቀረቡት የማስተማሪያ ግብዓቶች መመሪያዎችና መልመጃዎች ምን ያህል ባህላዊ ይዘት እንዳላቸውና ከማህበረሰቡ ባህልና ወግ ተቃራኒ ሃሳብ ያላቸው የተወሰኑ ጥያቄዎችን ለማየት ቢቻልም ከጠቅላላው አቀራረብ አኳያ በከፊል መልካም እንደሆነ ታይቷል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ለህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መኖር ምክንያት ከሆኑት ውስጥ ምንባቦች፣ መመሪያዎችና መልመጃዎች ከኃይማኖት አኳያ ያላቸውን ሽፋን ለመለየት በተደረገው ፍተሻ የተገኘው ውጤት ከቀረቡት 55 ምንባቦች ውስጥ አንድ ምንባብ የክርስትና ኃይማኖት አመልካች የሆኑ ሃሳቦች የያዘ መሆኑ የታየ ሲሆን መመሪያዎች ግን ምንም ዓይነት ኃይማኖትን አመልካች የሆነ ሃሳብ እንደሌለባቸውና በመልመጃዎች ውስጥ ግን አንድ ምሳሌያዊ አነጋገር ከክርስትና ሃይማኖት ጋር ተያያዥነት ያለው ሃሳብ የቀረበ ሲሆን የቀረበውም ሃሳብ ለማስተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት ማስተላለፍ እንዲችል ከኃይማኖታዊ ሃሳብ ውጪ የሆነ ቢሆን ወይም የጋራ የሆነ ሃሳብ ያለውን መጠቀም ቢቻል የተሻለ መሆኑ ታይቷል፡፡

በሶስተኛ ደረጃ ለህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መገለጫ ምክንያት ከሆኑት ውስጥ ከፆታ አኳያ የምንባቦች፣ መመሪያዎችና መልመጃዎች አቀራረብ ያላቸውን ሽፋን ለማየት በተደረገው ፍተሻ ለዚህ ጥናት ትኩረት የተደረገባቸው ግብዓቶች መመሪያዎች፣ ስሞች፣ ግሶች፣ ሀረጎች ዐረፍተ ነገሮችና ምንባቦች(ግለ-ታሪኮች) ሲሆኑ በተገኘውም አማካይ ውጤት 20.03 በመቶ የቀረቡት የወንድ ፆታ ብልጫ ያለው መሆኑ ታውቋል፡፡ ይህ ደግሞ የፆታ እኩልነትን ያልጠበቀና ለወንድ ፆታ ያደላ መሆኑን ከተገኘው ውጤት ለማወቅ ተችሏል፡፡

## 5.2. መደምደሚያ

በዚህ ክፍል የጥናቱን ዓላማ መሰረት በማድረግ አጥኚው ይዟቸው ከተነሳው መሪ ጥያቄዎችና በተገኘው ውጤት በኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ አዘጋጅነት በ2009 ዓ/ም የተዘጋጁት የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሃፍት ህብረ-ባህላዊነትና

ብዝሃነትን ትኩረት ከመስጠት አንፃር መገለጫ ከሆኑት ከባህል፣ ከኃይማኖትና ከፆታ አኳያ የተገኘውን ውጤት መሰረት በማድረግ የሚከተሉት መደምደሚያዎች ተሰጥተዋል፡፡

- በ2009 ዓ/ም የታተሙት የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መጽሃፍት አጠቃላይ አዘገጃጀት መልካም ነው፡፡
- በሁለቱም መማሪያ መጽሃፍት ውስጥ ለህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት የሰጡትን ትኩረት ለመለየት መገለጫ ከሆኑት ከባህል አኳያ የምንባቦች፣ መመሪያዎችና መልመጃዎች አቀራረብ በተደረገው ፍተሻ በቀረቡት ምንባቦች ውስጥ ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ጽንሰ-ሃሳብ የሚያንጸባርቁ ምንባቦች ተካተዋል፡፡
- በመማሪያ መጽሃፍቱ የቀረቡት መመሪያዎች ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነትን የጠበቁ ናቸው፡፡
- የቀረቡት መልመጃዎች ከባህል አንፃር መጠነኛ ችግር ያለባቸው ናቸው፡፡
- ከኃይማኖት አንፃር ለማስተማሪያነት የቀረቡት ምንባቦች፣ መመሪያዎችና መልመጃዎች በተደረገው ፍተሻ የቀረቡት ምንባቦች ውስጥ አንድ ምንባብ ኃይማኖታዊ ሃሳብ ያለው መሆኑ ታይቷል፡፡
- መመሪያዎቹ ኃይማኖታዊ ይዘት ያልታየባቸው ናቸው፡፡
- መልመጃዎች የስሞች አቀራረብ ከህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መገለጫ ከሆነው ከኃይማኖት አኳያ ለወንድ ፆታ ያደሉ ናቸው፡፡
- ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መገለጫ ከሆነው ከፆታ አኳያ ጥናቱ ትኩረት ካደረገባቸው ስሞች፣ ግሶች፣ ሀረጎችና ዐረፍተ ነገሮች የተገኘው ውጤት ለወንድ ፆታ ያደሉ ናቸው፡፡
- በመማሪያ መጽሃፍቱ የተሻለ ህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት አቀራረብ ያላቸው መገለጫው ከሆኑት ባህልና ኃይማኖት ሲሆን የህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መገለጫ የሆነው ከፆታ አኳያ የፆታ እኩልነትን ያልጠበቀ ነው፡፡

## 5.3. የመፍትሄ ሃሳብ

አጥኚው ከዚህ ጥናት ጋር በተያያዘና ከጥናቱ ውጤትም ካገኘው መረጃዎች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሃፍት ዝግጅት ወቅት ማሻሻያ ለማድረግ የይዘት መረጣ ስራ ላይ

ለተሰማሩት ባለሙያዎች በዝግጅት ወቅት ከህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት ጋር በተገናኙ ጉዳዮች ትኩረት ቢደረግባቸው የሚለውን አስተያየቶች እንደሚከተለው አቅርቧል፡፡

- በመማሪያ መጽሃፍቱ ዝግጅት ወቅት ከህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መገለጫ ከሆነው ከባህል አንፃር ምንባቦችና መልመጃዎች ትኩረት ቢደረግባቸው፤
- በመማሪያ መጽሃፍቱ ይዘት መረጣ ወቅት ከህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መገለጫ ከሆነው ከኃይማኖት አንፃር ምንባቦች(ግለ-ታሪኮች) ትኩረት ቢደረግባቸው፤
- በመማሪያ መጽሃፍቱ ዝግጅት ወቅት ከህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መገለጫ ከሆነው ከፆታ አንፃር ምንባቦች፣ መመሪያዎችና መልመጃዎች ትኩረት ቢደረግባቸው፤
- በመማሪያ መጽሃፍቱ ዝግጅት ወቅት ከህብረ-ባህላዊነትና ብዝሃነት መገለጫ ከሆኑት ከባህል፣ ከሃይማኖትና ከፆታ አንፃር ይዘታቸው ሚዛናዊነትን በጠበቀ መልኩ ቢዘጋጅ፤ መልካም ነው የሚሉት ናቸው፡፡

## ዋቢ ጽሁፎች


ሂሩት ካሳው፡፡(2006)፡፡ "በከፍተኛ ትምህርት ተቋም መምህራን የሚታዩ ስርዓተ ፆታዊ ዲስኩር ትንተና በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ መነሻነት፡፡" ለዶክተሬት ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡(ያልታተመ)፡፡

ሰለሞን ፍስሐ፡፡(2011)፡፡ "የባህለ ብዙነትን ግንዛቤ ማስጨበጫ ይዘት ፍተሻ በ9ኛ እና በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ተተኳሪነት፡፡" ለድህረ ምረቃ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ፡፡ ጅማ ዩኒቨርሲቲ፡፡(ያልታተመ)፡፡

በተባበሩት መንግስታት ዓለም አቀፍ ሰነዶች፡፡(1982)፡፡ ሰብአዊ መብቶች የሚመለከቱ ዓለም አቀፍ ሰነዶች፡፡ አዲስ አበባ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

በፍቃዱ እንዳለ፡፡(2012)፡፡ "በኦሮሚያ ክልል ለ7ኛ እና ለ8ኛ ክፍል የተዘገጁት የአማርኛ መማሪያ መጽሐፎች ህብረ-በህላዊነትን በማስረጽ ረገድ ያላቸውን አስተዋጽዖ ፍተሻ፡፡" ለድህረ ምረቃ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ፡፡ ጅማ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ቤተልሄም ከበደ፡፡(2011)፡፡ "የብዝሃ ባህላዊነት ጭብጦች በዘጠነኛ እና በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ተተኳሪነት፡፡" ለድህረ ምረቃ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ፡፡ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

አንበሳው ፈንታ፡፡(2009)፡፡ "የብዝሃ-ባህላዊነት አቀራረብ ፍተሻ በሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ተተካሪነት፡፡" ለድህረ ምረቃ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ፡፡ ጅማ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ክፍሌ ዳመነ፡፡(2011)፡፡ "የሰዋሰው ክፍለ ትምህርት ይዘት ከጾታ አንጻር ያላቸዉ ህብረ ባህላዊ አቀራረብ ፍተሻ፡፡" ለድህረ ምረቃ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ፡፡ ጅማ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት**፡፡(1987)፡፡

የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ፡፡(2009)፡፡ **አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ 7ኛ ክፍል**፡፡

የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ፡፡(2009)፡፡ **አማርኛ እንደሁለተኛ ቋንቋ የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ 8ኛ ክፍል**፡፡

ያለው እንዳወቅ፡፡(2009)፡፡ **የምርምር መሰረታዊ መርሆዎች አተገባበር**፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

Banks,J A., & Banks, C. A. M. (Eds.). (2004). **Handbook of research on multicultural education** (2nd ed.). SanFrancisco: Jossey-Bass.

Banks J.A.,(2006).**Multicultural Education and Knowledge Construction**. In J.A.Banks(Ed), Race, culture and education: The selected works of Jamses A. Banks (pp.127,164). London: Routledge.

Banks, J. A.,(2010). **Multicultural Education: Characteristics and Goals.** In J. A. Banks & Cherry A. McGee Banks (Eds.), Multicultural Education: Issues and Perspectives. Hoboken, NJ: John Wiley & Sons, Inc. 3-32

Campbell, Duane. (2010).**Choosing Democracy: a practical guide to Multicultural Education.** 4th.edition. Pearson, Allyn /Bacon

Fenwick,L.(2011). **Curriculum reform and reproducing inequality in upper-secondary education.** Journal of Curriculum Studies, 43(6):697-716.

Race, Richard.(2011). **Multiculturalism and Education.** London: Continuum International Publishing Group

Ramsey, Patricia G. and Leslie R.Williams. (2003). **Multicultural Education: A Source Book** (second edition) New York: RoutledgeFalmer.

Scherba de Valenzuela, Julia. 2011. **Defining Multicultural Education.** Online: http://www.unm.edu/~devalenz/handouts/nieto2.html.

Taylor, C (1994). **Multiculturalism–Examing the politics of Recognation**. Princeton University press.

The World Book Encyclopedia (2001). **Printed in United Stetes of America**, Chicago.Volume 4.

Tomlinson, B. (2003). **Materials Evaluation.** In Tomlinson, B. (ed). Developing Materials for Language Teaching. London and New York: Continuum.

# አባሪዎች

## አባሪ አንድ

## የስሞች ቀራረብ ከኃይማኖትና ከፆታ አኳያ

<u>7ኛ ክፍል</u>

- ጫልቱ
- ቱሉ
- ጫላ
- ቶሎሳ
- ሀሊማ
- ጀማል
- ጋዲሴ
- ረቡማ
- ስለሺ
- ቀነኒሳ
- አበበ
- ከበደ
- አልማዝ
- ፀሐይ
- አይሻ
- አብደላ
- መሐመድ
- ቀልቤሳ
- ጀቤሳ
- ቤካ
- ገነሞ
- ቶለሺ
- ኑሬ
- አብዲሳ
- ገመቹ
- ነመራ

8ኛ ክፍል

- ካሳ
- አያንቱ
- ቀልቤሳ
- ሶራ
- ጫላ
- ሌሊሳ
- ጋዲሴ
- ፈይሴ
- ኩለኒ
- ባይሳ
- ነገዎ
- ገለታ
- ለሊሴ
- ጫልቱ
- ለሜሳ
- አቤል
- ዋሪቴ
- ጀቤሳ
- ገቢሳ
- ቦንቱ
- ጂቱ
- ፈይሳ
- ደራርቱ
- ብርሃኔ
- ጌጤ
- ጥሩነሽ
- አበበች

- ሀሎ
- አስቴር
- እልፍነሽ
- ዲንቦ
- ኦነስሞስ
- ሊዲያ
- ፌበን
- ዶ/ር ባርቴስ
- ሂካ
- ጃለኔ
- ቃበታ
- መረርቱ
- ኩሜ
- ቶላ
- ዋቆ
- ወዬሳ
- ሶሪ
- አሰፋ

**አባሪ ሁለት**

**የግሶች አቀራረብ ከዖታ አኳያ**

<u>7ኛ ክፍል</u>

- መጠነ
- መጣ
- ጠጣ
- ሰራላቸው
- በላ
- አለ

- ወፈረ
- አነበበ
- ቆረጠ
- ጠበቀ
- ሰጠ
- ቀረ
- መራ
- ሰባ
- ቀና
- ሳለ
- ጋለበ
- ፈነጨ
- ቀኘ
- አመነ
- ይተጋል
- ሄደ
- ገጠመ
- ረገጠ
- ለካ
- ራቀ
- ታሚል
- ይረታል
- ሄደች
- አገሳ
- ካደው
- እወዳለሁ
- እነባለሁ
- ተነጠለች
- አልበላችም

- ይገነባሉ
- ያጋልጣል

<u>8ኛ ክፍል</u>

- ያድጋል
- ይቀንሳል
- ተገነዘበ
- ይበለጽጋል
- ይቀየራል
- ይሻክራል
- አወቀ
- ይገታል
- ይቀጥፋል
- አጠቃ
- ተሰራጨ
- ጠፋ
- ተቀጨ
- ተሰወረ
- ተለቀመ
- ሰደበ
- በረበረ
- ፃፈ
- መታ
- ተጠመቀ
- ተጣለ
- ከነከናት
- ቆጫት
- አደገ
- ተራባ

**አባሪ ሶስት**

**የሀረጎች አቀራረብ ከያታ አኳያ**

<u>7ኛ ክፍል</u>

- ታታሪው ገበሬ
- ጎበዙ ተማሪ
- የልብስ ነጋዴው
- መስማት ለተሳነው
- ማየት ለተሳነው
- መንቀሳቀስ ለማይችል
- መናገር ለማይችል
- ዙሪያውን ተመለከተ
- ሴቶችን ማክበር

<u>8 ኛ ክፍል</u>

- አንድ ጎበዝ ተማሪ
- አባሮ የሚይዝ
- ሮጦ የሚያመልጥ
- ምርጥ ዘር ይዘራል
- መቼ ትመጣለህ?
- ጤንነቷ የተጠበቀ ወጣት
- ተመራማሪዋ መምህር
- ተወዳጁ ዘፋኝ
- ተሸላሚዋ ገበሬ
- ታዋቂዋ ሯጭ

# አባሪ አራት

የጽሑፍ ዋና ሐሳብ

- የጽሑፍ ዋና ሐሳብ የጽሑፉን አጠቃላይ ሐሳብ የያዘ ነው።
- ዋናው ሐሳብ በጽሑፉ ማስተላለፍ የተፈለገው መልዕክት ነው።
- አንድ ጽሑፍ ዋናውን ሐሳብ ከያዘ ዐረፍተ ነገርና ይህንን ሐሳብ ለማብራራት ከሚቀርቡት ዐረፍተ ነገሮች ይመሰራታል።
- ዋናውን ሐሳብ ለማብራራት የሚቀርቡት ዐረፍተ ነገሮች በቅደም ተከተል ይቀርባሉ።
- ዋናው ሐሳብና ዋናውን ሐሳብ ለመደገፍ የሚጻፉት ዐረፍተ ነገሮችም በሚገባ ውህደት ፈጥረው ይጻፋሉ።

## ተግባር ሁለት

ውጥን ታሪክን አሟልቶ መጻፍ

ውጥን ታሪክን ማሟላት ማለት ሐሳቡ ያላለቀውን ታሪክ በማሟላት ጨርሶ መፃፍ ማለት ነው። አንድ ውጥን ታሪክ በተለያየ መንገድ ሊያልቅ ይችላል። ነገር ግን ታሪኩ የሚያልቅበት መንገድ ታሪኩ ሲጀመር ከነበረው ሐሳብ ጋር መስማማት ይኖርበታል። ከጅምር ሐሳቡ የተለየ መሆን የለበትም።

ምሳሌ፦

በድሮ ጊዜ ዝንጀሮና አይጥ ጓደኛማማቾች ነበሩ። የሚኖሩትም በአንድ ቤት ውስጥ ነበር። ከዚያም አብረው ለማምረትና ያመረቱትንም እኩል ለመካፈል ተስማሙ። በዚህም መሠረት እርሻ አርሰው ስንዴ ዘሩ። አብረውም አረሙ። ስንዴው በደረሰ ጊዜም አጭደው፤ ከምረውና ወቅተው ወደ ቤታቸው አጋዙ።

ለስንዴውም ማስቀመጫ ትልቅ ድብኝት ሠሩና ቁልፍ አበጁለት። ስንዴውንም ድብኝቱ ውስጥ ጨመሩትና ድብኝቱን ቆልፈው መክፈቻውን ዝንጀሮ እንዲይዝ ተደረገ። አይጥ የቁልፉ መክፈቻ ዝንጀሮ እጅ መሆኑን አውቃ ስንዴውን መብላት የምትችልበትን ዘዴ አሰበች። ከዚያም መሬቱን ቆፍራ ድብኝቱ እንደተቀመጠ ከሥሩ ሽንቁራ መብላት ጀመረች። ቀስ በቀስም ግማሹን እህል በልታ የተቀረውን ደግሞ ጉድጓዷ ውስጥ እንዲፈስ አድርጋ ከድብኝቱ ውስጥ ጨረሰች።

ቆይቶም አንድ ቀን ዝንጀሮ አይጧን ስንዴውን መካፈል እንዲችሉ ጠየቃት።

አይጧም የሠራችው ተንኮል እንደማይታወቅባት አስባ በጥያቄው ተስማማች፡፡ በስምምነታቸውም መሠረት ስንዴውን ለመካፈል ዝንጀሮ መክፈቻውን አውጥቶ ድብኝቱን ከፈተው፡፡ በውስጡም ምንም ስንዴ አልነበረም፡፡ ሁለቱም በጣም ደነገጡ፡፡ አይጧም ከዝንጀሮው በባሰ የተናደደች በማስመሰል "የድብኝቱ መክፈቻ ያለው አንተ እጅ ነው! ስንዴውን በልተህ ከጨረስህ በኋላ መልሰህ ቆለፍከው፡፡ እኔም እፋረድሃለሁ" አለችው፡፡

የዝንጀሮውና የአይጧ ታሪክ አላለቀም፡፡ በውጥን ወይም በጅምር ያለ ታሪክ ነው፡፡ ይህንን ታሪክ በተለያዩ መንገዶች መጨረስ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ ታሪኩ ሊያልቅ ከሚችልባቸው መንገዶች አንዱ የሚከተለው ነው፡፡

በመጨረሻም ጉዳዩን መርምረውና አጣርተው ፍርድ እንዲሰጡዋት አቤቱታዋን ለዱር አራዊት ሽማግሌዎች አቀረበች፡፡ አራዊቱም እውነታውን በማጣራት ጥፋተኛውንም ለመቅጣት ብዙ ጥረት አደረጉ፡፡ ነገር ግን ጥፋተኛውን መለየት አልቻሉም፡፡ ሽማግሌዎቹም "ኃጢአት ያልሰራው በንጽህናው ይውጣ፤ ጥፋተኛም ለጥፋቱ ቅጣቱን ይቀበል፡፡ ስለዚህ ጉዳዩን በመሃላ እናጣራለን፤ በዚህም እንወስናለን በማለት በመሃላ ለማጣራት ተስማሙ፡፡"

## መልመጃ ሁለት

1. የሚከተለውን ውጥን ታሪክ አሟልታችሁ ጻፉ፡፡

ወቅቱ ክረምት ነው፡፡ በክረምት ወራት በአካባቢያችን ሁል ጊዜ ከሰዓት በኋላ ከባድ ዝናብ ይጥላል፡፡ ከርቀት የሚታየው የጭላሎ ተራራ ቡልኮ ተከናንቦ የተቀመጠ ሽማግሌ መስሏል፡፡ ጭላሎ ተራራ በጥቁር ደመና ከተሸፈነ ከጥቂት ሰዓታት በኋላ በአካባቢያችን ከፍተኛ ዝናብ እንደሚዘንብ ይታወቃል፡፡

በክረምት ወራት ትምህርት ቤቶች ሲዘጉ የአካባቢያችን ልጆች ዋና ሥራ ከብት ማገድ ነው፡፡ ከብቶችንም የሚያግዱት ከመንደራችን ራቅ ብሎ ከሚገኘው ሸለቆ ማዶ በተንጣለለው ሰፊ መስክ ላይ ነው፡፡ በአካባቢያችን ከባድ ዝናብ ከዘነበ ወይም በደጋው አካባቢ ከዘነበ ሸለቆው ይሞላል፡፡ ሸለቆው ሰፊ ስለሆነ ድልድይም ስለሌለው ከሞላ ከብቶችም ሆኑ ሰዎች መሻገር አይችሉም፡፡ ስለዚህ ውኃ እስኪቀንስ ይጠብቃሉ፡፡

ዛሬም እንደተለመደው የመንደራችን ልጆች ጧት ወደ መስኩ ያስማሩትን ከብቶች ፀሓይዋ ለመጥለቅ ስታዘቀዝቅ ወደ ሰፈራቸው ለአዳር መንዳት ጀመሩ፡፡ ነገር ግን ሸለቆው ጋር ሲደርሱ ሸለቆው ከመጠን በላይ ሞልቶ

# አባሪ አምስት

## ትምህርት አንድ:- ማዳመጥና መናገር

### ማዳመጥ

የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን አዳምጠው እንዲመልሱ ያድርጉና የመምህር መምሪያው ላይ ያለውን ምንባብ ረጋ ብለው ያንብቡላቸው፡፡ ቀጥለውም በምንባቡ ላይ ተመስርተው የቀረቡትን መልመጃዎች በትዕዛዞቹ መሠረት ያሰሩዋቸው፡፡

ጊዜው ርቆ ቢሄድም ትዝታው ከኔ ጋር ነው፡፡ እነዚያ ሽለቆዎች፣ ተራሮች፣ ሽንተረሮች፣ ጥንቸሎች፣ ሚዳቆዎች፣ ቀበሮዎች፣ ወዘተ. ሳሩ አፈሩ በአንድነት ተስለው በህሌናየ የሚቀርቡበትም ጊዜ አለ፡፡ ያቺ ጎጆዬ፣ ያቺ የቁርበት ምንጣፌ፣ ያ የበቆሎ ገንፎ፣ አሬራው፣ አይቡ፣አጓቱ፣ ወተቱና ቅቤው ሊረሱኝ አልቻሉም፡፡ ከጉረኖው ያሉት በጎችና ፍየሎች፣ ከበረቱ ያሉት ከብቶች እስካሁንም አልተረሱኝም፡፡ የዛሬን አያድርገውና ያኔ በጎችና ፍየሎች እጋልብ ነበር፡፡ በግልቢያውም ከፍተኛ ደስታ ይሰማኝ ነበር፡፡ ጠዋት የበላሁት ገንፎ ከሆዴ ሳይጠፋ እስከማታ ይቆያል፡፡

ከሳር ግጦሽና ከወንዝ መልስ ከብቶች ሲያርፉ ከአንድ ወደአንዱ ዛፍ ጥላ እየተሯሯጥኩ እጠጣ የነበረው የላም ወተት ጉልበቴ ሆኖ ቀርቷል፡፡ ያኔ ስለ በሽታ አምጪ ተህዋሲያን የምናውቀው ነገር አልነበረም፡፡ ወተቱ ተፈላም አልተፈላም የሚያመጣውን ሳንክ አላየሁም፡፡ ይሁን እንጂ እኔን ያበሳጨኝ የነበረው የበጎች በቀበሮ መበላት፣ የአህዮቼ መጥፌትና ማታ ስገባ የሚቀርብልኝ የአባቴ አለንጋ ነበር፡፡ ቡሬ የት አለች? ፣ ወደሉ ጠፍቷል፣ ጥጆቹ አልመጡም ምን ይሻለኛል? አወይ ጣጣዬ! በእነዚህ ነገሮች ተማርሬ ከከብት ተከታይነት መማር ይሻለኛል ብዬ ትምህርት ቤት ገባሁ፡፡

በራሴ ፍላጎት ትምህርት ቤት ስለገባሁ ትምህርቱም እየቀለለኝ መጣ፡፡ የደረጃ ተማሪ በመሆን በየጊዜው እሸለም ነበር፡፡ ሽልማቱም ተጨማሪ ብርታት ስለሰጠኝ ይሄው ዛሬ ለከፍተኛ ደረጃ በመብቃቴ እራሴንና ወላጆቼን በማገኘው ከፍተኛ ገቢ በመርዳት ላይ እገኛለሁ፡፡

(ዮናስ አድማሱና ሌሎችም፣አማርኛ ለኮሌጅ ደረጃ፣ቀ.ኃ.ስ ዩኒቨርሲቲ 1966)

### መናገር

በዚህ ትምህርት ሥር የተለያዩ ተግባሮች ቀርበዋል፡፡ ለየተግባራቱም ግልፅ የሆኑ ትዕዛዞች ተሰጥተዋል፡፡ ተማሪዎቹ ትዕዛዞቹን ተከትለው እንዲሰሩ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው፡፡ በመቀጠል የሕፃናት መብት በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በግላቸው እንዲያነቡ ያድርጉ፡

በኢኮኖሚ የዳበረችና ለዜጎቿ ምቹ የሆነች አገር እናደርጋታለን:: ለሀገራችን እድገት ባለን ዕውቀት፣ ገንዘብና ጉልበት ሁሉ መረባረባ አለብን:: ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት ዝግጁ ከሆንን ድህነትን ማሰናበት ከባድ አይሆንብንም:: በዚህ ስራ ውስጥ የወጣቱ ሚና ጎልቶ መውጣት አለበት::

## መልመጃ

በዚህ መልመጃ ሥር አራት የተለያዩ ትዕዛዞች ቀርበዋል:: የመጀመሪያው "ሀ" ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን ተማሪዎች በቃል እንዲመልሱ የሚጋብዝ ነው:: የሚቀጥለው "ለ"እውነት/ሐሰት በማለት እንዲመልሱ፤ ሦሥተኛው "ሐ" የማዛመድና አራተኛው "መ" ያገር ፍቅር መገለጫዎች ላይ ተማሪዎች ሐሳብ እንዲለዋወጡ የሚጠይቅ ነው:: በዚሁ መሠረት ጥያቄዎቹን እያነበቡላቸው መልሶቻቸውን እየተቀበሉዋቸው ተማሪዎችን ያሰሩዋቸው::

## መናገር

ለትምህርቱ መግቢያ እንዲሆን አንድ ተግባር ተሰጥቷል:: ተግባሩ የማዳመጥ ሂደትን የሚያደናቅፉ ሁኔታዎች ላይ ግንዛቤ እንዲያገኙ የሚረዳቸው ስለሆነ አሳታፊ በሆነ መንገድ ያሰሩዋቸው:: ቀጥሎ የቀረበውንም ተረት ያንብቡላቸው:: ቀጥሎም ወደ መልመጃዎች ይሂዱ::

## የመልካም አባት ኑዛዜ

አንድ ገበሬ ሞቱ በደረሰ ጊዜ ልጆቹን ጠርቶ ባጠገቡ አቁሞ የሚከተለውን ተናዘዘላቸው::ልጆቼ ሆይ! አሁን በሽታው ስለጠናብኝና እያጣደፈኝ ስለሆነ መሬታችን ውስጥ ወርቅ የደበቅኩበትን ቦታ ላሳያችሁ አልቻልኩምና ቦታውን በመደዳ ቆፍራችሁ እንድትፈልጉት አላቸው:: ልጆቹም አባታቸው ሞተው ከቀበሯቸው በኋላ ኑዛዜያቸውን ተከትለው ዶማቸውንና አካፋቸውን ይዘው ቦታቸውን ከዳር እስከዳር ቆፈሩት ይባላል::

ነገር ግን እንደዚያ ያላቸው ልጆቹ ሥራ እንዳይፈቱ ብሎ ነው እንጂ በእርግጥ ወርቅ ደብቆ አልነበረም::ልጆቹም ቦታውን ሁሉ ቆፍረው ወርቁን ባለማግኘታቸው፣ እንግዲህ ወርቁን እንደሆነ አላገኘነም::ስለዚህ የቆፈርነው ቦታችን ላይ ስንዴና ገብስ እንዝራ ተባብለው በሀሳቡ ተስማሙና ገብስና ስንዴ ዘሩበት::የዘሩትም ጥሩ ሆኖ ከፍተኛ ምርት ሰጣቸው::ከዚያም ያመረቱትን ስንዴና ገብስ እየሸጡ ወርቃቸውን ይገዙበትና ይሰበስቡ ጀመር:: በዚህ ዓይነት ጥቅማቸውን ካወቁ በኋላ ልጆቹ ሥራ እንዳይፈቱና መሬቱም እንዳይቦዝን ብለው እንጂ አባታቸው



ወርቅ እንዳልደበቁ ተረዱና መልካመ

(ከበደ ሚካኤል፣ ታሪክና ምሳሌ፣ 2

## መልመጃ

በዚህ መልመጃ ሥር ስድስት ትዕ

ይህ ትምህርት በተግባር ይጀም
እንዲለዋወጡ ያድርጉ::

የጥያቄ ለ እና ሸ ዓላማ ተማሪ
ሞያተኞችን በማነጋገር ሃሳባቸው
ጥያቄዎቹን እንደየትዕዛዛቸው ያ

ትህምርት ሁለት ተማሪዎች የግ
ለማስተማር የታሰበ ነው፡ በ
ያንብቡላቸውና በመቀጠል ተማ
ሲሳሳቱ ማስተካከያዎችን ይስጠ

## ትምህርት ሁለት፡- ማንበ

በትምህርቱ ሥር የቀረበውን
ምንባብ በግል እንዲያነቡ አ
የቀረቡትንም መልመጃዎች ያ

## ማንበብ

በዚህ ትምህርት ሥር የቀረበ
በዚህ ትምህርት ተማሪዎች
እየተረዱ ሌሎችንም ጨያ
ምሳሌዎች ያንብቡላቸው፤ እ
ትምህርት ይሸጋገሩ::

በዚህ ትምህርት ሥር ተ
ተግባር ቀርቧል:: አንድ ም
በቃላቸው እንዲጽፉ ያድርገ

ወርቅ እንዳልደበቁ ተረዱና መልካሙን አባታቸውን አመሰገኑ ይባላል።

(ከበደ ሚካኤል፣ ታሪክና ምሳሌ፣ 2ኛ መጽሃፍ ገጽ 85)

## መልመጃ

በዚህ መልመጃ ሥር ስድስት ትዕዛዞች አሉ። በትዕዛዞቹ መሠረት ያሰሩዋቸው።

ይህ ትምህርት በተግባር ይጀምራል። ስለአገር ፍቅር በስሙት ላይ ሐሳብ እንዲለዋወጡ ያድርጉ።

የጥያቄ ስ እና ሽ ዓላማ ተማሪዎች ሚና መጫወት እንዲለማመዱ ማድረግና ሞያተኞችን በማነጋገር ሃሳባቸውን በንግግር እንዲገልፁ ማለማመድ ነው ስለዚህ ጥያቄዎቹን እንደየትዕዛዛቸው ያሰሯቸው።

ትህምርት ሁለት ተማሪዎች የግጥምን ዜማ ጠብቀው እንዴት ማንበብ እንዳለባቸው ለማስተማር የታሰበ ነው፡ በዚሁ መሠረት ግጥሞቹን በመጀመሪያ እርሶ ያንብቡላቸውና በመቀጠል ተማሪዎች እንዲያነቡ በማድረግ ያለማምዱዋቸው። ሲሳሳቱ ማስተካከያዎችን ይስጡዋቸው።

## ትምህርት ሁለት፡- ማንበብና መፃፍ

በትምህርቱ ሥር የቀረበውን ተግባር ካሰሩ በኋላ በመጽሐፋቸው ላይ ያለውን ምንባብ በግል እንዲያነቡ አድርጉ። በዚሁም በትዕዛዞቹ ላይ ተመስርተው የቀረቡትንም መልመጃዎች ያስሩዋቸው።

### ማንበብ

በዚህ ትምህርት ሥር የቀረበው ስለግጥም አጻጻፍ ግንዛቤ የሚያዳብር ሀሳብ ነው። በዚህ ትምህርት ተማሪዎች ሐረግንና ስንኝን እንዲለዩ በተሰጡት ምሳሌዎች እየተረዱ ሌሎችንም ጨምረው ሀሳብ ያስጨብጡዋቸው። የተሰጡትንም ምሳሌዎች ያንብቡላቸው፤ እነርሱም እንዲያነቡ ያድርጉ። ከዚህያም ወደ ዋናው ትምህርት ይሸጋገሩ።

በዚህ ትምህርት ሥር ተማሪዎች በቃል መጻፍ እንዲችሉ የሚለማመዱበት ተግባር ቀርቧል። አንድ ምንባብ መርጠው ያንብቡላቸው። ከዚህያም ተማሪዎች በቃላቸው እንዲጽፉ ያድርጉ።

# አስቴር ገኖ

የትውልድ ስሟ ገኖ ሳልባና ይባላል። በ1874ዓ.ም በጅማ ዞን ሊሙ አካባቢ ተወለደች በ1880ዎቹ የአካባቢው አገር ገዥ ሕዝቡ ቤተ መንግሥት እንዲሠራለት አዘዙ። አንዳንድ ሰዎች ግን ትዕዛዙን እምቢ በማለት ቤተመንግሥቱን በመሥራት ላይ ሳይሳተፉ ቀሩ። ገዥውም በዚህ ጉዳይ በመናደዱ በቤተመንግሥቱ ሥራ ላይ ያልተሳተፉ ቤተሰቦች ታድነው በባርነት እንዲሸጡ ትዕዛዝ አስተላለፉ። በዚህ ትዕዛዝ ከተሸጡት ህፃናት መካከል አንዷ ገኖ ነበረች። በዚህ ወቅት ዕድሜዋ አስር ዓመት ነበር። ለመጀመሪያ ጊዜ ለሀበሻ ነበር የተሸጠችው። የመጀመሪያ ገገርዋን ለሁለት ዓመታት ካገለገለች በኋላ ለሌላ ሰው ተላልፋ ተሸጠችና የባሪያ ነጋዴዎች ወደ አረብ በመርከብ ሊያሻግሯት በቀይ ባህር በኩል አጓጓዟት። በዚህ ጊዜ ለጋ ወጣትና የ12 ዓመት ልጅ ነበረች።

ነጋዴዎቹ ወደ አረብ አገር ሊያሻግሯት ጥረት እያደረጉ እያሉ አካባቢውን እየጠበቁ በነበሩ የጣሊያን ወታደሮች ቁጥጥር ስር በመዋል እነገኖን ነፃ በማውጣት በአካባቢው ለሚኖሩ የሲዊድን ሚስዮኖች ሰጧቸው። ገኖን ጨምሮ 24 ሴቶች ልጆችን ነፃ አወጧቸው። ከነዚህም ውስጥ ዲንቦ ገርባ (የኦነስሞስ ነሲብ ባለቤት) በኋላ ላይ ሊድያ ዲንቦ የተባለችውና ፊበን ሂርጴ የተባለችው አብረው ነበሩ። እነዚህ ሴቶች የሲዊድን ሚሲዮኖች እጅ እንደገቡ ወዲያውኑ ትምህርታቸውን ቀጠሉ። የክርስትና እምነትን ከተቀበሉ በኋላ አዲስ ስም ወጣላቸው። ገኖ ሳልባናም አስቴር ገኖ ተብላ የተሰየመችው በዚሁ መሠረት ነበር።

አስቴር ገኖ የተለየ ችሎታ ነበራት። በኦሮሞ ባህል ስም የወጣላቸው፣አባባልና ተረትና ምሳሌዎች ላይ የላቀ እውቀት ነበራት። ለኦሮሞ ስነቃልና ስነጽሁፍ በወቅቱ ሊሞክሩ ከሚችሉ በላይ ትሠራ ነበር። በተለያዩ ቋንቋዎች የተፃፉትን የእምነት መጻሕፍትንም ከኦኒስሞስ ነሲብ ጋር ወደ አፋን ኦሮሞ ቋንቋ ለመተርጎም የተመረጠችበትም ምክንያት በዚሁ ችሎታዋ ነበር። ችሎታ ብቻ ሳይሆን ተነሳሽነትም እንደነበራት ይነገራል። የመጀመሪያ ሥራዋ "የመጀመሪያ መምህር" የሚለው በኤርትራ እምኩሉ በተባለ ሥፍራ በ1894 የታተመ ነበር። በአስቴር የተተረጎሙ ሌሎች መፃሕፍት አዲስ ኪዳንና የእግዚአብሔር ምህላ የተባሉ መጻሕፍት ናቸው። በአስቴር ወደ አፋን ኦሮሞ ቋንቋ የተተረጎመው ሌላው መጽሐፍ ዶክተር ባርቴስ የፃፈው መጽሐፍ ቅዱስ ሲሆን፣ "ሁለት ጊዜ ሃምሳ ሁለት ዜናዎች" በሚል ርዕስ የታተመ ነው። በሠራቻቸው ሥራዎች ሁሉ የኦኒስሞስ ድጋፍ አልተለያትም። ከዚህም ሌላ 200 የፍቅር የኦሮሞ የዘፈን ግጥሞች 'ስነቃል' በማለት አሳትማለች። ከነዚህም ሌላ ብዙ ሥራዎች አሏት። አስቴር እነዚህን ስራዎች ከሰራች በኋላ ወደ ወለጋ ገባች።

ዘመኑም በ1904 ነበር:: አብረዋት የነበሩት (ሂካኦኒስሞስ)፣ዲሞስህርጼና ሌሎች ሆነው ሚያዝያ 28፣ 1904 ነቀምቴ ገቡ:: ንጉስ ኩምሳሞረዳም በደስታ ተቀበሏቸው:: የተወሰነ እረፍት አድርገው ከሰነበቱ በኋላ ከንጉሱ ጋር ሆነዉ ወደ ነጆ ሄዱ:: መኖሪያና ትምህርት ቤት እንዲሰሩ ሁኔታዎች ተመቻቹላቸው:: ህያ የሚያህሉ ተማሪዎችን መዝግበዉ የትምህርት ሥራን ቀጠሉ:: አስቴርም የሴት ተማሪዎች መምህር ሆነች:: ይሁን እንጂ በወቅቱ በነበሩ አንዳንድ ችግሮች ምክኒያት አካባቢውን ለቀው ወደ ነቀምቴ ተመለሱ:: ነቀምቴ ላይም እንደበፊቱ የሴት ተማሪዎች መምህር ሆነች::

አስቴር ከሕፃንነት ጊዜዋ ጀምሮ ለኦሮሞ ስነጽሁፍ ዕድገት በተለያዩ መንገዶች አስተዋጽኦ ስታደርግ ቆይታ በ1964ዓ.ም በ90 ዓመቷ ነቀምቴ ላይ አረፈች:: ታሪኳ በኦሮሞ ሥነጽሁፍና ትምህርት ሁል ጊዜም ሲታወስ ይኖራል::

(ከአፋን ኦሮሞ ቋንቋ፣የመምህር መምሪያ 8ኛ ክፍል ለማስተማሪያ እንዲሆን ተደረጎ የተወሰደ)

ለ. በምንባቡ መሠረት ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች መልሱ::

1. የአስቴር ገኖ ስም ማን ይባላል?
2. የአስቴር ገኖ የትውልድ አካባቢየት ነበር?
3. ለነአስቴር ገኖ በባርነት መሸጥ ሰበብ የሆነው ምንድነው?
4. እነ አስቴር ገኖ ከባሪያ ነጋዴዎች ነፃ የወጡት በምን አጋጣሚ ነበር?
5. አስቴር ገኖ ወደ ወለጋ የገባችው በየት በኩል ነው?

ሐ. በምንባቡ መሰረት ትክክል የሆነውን ሀሳብ እውነት ስህተት የሆነውን ሐሰት በማለት መልሱ::

1. እነ አስቴር ገኖን የተቀበለው የወለጋ ንጉሥ ኩምሳ ሞረዳ ነበር::
2. እነ አስቴር ገኖ ከነጆ የወጡት አካባቢውን ስላልወደዱት ነበር::
3. አስቴር ገኖ ለመጀመሪያ ጊዜ ተሸጣ የነበረው ለአረብ ነጋዴ ነው::
4. የባሪያ ነጋዴዎቹ እነ አስቴር ገኖን ወደ አረብ አገር የማሻገር ፍላጎት ነበራቸው::
5. አስቴር የመፃፍ እንጂ ከሌላ ቋንቋ ወደ አፋን ኦሮሞ የመተርጎም ችሎታ አልነበራትም::

# አባሪ ስድስት

2.1. ማንበብ

ሀ. የሚከተሉትን ስእሎች በትኩረት ተመልከቱና ከስእሎቹ ቀጥለው በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ



ስዕል 1



ስዕል 2



ስዕል 3



ስዕል 4

1. ከስዕል አንድ ስለኦሮሞ ባህላዊ ጋብቻ ስርአት የሚያውቅ ተማሪ በስእሉ ላይ ተመስርቶ ስለ ጋብቻ ስርአቱ ይተርክላችሁ፤ የተቀራችሁት በጥሞና አዳምጡ፡፡
2. በስዕል ሁለት ክብ ሰርተው የተቀመጡ ሽማግሌዎች ምን እያደረጉ ነው? ስለዚህ ባህል የሚያውቅ ተማሪ ሲያስረዳ የተቀራችሁት አዳምጡ፡፡
3. በስዕል ሦስት የምታዩዋቸው ሴቶቹ የያዟቸው ምን ይባላሉ? ባህላዊ አገልግሎታቸውስ ምንድነው?
4. ስእል አራት ስለምትመለከቱት የባህል ጭፈራ የሚያውቅ ተማሪ ወይም ሌላ ሰው/እንግዳ ጋብዙና መቼና የት፣ ለምን ለምን ጊዜ እደሚከወን ሲያስረዳ አዳምጡ፡፡